
# ሐመር

ሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኅዳር-ታኅሣሥ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም



## መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን

(34-1967 ዓ.ም)

© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ትምህርተ ወንጌል ለከተሜው ብቻ ...

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ሚያስተምረን መምህራንና ሊቃውንት የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተምሩ ከተማና ገጠርን እያማረጡ አልነበረም:: ዛሬ ከዋናው አውራ ጎዳና አጠገብ ወይም ከተማ ውስጥ ያልተተከለች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰበካዋ ምእመናን ትምህርተ ወንጌልን የሚያገኙበት ሁኔታ እየተዳከመ የመጣ ይመስለኛል:: አጽራረ ቤተ ክርስቲያን በከተማው የስብከተ ወንጌል ትጋትና የምእመኑ ንቃት አፍረውና ተዳክመው ወደ ገጠሩ እየገቡ ከትመውበታል:: በዚያም በአንድ እምነትና ባህል ተሳስሮ የኖረውን ምእመን እያለያዩት ይገኛሉ:: ከትምህርተ ወንጌሉ መስፋፋት አኳያ ዘላቂ ዕቅድ ካልተያዘ በቀር የገጠሩን ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ቀስበቀስ እንዳናጣ እሰጋለሁ::

*ምሥራቅ አቦነህ*
*ቡታጅራ*

## ለይተን ብናውቅ

በተለያዩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በተደጋጋሚ እንዳየሁት ወደ ቅጽሩ ሲገባና ከቅጽሩ ሲወጣ ያለው ግፊያና ትርምስ አስቸጋሪ ነው:: በመግቢያና በመውጫ በሮች ለይተን መጠቀም ይኖርብናል:: ለዚህም የመግቢያና የመውጫ በሮች በግልጽ ተለይተው ቢታወቁ ምእመናን ለብዙ አደጋ ከመለጋጥ ይድናሉ:: በተለይ በበዓላት ቀናትና ከሠርክ ጉባኤያት በኋላ ከግፊያና ትርምሱ «ተጠቃሚ እንሆናለን» የሚሉትን ለመከላከል ያስችላል:: በሌላ በኩል በቅጽር ግቢው የተለያዩ ሥፍራዎች ምእመናን እንደ የጸታችን የምንጸልይበትን፣ የምንቆምበትንና የምንቀመጥበትን ቦታ ለይተን ማወቅ አለብን:: ከዋናው መግቢያ በር ጀምሮ በግቢው ውስጥ ሰዎች ሊተላለፉባቸው በሚችሉባቸው መንገዶች በግንባር መሬት ላይ ወድቆ መሳለም፣ ቆሞ መጸለይ ወይም ሻማና ጧፍ ማብራት ወዘተ አገባብ አይመስለኝምና ቢታረም መልካም ነው::

*ፈቃዱ ሙሉነህ*
*አዲስ አበባ*

## ተስፋ እንደ መቁረጥ የከፋ ኃጢአት የለም

የኃጢአት መጨረሻው ሞት ሲኾን ዋዜማው ተስፋ መቁረጥ ነው:: የፍላጎታችን ክብደት ኃጢአት እንድንሠራ ይገፋፋናል:: ዲያብሎስም በመጀመሪያ ልንሠራ ያልወደድነውን ኃጢአት እንድንሠራ ያደፋፍረናል:: ኃጢአቱን ከሠራን በኋላ ደግሞ የሠራነው ኃጢአት እጅግ ከባድ እንደ ሆነና ንስሐ ብንገባ እንኳ ይቅር እንደ ማንባል አድርጎ ያሳየናል:: እኛ ግን ተስፋ መቁረጥ የለብንም:: ብንወድቅ እንነሣለን:: ተስፋችን እግዚአብሔር ነውና:: መዝ.33÷7::

*ዲ/ን ጋሻሁን ወ/ሚካኤል*
*ምዕ.ሸዋ- ባኮ*

## እውነቱን እንናገር

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር አምስት ከአንባብያን ለአንባብያን ዓምድ ላይ ከምርጫ - 97 ጋር በተያያዘ በተፈጠረው ችግር «ስለ ሀገር ማዘንና መጸለይ ይገባል» በሚል ርእስ ወንድማችን ባስተላለፋልን መልእክት፡ - «እግዚአብሔር ለሁሉም እውነቱን ገልጦ መተማመንን እንዲሰጥልን መጸለይና ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያለው የማቀራረብ ተቋማዊ ሚናዋን መጫወት እንዳለባት» አመልክተዋል:: ተገቢና ትክክለኛ መልእክት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ተቋማዊ ሚናዋን መጫወት ያለባት ግን እውነትን ወደ ጎን በማድረግና በወገናዊነት መሆን የለበትም:: ለሁሉ መጸለይ ታላቅ ሓላፊነትዋ ሲሆን እንደ ተቋም ግን እውነትን በግልጽ መናገር አለባት፤ እውነት እግዚአብሔር ነውና:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ::

*ቸርነት ዘውዴ*
*ባሌ-ጊንር*

## መዘበቻ እንዳንሆን

በጨንቻ ወረዳ የከተማዋን አምስት ቀበሌዎች ጨምሮ በአጠቃላይ 50 ቀበሌዎች ይገኛሉ:: በእነዚህ ቀበሌዎች ደግሞ በቅርቡ ቅዳሴ ቤታቸው ተከብሮ አገልግሎት ከሚጀምሩት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ተደምሮ 40 ያህል አብያተ ክርስቲያናት ይኖራሉ:: ወደፊቱም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚታነጹ ይኖራሉ:: እኔን የሚያሳስበኝ ግን አብያተ ክርስቲያናቱ በቁጥር የመ[illegible]ዛታቸውን ያህል አገልጋይ ካህናት ያልተሟሉላቸው፣ በወር አንድ ቀን ብቻ የሚቀድስባቸው ናቸው:: ይህም በምእመኑ ላይ የሚያመጣው ጉዳት እንደ ተጠበቀ ኾኖ የመናፍቃኑ መዘባበቻ አድርጎናል:: ስለዚህ በ50 ቀበሌዎች የግድ አንዳንድ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ከመትከል ይልቅ ቀድሞ የነበረንን እንደ ሚገባ ብንይዝ፣ ለመጨመር ካስፈለገ ደግሞ በቅድሚያ ተዘጋጅተንበት ቢሆን መልካም ነው::

*ዲ.ን ደረጀ ግርማ*
*ዶርዜ ደብረ ሲና ቅድስት*
*ኪዳነ ምሕረት*
*ቤተ ክርስቲያን ሰንበት*
*ት/ቤት*


አዲስ መጽሐፍ

**ሕብረ ብዙ**

*ርዕስ ጉዳይ:-*

⇒ አዋልድ መጻሕፍትና የቤተ ክርስቲያን ጸሎታት መጽሐፍ ቅዱሳውያን ናቸው፤ ከመሠረታዊው የክርስትና ትምህርት ጋርም የተስማሙ ናቸው::

⇒ የኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ታሪክ

(በተለይ ለአብነት ተማሪዎች የተዘጋጀ)

*አዘጋጅ:-* ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ
የሰሜን ወሎና ዋግ ሕምራ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

*አከፋፋይ:-* በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን

ስልክ:- 011-122-86-01
011-213-81-30

**E-mail: MK_distribution@yahoo.com**


የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር 81164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_ distribution @ Yahoo.com

ሐመር
፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፮
ኅዳር/ታኅሣሥ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

*« የሕዝብ ዕድገት፣ አንድነት፣ ሰላምና ፍቅር በእጃችን ነው::»*

«ቤተ ክርስቲያናችን ድኻ ናት ብሎ መናገር ኃጢአት ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን ሰማያዊ ሀብት ብቻ ሳይሆን ምድራዊ ሀብትም ተሟልቶላታል:: ቤተ ክርስቲያናችን የጎደላት ነገር የለም:: የጎደለ ነገር ካለ ተጠያቂዎቹ እኛው ነን:: በእኛ ላይ ጉድለት ካልተገኘ በስተቀር ቤተ ክርስቲያናችን ድኻ አይደለችም:: ታሪካዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን በየጊዜው ታሪክ እየሠራች ነው:: ነገር ግን የእኔና የእናንተ ጽኑ እምነት ያስፈልጋል:: በሌላ በኩልም እኛ የሌላ መሣሪያ መሆን የለብንም:: የሕዝብ ዕድገት፣ አንድነት፣ ሰላምና ፍቅር በእጃችን ነው:: የክርስቶስ ወታደሮች መሆን ያስፈልጋል:: ከዚያ ውጭ የሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያናችን ዓላማ ውጭ ነው:: ....» */ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በ24ኛው መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቃለ በረከት የተወሰደ/::*

*«ቤተ ክርስቲያን የምታገናኝ ናት»*

«ቅዱሳን ሐዋርያት በመጀመሪያ ብዙ የታገሉት እስራኤልንና አሕዛብን ለማገናኘት ነው:: ቤተ ክርስቲያን የምታገናኝ ናት፤ ሕዝብንና ሕዝብን የምታዋሕድ አንድ የምታደርግ ናት:: ስለዚህ ነው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድ ሕዝብ ያደረገችው:: አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ ነው፤ ምንም ብትሉ ምንም ብትሉ የማይከፈል ሕዝብ ነው:: ደኅና አድርጋ መሥርታለች ቤተ ክርስቲያኒቱ:: የአባቶቻችን ነፍስ ይማርና ደኅና አድርገው መሥርተውት አንድ ሆኗል:: ይኼን እንዳታፈርሱ ነው ቤተ ክርስቲያን አሁን የምታስተምረው፤ በየጊዜው የምትሰበስበው ይህን ለማስተማር ነው::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ብቻ ሳይሆን በየሄደችበት በውጭ ሀገርም የምታስተምረው ሕዝብና ሕዝብ እንዲገናኝ÷ እንዲተባበርና እንዲተዛዘን÷ አንድ እንዲሆን÷ መለያያ ምልክት እንዲጠፋ ነው:: የጌታችንም ትምህርት ይኸው ነበር፤ ሕዝብንና ሕዝብን አንድ ለማድረግ:: ኹሉም የብርሃን ልጅ እንዲኾን ነበር የጌታችን ትምህርቱ:: .... እርስ በእርሳችን ብቻ ሳይሆን ደግሞ ከእርሱ ጋርም አንድ እንድንሆን ነው:: ከመ ይኩኑ አሐደ ብነ ከማነ፤ እኛ እርስ በእርሳችን ያለንን አንድነት እንድናጠናክርና ከእግዚአብሔር ጋር ደግሞ ያለንን ግንኙነት እንድናጠናክር ነው::» */የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ካስተማሩት ትምህርት የተወሰደ/::*

*«ሕሙማንንና የታሰሩትን መጠየቅ*
*የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ነው»*

«የታሰሩትን በመጠየቅና በመጎብኘት በኩል ቀሳውስትና ጳጳሳት ብቻ ሳይሆኑ ምእመናን ሁሉ ለዚህ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: ጌታችን መድኃኒታችን ያስተማረን ይህን ነው:: ራሱ ወደዚህ ዓለም የመጣው እኛን ከእስር ለመፍታትና ነጻነትን ለመስበክ ስለሆነ ዓርማችን ሊኾን የሚገባው ይኸው ነው:: .... ቤተ ክርስተያንማ ከሐዘንተኞች ጋር፣ ከእስረኞች ጋር ነው ጉዞዋ:: በእስር ቤት ያለ ሰው÷ ሰው ይናፍቀዋል:: እስረኞች ሰው ሲጠይቃቸው ትልቅ ደስታ ይሰጣቸዋል:: መታሰር ቀላል ነገር አይደለም:: ለዚህ ነው ሕሙማንንና የታሰሩትን መጠየቅ የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ነው የምንለው:: .... ይኼ ነው የእግዚአብሔር ተከታታይነታችን መታወቂያ:: እርሱ ለታሰሩትና ለተጎዱት አይደለም እንዴ የመጣው? በመስቀል የተሰቀለው ለማን ነው? እኛም የእርሱ ተከታዮች ከሆን ይህን ማንጸባረቅ አለብን::» */ከየካቲት 9 ቀን 1968 ዓ.ም - መስከረም 1 ቀን 1975 ዓ.ም ድረስ ለሰባት ዓመታት በደርግ ታስረው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ከተናገሩት የተወሰደ/::*

ዋና አዘጋጅ - ዲ/ን መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ - አሉላ ጥላሁን
ከፍተኛ ሪፖርተር - መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊዎች - ፍቅርተ ኃይሌ
- ጸዳሉ ሁንዴሳ

ስልክ: 011-155-63-28
E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል::

# ይዘት

የማኅበረ መልእክት

• በችግርና በፈተና ወቅት ከቤተ ክርስቲያን ብዙ ይጠበቃል.......................... ፪

ደብዳቤዎች ......................................... ፫

ከስሞኑ በረከት

• ምድረ ፍልስጥኤል በገና ዋዜማ.......................... ፮

ትምህርተ ሃይማኖት

•ሰባቱ ኪዳናት.......................................... ፱

•ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዱስ......................... ፲፫

•መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ............... ፲፯

/ ከ34 - 1967 ዓ.ም./

ኪነ ጥበብ

• ከሞት ባሻገር ......................................... ፳፭

እናስተዋውቃችሁ

• አቡነ ዮሐንስና ከሣቴ ብርሃን.......................... ፳፫

• ልደተ ስምዖን........................................ ፴

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

• ሐዋርያዊነት በኢትዮጵያ እንዴት?.................. ፴፪

ሐመረ ሕይወት

• መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ..................... ፴፭

*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::*

© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

***በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::***

> **በችግርና በፈተና ወቅት ከቤተ ክርስቲያን ብዙ ይጠበቃል**

ባሳለፍነው ጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ማገባደጃ በሀገራችን በተፈጠረው አሳዛኝ ክሥተት የሲቪሎችም የጸጥታ አስከባሪዎችም ሕይወት አልፏል፤ ንብረት ወድሟል:: በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ታስረዋል::

የግንቦት 1997 ዓ.ም የክልልና የተወካዮች ምክር ቤት ምርጫን ተከትሎ የተፈጠረው ይህ ክሥተት ከሰው ሕይወትና ከንብረት ጉዳት በተጨማሪ ስጋትና ያለመተማመንን፣ ጠባብነትንና ዘረኝነትን፣ ፍርሃትንና ተስፋ መቁረጥን፣ ወዘተ... በሕዝቡ ውስጥ እንዲነግሥ አድርጓል::

የዚህ መልእክት ዓላማ ስለዚያ አሳዛኝ ክሥተት ትንታኔ መስጠት አይደለም:: ነገር ግን ይህን የመሰለው ሁኔታ በሀገር ላይ ሲፈጠር የቤተ ክርስቲያን ሚና ምን መሆን አለበት? የሚለውን አስከትሎ ለማንሣት ነው እንጂ:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የ2000 ዘመን ታሪክ፣ ከ20ሺሕ በላይ አብያተ ክርስቲያናት፣ ከ45 ሚልዮን በላይ ምእመናን ያሏት ታሪካዊት፣ አንጋፋና ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ተቆርቋሪና ተጠሪ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት:: በዚህች ሀገር የሚፈጠር ክፉም ሆነ በጎ ነገር በዋናነት ተጽዕኖውን ያሳርፍባታል:: ደርቡሽ ኢትዮጵያን ሲወር የጎንደርን አብያተ ክርስቲያናት አጠፋ፤ እንግሊዞች በመቅደላ ውጊያ የቤተ ክርስቲያንን ቅርስ ዘረፉ፤ ጣልያን በአምስት ዓመቱ ወረራ ካህናትዋንና ጳጳሳትዋን ገደለ፤ ገዳማቷንና አድባራቷን አቃጠለ፤ ቅርሷን ዘረፈ:: በሶማልያ ጦርነት ጊዜ አያሌ አብያተ ክርስቲያናት ፈረሱ:: ሌላም ሌላም....

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሕዝቡን መከራ ተቀብላ በፀረ ቅኝ አገዛዝ ጦርነት ሕዝቡን መርታለች:: የዐድዋ ጦርነት ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው:: ሰማዕቱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በፀረ ቅኝ አገዛዝ አቋማቸው ምክንያት በግራዝያኒ ጦር ተሠውተዋል:: በኢትዮጵያ በ1965/66 ዓ.ም. እና በ1977 ዓ.ም ከባድ ድርቅ በደረሰ ጊዜ ሕዝቡን በመመገብ፣ ዕጓለ ማውታንን በማሰባሰብ፣ የጤና ተቋማትን በማቋቋም ታሪክ የማይዘነጋው ታሪክ ሠርታለች::

ይህች ታላቅ ታሪካዊት፣ ባዕለ ጸጋ ቤተ ክርስቲያን የዘረጋችው መዋቅር የማይደርስበት መንደርና ጐጥ፣ ወንዝና ተራራ የለም፤ በዕቅፏ ያልያዘችው ኢትዮጵያዊ ብሔር፣ብሔረሰብ፣ ነገድ፣ ቤተሰብ የለም፤ በመሆኑም በችግርና በፈተና ወቅት ኢትዮጵያውያን ከቤተ ክርስቲያን ብዙ ይጠብቃሉ::

***የቅድመ ምክር አገልግሎት ይጠብቃሉ::*** ሁኔታዎች የመጨረሻ ጠርዝ ላይ ደርሰው አላስፈላጊ ነገር ከመፈጠሩ በፊት ወደ በጎ ሁኔታ የሚለወጡበትን መንገድ መምራት፣ መምከር፤ ስሕተተኛው ከስሕተቱ እንዲመለስ ማረም፤ የተወጠረው እንዲላላ፣ የከረረው እንዲለዝብ ማስተማርና መገሠጽ ከቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል:: ሀገር በርእዮተ ዓለም ምክንያት መለያየት ሲገጥማት፣ የርእዮተ ዓለም ልዩነቶችም ወደ ኃይልና እንካ ሰላንትያ ሲለወጡ ከሁለቱም ርእዮተ ዓለም ውጭ የሆነ፤ ለሁለቱም ቅርብ የሆነ፤ በሁለቱም የሚታመን አካል የሽምግልና ሐሳብ ማቅረብ አለበት:: ለዚህ ደግሞ ከኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያን የተሻለ አካል ማግኘት አይቻልም:: በመሆኑም አንተም ተው፣ አንተም ተው፤ ሁላችሁም ይህን ተዉ፤ በዚህ ሂዱ፤ ብላ ችግ ሮች ከመፈጠራቸው በፊት የእናትነት ተግ ባርዋን ታከናውን ዘንድ ልጆቿ ይጠብቃሉ::

***የማስታረቅ አገልግሎትን ይጠብቃሉ::*** በአሁኑ ሰዓት በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች፣ በልዩ ልዩ ብሔረሰቦች፣ በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል የመቃቃር፣ የዝምድና መሻከር፣ የቂም በቀል፣ የጠብና የጥላቻ ስሜቶች እየተፈጠሩ ናቸው:: ነገሮች በዚህ መልክ መቀጠል የለባቸውም:: ፍቅርና አንድነታችን፣ የመተባበርና የመተጋገዝ ባህላችን፣ ችግሮችን ተቻችሎ የማለፍ ልምዳችን፣ <መወለድ ቋንቋ ነው> የሚለው አመለካከታችን ተመልሶ መምጣት አለበት:: ለዚህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን የአስታራቂነት ሚና ወሳኝ ነው፤ ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ሊያስታርቁ የለመኑ ቅዱሳን ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ከላይ የገለጥነው ቀላል ነገር አይከብዳትምና::

***የማረጋጋትና የማጽናናት አገልግሎትን ይጠብቃሉ::*** «ልጆቻችን የት ናቸው?» የሚሉ ወላጆች፣ ንብረት የጠፋባቸው ዜጎች፣ ወዳጅ ዘመድ የሞቱባቸው ወገኖች፣ «ነገ ደግሞ ምን ይመጣ ይሆን?» የሚሉ ግለሰቦች፣ ወዘተ መረጋጋትንና መጽናናትን ይጠብቃሉ:: በዚህም በዚያም ሕይወታቸውን ላጡት የፍትሐትና የመታሰቢያ ጸሎት መደረግ አለበት:: የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕይወታቸውን ላጡት ወገኖች የኅሊና ጸሎት አድርጓል:: ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በተለያየ አጋጣሚ በሞት ለተለዩት ልጆቿ ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ አለባት::

በልዩ ልዩ ምክንያቶች የታሰሩ ዜጎች ያሉበትን ሁኔታ /በቅርቡ ብፁዕ አቡነ ኢሳይያስ እንዳደረጉት/ በእናትነቷ በመኅብኝት ለቤተሰብ ማሳወቅ፣ መንግሥት በዐቅም እጥረት ሊያሟላቸው ያልቻላቸውን ሁኔታዎች በርዳታ ማሟላት፣ የታሰሩትን መምከር፣ ማስተማርና ማጽናናት፤ የፍርድ ሂደቱ የሚፋጠንበትን ሁኔታም ማመቻቸት ይገባል::

***ተመሳሳይ ክሥተት እንዳይደገም መሥራት፤*** የመወያየትና ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያና በሕግ መስመር የመፍታት ባህል እንዲዳብር፥ ነገሮች ከርረው የመጨረሻ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት የሚፈቱበት ነገር እንዲመቻች፣ በግለሰብና በኅብረተሰብ ደረጃ ቂምና በቀል ቀርቶ ይቅር ባይነትና መቻቻል እንዲሰፍን ትሠራ ዘንድ ልጆቿ ቤተ ክርስቲያንን ተስፋ ያደርጋሉ::

በየዱሩ በየገደሉ፣ በየዋሻው በየፍርኩታው የሚገኙ አበው ተግተው እንዲጸልዩ፤ መምህራኑ ወንጌል ፍቅርንና መቻቻልን፣ ዕርቅንና ሰላምን ጸንተው እንዲያስተምሩ፤ በሁሉም ዘንድ ፈሪሃ እግዚአብሔር አድሮ፣ ትዕግሥትና መቻቻል ሰፍኖ፣ ሀገራችን በሰላምና በዕድገት ጎዳና ወደፊት ትገሠግሥ ዘንድ ካህናት በየአካባቢያቸው ገባርያነ ሰላም ሆነው እንዲሠሩ አደራችን ከፍ ያለ ነው:: አምላከ ሰላም መድኃኔ ዓለም÷ሰላሙን፣ ፍቅሩንና አንድነቱን ይስጠን:: አሜን::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## «ያለፈው ዘመን ይበቃኛል»

የኛያ አንድ ዓመት ወጣት ስሆን በጌድኦ ዞን ማረሚያ ቤት የዐሥራ አራት ዓመት ፍርደኛ ሆኜ ለሰባት ዓመታት በማረሚያ ቤቱ ቆይቻለሁ፡፡ የቀረኝን ጊዜ አምላክ በሰላም እንዲያስፈጽመኝ በቅዱሳኑ ቃል ኪዳን እማፀናለሁ፡፡ ውድ አዘጋጆች፡- በ13ኛ ዓመት ቁጥር አምስት እትም የወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ «ያለፈው ዘመን ይበቃል» በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ ይህ ነው የማይባል ትምህርትና ምክር ለግሦኛል፡፡ ርትዕት ሃይማኖትን ከአበው ካህናት ተምሬአለሁ፡፡ ፍጹም የኾነ መመለስን ከቅዱስ ጳውሎስ ተምሬአለሁ፡፡ ይህን ሁሉ በርጋታ ስረዳው እውነትም በኃጢአትና በበደል የኖር ኩበት ያለፈው ዘመን ይበቃኛል፡፡

በሸበሸ ባሻ

ጌድኦ ዞን ማረሚያ ቤት

## ተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ቢታነጽ

ፀአገራችን በበረሓማነቱ በሚታወቀው የአፋር ክልል ክርስትና የሚፈለገውን ያህል አልተስፋፋም፡፡ በሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና እንዲሁም በፈንታሌ ወረዳ የምትገኘው የአዋሽ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት አባላት እንቅስቃሴ ሊበታታ የሚገባው ነው፡፡ ኾኖም ከተማው በጣም እየሰፋ ከመምጣቱ የተነሣ ምእመኑ ባለችው አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌሉን ለመከታተል ካለመቻሉም በላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ በርቀቱ ምክንያት ቁጥሩ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን በአቅራቢያው ይታነጽ ዘንድ በሚመለከተው አካል ቢታሰብበት፡፡

ታምራት ለገሠ

መልካ ወረር

## «ምንደኛዋ»

«ምንደኛዋ» በሚል ርእስ በ13ኛ ዓመት ቁጥር አምስት ሐመር መጽሔት እትም ኪነ ጥበብ ዓምድ በትዕግሥት ታፈረ የቀረበው አጭር ልቦለድ ራሳችንን እንድንመረምር የሚረዳን ነው፡፡ መስተካከል ነበረበት የምለው ነገር አለኝ፡፡ ከቅዳሴ በኋላ በተሰጠው ትምህርት የ«ምንደኛዋ» የቀድሞ አሠሪ «ምንደኛዋ» አሁን ላለችባቸው አሳዳሪ «ሌባ ናት» ብለው ተናግረው ሄደዋል፡፡ ከዚህ ይልቅ «ይህች ሴት ከእኔ ጋር በነበረችበት ወቅት አሠቃይቻታለሁ፤ በድያታለሁ፤ አስታርቁኝ» ብላ ጠይቃ ይቅር አባብለው ቢታረቁ፥ መምህሩም የዘሩት ቃል ፍሬ እንደ አፈራ ቢያሳይ፤ ምክንያቱም ጥልን አስወግዶ መታረቁ ለአንባቢው ትምህርት ስለሚሰጥ ነው፡፡

ጸጋዬ ዘውዴ

ወልድያ

## «ደባ» ተውኔት

«ደባ» በሚል ርእስ በማኅበረ ቅዱሳን ተዘጋጅቶ በፑሽኪን አዳራሽ ለተከታታይ ሳምንታት የቀረበውን ተውኔት በመክፈቻው ዕለት ተገኝቼ ተከታትየዋለሁ፡፡ ተውኔቱ የመናፍቃን ስውር ተንኮል ምን ያህል ስር የሰደደ እንደ ሆነና ይህም በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት ያስረዳል፡፡ ተዋንያኑም የተዋጣላቸው ነበሩ፡፡ በተውኔቱ መክፈቻ ላይ በክብር እንግድነት የተገኘው ባለቅኔና ጸሐፌ ተውኔት ደራሲ አያልነህ ሙላት፡- «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍና የሥነ ሕንፃ ባለቤት ናት፡፡ ለዚህ ሁሉ ሀብቷ የባለቤትነት መብት /Copy right/ ብትጠይቅ እኛ የምንናገርበት አንደበት አይኖረንም፡፡ … ተውኔት ወጣቱን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያቀራርባል፡፡ ይህ ተውኔት በቤተ ክርስቲያን ስም ተዘጋጅቶ ለመድረክ መብቃቱ ያኮራል፡፡ ጅምሩ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት» ብሏል፡፡ በእውነቱ እንዲህ ካሉት አስተያየቶች ብዙ መማር ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተውኔቱ በመድረክ መቅረቡ እንዲቀጥል፣ በፊልም መልክ ተዘጋጅቶ ወደ አህጉረ ስብከት ቢሠራጭ ወዲያውም ደግሞ ባለሞያዎችን እየጋበዛችሁ በተነሣው ጭብጥ ዙሪያ ብታወያዩን መልካም ነው እላለሁ፡፡

ደመላሽ አሰፋ

ስድስት ኪሎ

## ኅትመቶችን በየቋንቋው

በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጁትን የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ እንዲሁም መጻሕፍትን እየተከታተልኩ አነባለሁ፡፡ ኅትመቶቹ ከአማርኛ ቋንቋ ውጭ ወደ ብሔረሰብ ቋንቋዎች ተተርጉመው ለመሠራጨት እንዲችሉ ጥረት ይደረግ፡፡ ሁሉንም የሕዝብ ወገን በየቋንቋው ማስተማር፣ ስለ እምነቱ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ማስጨበጥ፣ መንፈሳዊ ሕይወቱም የተቃና እንዲኾን ማድረግ ሐዋርያዊነት ነውና፡፡ በርቱልን፡፡

አባ ይርጋ ኮሮ ሐጎስ

ምዕ. ትግራይ - ፀገዴ ወረዳ

## የስፖርት ማዕከል ቢኖር

ለአንድ ክርስቲያን ሦስት ነገሮች ቢኖሩት መልካም ነው፡፡ አንደኛ፡- የቀና ሃይማኖትና በጎ ምግባር፤ ሁለተኛ፡- ገቢ የሚያገኝበት ሥራ፤ ሦስተኛ፡- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማዘውተር ናቸው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎቱን ሃይማኖትን ለማጽናት ምግባርን ለማስተማር በመንፈሳዊ ጽሑፎች /በመጽሔት፣ ጋዜጣ፣ መጽሐፍ/ ጀመረ፡፡ ከዚያም ዐጸደ ሕፃናትና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሠራ፤ ዳግመኛም ለተቸገሩ ገዳማት፣ አድባራትና የአብነት ትምህርት ቤቶች የልማትና የርዳታ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እያከናወነ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ያስመ ሰግነዋል፡፡ ታድያ ከዚህ ሁሉ ጋር አካ ላዊ ጤንነታችንን፣ መንፈሳዊ ንቃታች ንን ለማጎልበት /ለመከባከብ/ የስፖርት ማዕከል ቢኖረውስ? በተለያዩ የስፖርት ውድድሮች ማኅበሩ ቢካፈልስ? አገል ግሎቱን የበለጠ አያስተዋውቀውም ትላ ላችሁ? ለማንኛውም እግዚአብሔር ጥረ ታችንን ይባርክ፡፡ አሜን፡፡

ኤልያስ ደስታ

አዲስ አበባ

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል፡፡ ሐመርን አንብቡ፤ ለሐመር ጻፉ፤ በተሳትፏችሁ ቀጥሉ፡፡

ዓባይነህ ውበቱ፣ ጥላሁን ወንዴ /ደብረ ማርቆስ/፤ ዲ.ን ተከተል ልደቱ /ኢሉ ወረዳ - አስጎሪ/፤ ጸጋዬ ዘውዴ /ወልድያ/፤ ከተማ አያሌው /አሶሳ/፤ ሽፈራው ሙሉጌታ /ኅሐ ጽዮን/፤ ምክትል ፲ አለቃ መኮንን ገብሬ /ዐድዋ/፤ ተክሊት ኪዳኑ /ደብረ ዘይት/፤ መ/ር ብርሃኑ ይመር /ደብረ ብርሃን/፤ መካሻ ገሠሠ /ጌድኦ ዞን/፤ ዲ.ን ዘርይሁን ላቀው /ኢተያ/፤ ወልደ ኢየሱስ ወልደ ጻድቅ /ወንጂ/፤ ተስፋ ጊዮርጊስ ኃይለ ማርያም /ይርጋ ሙዳ ከተማ/፤ ልየው ፈረደ /ደሴ/፤ ታምራት ደበበ /ሮቤ/፤ ብርሃነ ሥላሴ /መቐለ/፤ ባኮ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች፤ መላኩ በቀለ /አሰበ ተፈሪ/፤ ግዛው ዓምደ ማርያም /ባሌ ሮቤ/፤ ሰይፈ ገብርኤል፣ ምትኩ ግርማ፣ ወልደ መስቀል፣ ነቢዩ ተስፋዬ፣ አንተነህ እንዳሻው፣ ነጋ ስሜ፣ ጸጋዬ ሀብቴ፣ ፍሬ ሕይወት ተክሉ፡፡



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅርሶቻችን ይመለሱ ወይስ ለደኅንነታቸው ሲባል በዚያው ይቆዩ?

## «ቅርሶቻችን ባይመለሱ፣ መጀመሪያ ጠግበን መብላት አለብን»

የእኔ አቀዋም «ቅርሶቻችን ባይመለሱ» የሚል ነው። ከዚህ ይልቅ ኢትዮጵያ መጠየቅ ያለባት ሕዝቧን፦ ከረኀብ፣ ከበሽታ፣ ከጦርነት ወዘተ ስለማላቀቅ ነው። የቅርስ መመለስ አለመመለስ ጉዳይ ከድህነትና ኋላ ቀርነት ከተላቀቅን በኋላ የምናስብበት ይሆናል። ለመሆኑ እዚሁ በአገር ቤት ሳሉ ተሰርቀው የሚሸጡትን ቅርሶቻችንን አስበናቸው እናውቃለን? የሚሸጧቸው የተቸገሩ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ መጀመሪያ ጠግበን መብላት አለብን። አባቶቻችን እየተራቡ፣ እየተጠሙ፣ እየተሠው ቅርሶቻችንን የጠበቁበትን ሁኔታ ዛሬ ደግመን ለመተግበር አንችልም።

በሌላ በኩል፦

1. ውጭ ያሉት ቅርሶቻችን ምን ጊዜም የእኛው ናቸው። በእንግሊዝ ሙዚየም ከሚገኙትና ዛሬ ሀገር ውስጥ ካሉት የተሰረቁትና ለስርቆት ስጋት የተጋለጡት የትኞቹ ናቸው? በአያያዝ ችግር እየተንገላቱ ያሉትስ? «በመብረቅና በእሳት ቃጠሎ» እየተባለ የወደሙትስ?
2. በጥንቱ ጊዜ የተወሰዱቱ በቁጥራቸውና በመልካቸው ታውቀው በሙዚየም ተቀምጠዋል። በአገር ውስጥ ያሉቱስ?
3. የአክሱም ሐውልት ከሮም አደባባይ እንደ ቆመ ቢቀር ጥሩ ነበር። ለምን ብትሉኝ በቱሪስቶች ለመጎብኘት የተመቸ ነበር። የእኛ መኾኑን ማንም ሊሸርብን አይችልም። አሁን ግን ወደ አክሱም መጣ፤ ለቱሪስቶች የሚመጥን የትራንስፖርትና የአገልግሎት መሠረተ ልማት /ሆቴል፣ መንገድ፣ ተሽከርካሪ፣ ቀልጣፋ ቢሮክራሲ/ በበቂ የለም። ቱሪስቶችም በነዳያን ልመና እየ ተዋከቡ ይማረራሉ።
4. እስኪ ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ /ሴባስቶፖል/ እንነጋገር። ዛሬ ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል? ወደ መቅደላ ተራራ ለመውጣት በእግር መጓዝን ይጠይቃል። ይህን መከራ ታግሦ ለደረሰ ደግሞ ምቹ ማረፊያ ቦታ የለም። «ምነው፥ ይኼን መሣሪያ እንግሊዞች ወስደው በሙዚየማቸው ባስቀመጡት ኖሮ!!» ብዬ እመኛለሁ።
5. እኛ «ቅርሶቻችንን ስጡን» ብለን እንጠይቃለን። ኧረ ለመኾኑ «እናንተም ታቦተ ጽዮንን መልሱልን» ብለው እስራኤላውያን ቢጠይቁንስ ምን ይውጠን ይሆን?

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ቅርሶቿን ለማስመለስ ብር ከምናዋጣና ጊዜያችንን ከምንፈጅ ይልቅ ጠግበን ማደር የሚቀድም ይመስለኛል። ስለዚህ አሁን መነጋገር ያለብን የሥራ ባሕልን ስለማዳበር፣ ሰላምን ስለማስፈን፣ ከበሽታ ራስን ስለመከላከል፣ ልመናን ስለማስቀረት ነው። ቅርሶቻችሁን ውሰዱ ቢሉን እንኳን የምናስቀምጥበት በቂና ምቹ ቦታ አላዘጋጀንም። ለምሳሌ፦ ከ400 በላይ የብራና መጻሕፍት እንደ ተዘረፉብን «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትላንት ዛሬና ነገ» በሚል ርእስ በ1994 ዓ.ም በማኅበረ ቅዱሳን የተዘጋጀው መጽሔት ያስረዳል። እኒህ ሁሉ መጻሕፍት ቢመለሱ ተስማሚ መቀመጫቸው የት ነው የሚኾነው? ተመልሰው ላለመዘረፋቸውስ ዋስትናችን ምንድን ነው?

በአጠቃላይ በእጃችን ያሉትን እንጠብቅ፤ በውጭ ያሉቱ ዝርዝራቸው ተለይቶ ይታወቅ፤ በቅርስነትም ይመዝገቡ። በተረፈ የተወሰዱ ቅርሶቻችንን ወደ አገር ቤት ይመለሱ ዘንድ ጊዜው አሁን አይደለም።

*መ/ር ሙሉታ አንተነህ*
*አሰላ*

## «ለራሳችን ንብረት የማስቀመጫ ቦታ አይቸግረንም»

ኢትዮጵያውያን «የተዘረፉት ቅርሶቻችን ይመለሱ» በምንልበት ወቅት እነርሱን አደጋ ላይ የምንጥል፣ የምናስቀምጥበት ቦታ የተቸገርን እንደ ሆነ ተደርጎ መነገሩ የሚያሳዝን ነው። ምናልባት ይህ ሐሳብ ካለብን ዘርፈ ብዙ ችግር አኳያ ለቅርሶቻችን ደኅንነት ከመቆርቆር የተነሣ የመጣ ሊኾን ይችላል። ግን፥ በመጠኑ /በግዝፈቱ/ የላቀውን የአክሱምን ሐውልት ከጣልያን መንግሥት ስንረከብ የቦታ ጥያቄ ያቀረብንለት ወገን የለም። እኒህ ወገኖች ቢያንስ በዚህ ምሳሌ ስጋታቸውን ቢያስወግዱ መልካም ነው። ለራሳችን ንብረት የማስቀመጫ ቦታ አይቸግረንም። የደኅንነት ጥበቃቸውን በተመለከተም ኢትዮጵያውያን መተኪያ ከሌላት ሕይወታቸው በላይ ቅድሚያ የሚሰጡ መሆናቸው እሙን ነው። ለቅርሶቻቸው ደኅንነትም ሓላፊነቱን ይወስዳሉ። ስለሆነም ካሉበት ወደ ሀገር ቤት ቢመለሱ መልካም ነው።

*ምክትል መቶ አለቃ ገብረ*
*እግዚአብሔር*
*ደሴ-ጢጣ*
*ሰሎሞን ጌታቸው*
*42ኛ ክፍለ ጦር ሆስፒታል*
*አፋር - ዔሊዳር*

## «በየአጥቢያችን ሙዚየሞችን እንገባ»

ቅርሶቻችን ይመለሱ ዘንድ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካውያንም ምኞት ነው። ይመለሱልን እንጂ ምቹ ቦታ አለን፤ ሳይዘረፉ በፊት ቦታ ነበራቸውና። ለዚህ ደግሞ በቀላሉ ልንጎበኛቸውና ለሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት በአርአያነት የምንቆጥራቸው አጥቢያዎች በመዲናችን አዲስ አበባ አሉ። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፦

- ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መዘክር
- ታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም ሚዚየም
- መንበረ ፀሐይ /እንጦጦ/ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሚዚየም... ናቸው።

የእነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ምሳሌ በመከተል ሁላችንም የየአጥቢያችንን አብያተ ክርስቲያናት በማስተ ባበርና ዘመናዊ ሚዚየም በመገንባት ቅርሶቻችንን መጠበቅና መከባከብ እንችላለን። ቅርሶቻችን ከማንነት መገለጫቸው ባሻገር ከቱሪዝም አንጻርም የገቢ ምንጮች ናቸው።

*ወለተ ማርያም*
*ህገረ ሕይወት*

## «የእኛው ሣር ቤት ይሻላቸዋል»

ቅርሶቻችን ባዕዳን በሠሩላቸው ያሸበረቁ ቤቶች ትርጉማቸውንና ክብራቸውን አጥተው ከሚቀመጡ እኛ እንደ አቅማችን በምንሠራላቸው የሣር ቤቶች ትክክለኛ ትርጉማቸውንና ተገቢ ክብራቸውን ይዘው ቢቀመጡ በእጅጉ የተሻለ ነው። በሐመር መጽሔት 11ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት ላይ በአንድ ስኮትላንዳዊ ግለሰብ ቤት ተቀምጦ ሲኖር በለንደን ሀገር በመጻሕፍትና ቅርሳ ቅርስ መሸጫ መደብር ለሽያጭ ቀርቦ የተገኘውን የቃል ኪዳን ታቦት ዘገባ ያስታውሷል። ይህ የቃል ኪዳን ታቦት በመጨረሻ ኢትዮጵያውያን ባልሆኑ ሁለት ግለሰቦች ከፍተኛ ጥረት ወደ ሀገሩ ለመመለስ በቅቷል። ባዕዳኑ ለቅርሶቻችን የሚሰጧቸው ቦታዎች ፊዚካላዊ ሁኔታዎች ምቹዎች ቢመስሉም ለክብራቸው ግን ተገቢዎች አይደሉምና ይመለሱልን። እዚህ ባለመሆናቸው በረከታቸውም ሊቀርብን አይገባም። ለዚህም አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ እናድርግ።

ዲ.ን መስፍን በትሩ
አቤቤ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት
ኃይለ ሚካኤል
አዲስ አበባ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሰባቱ ኪዳናት

(መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው)

## ኪዳን ምንድን ነው?

.«ኪዳን»፡- የግእዝ ቃል ሲሆን «ተካየደ» ከሚለው ግስ የወጣ ነው፡፡ «ተካየደ» ማለት «ተዋዋለ፣ ተጣጣፈ፣ ቃል ኪዳን ተጋባ፤ ተማማለ፣ ነገር ተቋረጠ» ማለት እንደ ሆነ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ /1948፣ 529/ ያብራራል፡፡ ኪዳንን በቁሙ፡ - ውል፣ ቁም ነገር፣ የፍቅርና የአንድነት መሐላ፣ ሰላማዊ ሕግ፣ ኹለቱን ወገን አንድ የሚያደርግ፣ ስለ ረብና ስለ ጥቅም በተስፋ የቆመ፣ የተጣፈ፣ ቢያፈርሱት ጉዳትና ጠብ የሚያመጣ፣ ጥቅም የሚያሳጣ» /1948፣529/ የሚል ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ስለዚህ ኪዳን በጥሬ ትርጉሙ እንደ ተመለከትነው፡- «ስምምነት ባላቸው ሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል» ማለት ይሆናል፡፡ ብዙ ቁጥሩም ኪዳናት ይባላል፡፡

ሌላው ለዚህ ጽሑፍ የሚስማማው የቃሉ ፍቺ፡- ለቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጽሐፍ የተሰጠ ስያሜ መሆኑ ነው፡፡ ይህንኑ መጽሐፈ ሰዋስው ሲያስረዳ፡- «ኪዳን፡- የመጽሐፍ ስም፣ ተረፈ ወንጌል፣ ሐዋርያት ያስተማሩት ÷ ጌታ ከትንሣኤ እስከ ዕርገት ያስተማራቸው÷ እየጠየቁት የመለሰላ ቸው» ይለዋል፡፡ /መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው ÷1988÷1/፡፡ ጌታችን በሕይወተ ሥጋ ሳለ ያስተማረው ወን ጌል መባሉ፡- ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንደ ጠፋ÷ ወልደ እግዚአብሔር እንደ ነገሠ÷ ዲያብሎስ እንደ ተሻረና አዳም እንደ ዳነ ስለ ሚናገር ነው፡፡ ከሞት ተነሥቶ ያስተማረው ኪዳን መባሉ፡- «ስለምን ነው ቢሉ ደግ ነገር ነውና፡፡» ቅዱስ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተገባ ቃል ኪዳን ተፈጻሚነት ያለውና የማይለወጥ እንደ ሆነ ሲያስተምር፡- «እንግዲህ ይህ ኪዳን ከእግዚአብሔር ዘንድ የጸና ነው» በማለት ተናግሯል፡፡ ምክንያቱም የአብርሃም ልጆች ሃይማኖታቸውን ቢያጸኑ÷ ሕጉን ቢጠብቁ ምድረ ርስትን እንደ ሚያወርሳቸው እግዚአብሔርና አብርሃም የተካየዱበት (የተዋዋሉበት) በመሆኑ ነው፡፡

መጻሕፍተ ኪዳን መሠረታዊ መገኛቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከዕርገቱ በፊት ካስተማረው ትምህርት ውስጥ ነው፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎችን እየጠየቁት ለጥያቄያቸው መልስ እየመለሰላቸው አስተምሯቸዋል፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ፡- «ቴዎፍሎስ ሆይ÷ ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ÷ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ፤ ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው÷ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው» /የሐዋ.1÷1-3/ ሲል መጻፉ ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ማስተማሩን ያረጋግጥልናል፡፡

ምንም እንኳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *ከሞት* ከተነሣ በኋላ ቢያስተምርም ትምህርቱ እንደ ወትሮው ለመላው ሕዝብ አልነበረም፡፡ ለደቀ መዛሙርቱ በኅብረት÷ በተናጠል ለአንዱም ለሁለቱም እየተገለጸ ነበር፡፡ ዮሐ.20÷19፣ ሉቃ.24÷16፡፡ በጉባኤ እየታየ ደቀ መዛሙርቱን ያስተማራቸው አራት ጊዜያት መሆኑ ይታወቃል፡፡ እነዚህም የትንሣኤ፣ የአግብዖተ ግብር /የዳግም ትንሣኤ/፣ የጥብርያዶስና የዕርገት ትምህርቶቹ ናቸው፡፡

**«መተርጉማነ ሐዲስ ጌታ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ያስተማረው ወንጌል÷ ከትንሣኤው በኋላ ያስተማረው ኪዳን እንደ ሚባል ያስረዳሉ፡፡»**

መሪያው ከምክንያት በላይ በሆ ነው ፈቃዱ ወንጌልን ለሰው ልጅ እንደ ሚጠቅም÷ ወዶ ፈቅዶ በልበ ሐዋርያትና በሚያምኑት ኅሊና እንደ ሣለ መጻሕፍተ ኪዳንንም ሰዎች ተምረው እንዲጸድቁ በልበ ሐዋርያት ጽፎታል፡፡ ሁለተኛው «በመዋዕለ ሥጋዌው የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቁት እንደ ነበረ ሁሉ ይህንም ጠይቀውት አስተምሯቸዋል» የሚል ነው፡፡

በተለይም ከሙታን ከተነሣ በኋላ ትንሣኤው ቢያስደስታቸው ከእነርሱ ተለይቶ በማረጉ አዝነው ነበር፡፡ ምክንያቱም ስኳን እግዚአብሔርን የሚያህል ወዳጅ፣ አባትና አምላክ ቀርቶ ጓደኛም ሲለይ ያስተክዛል፡፡ እነርሱም ነገረ ዕርገቱን ሲነግራቸው አዝነው ተክዘው፡- «አንተ ዐርጋለሁ ካልክ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በምን ትተዳደር? ብለው ጠይቀው ቤተ ክርስቲያን ትተዳደርበት ዘንድ እየጠየቁት እየመለሰላቸው ጽፈውታል፡፡» አንድም ቁጥራቸው ከሠላሳ ስድስት ቅዱሳት አንስት የሚሆኑ ቤርዜሊ÷ ቤርዜላ÷ ሜልቲዳ የሚባሉ ሦስት ሴቶች ጠይቀውት አስተምሯቸዋል፡፡

### መቼ ተጻፉ?

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ/ 1948÷530/ መጻሕፍተ ኪዳን ከዕርገት በኋላ ከወንጌል በፊት እንደ ተጻፉ ያስነብባሉ፡፡ ይኸውም ከ34 እስከ 40 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ውስጥ እንደ ተጻፈ መገመት አያዳግትም፡፡ አርባዕቱ ወንጌል ከ60-90 ዓመተ ምሕረት ድረስ ተጽፈዋል፡፡ /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ 1972÷39 እና 221/፡፡ ከዚህ አንጻር ሰባቱ ኪዳናት አርባዕቱን ወንጌላት ቀድመው ለአገልገሎት ውለዋል፡፡

### ምክንያተ ጽሕፈት

«የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብን ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል» ተብሎ እንደ ተጻፈ የመጻሕፍተ ኪዳንም ምክንያተ ጽሕፈታቸው ይኸው ነው፡፡ ይሁንና ለግንዛቤ እንዲረዳን ምክንያተ ጽሕፈታቸውን በሁለት ከፍለን ለመመልከት እንችላለን፡፡ የመጀ

### ማን ጻፋቸው?

ቅዱሳት መጻሕፍት በፍኖተ አሚን ለሚጓዙ ሰዎች የሕይወት መመሪያ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር በመረጣቸው ቅዱሳን አባቶች የተጻፉ ናቸው፡፡ መጻሕፍተ ኪዳንም በነዚሁ በተመረጡ ቅዱሳን አባቶች (ቅዱስ ጴጥሮስ፣ቅዱስ ዮሐንስ፣ቅዱስ ማቴዎስ) ተጽፈዋል፡፡ «መጽሐፈ ኪዳን ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ጸሐፍዎ ለዝ ኪዳን ዮሐንስ ወጴጥሮስ ወማቴዎስ እንዘ ያጽሕፎሙ እግዚእነ፤ ወፈነው በአርአያዝ ግጽው እምኢየሩሳሌም፤ ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የኪዳን መጽሐፍ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስና ማቴዎስ ጌታችን እየነገራቸው ጻፉት፡፡ በዚህ ዓይነት መግለጫ ወደ ኢየሩሳሌም ላኩት፡፡ /ክፍል 1÷ ኪ.ወ.ክ /1948÷530/፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ይቀጥላል



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

*/ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ
የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
1932-1982 ዓ.ም./*



«ይህ ነው፤ ሰው ሆኖ የተገለጠ÷በመንፈስ የተረዳ÷ ለመላእክት የታየ ÷ለአሕዛብ ያስተማሩት፣ በዓለም የታመነ ÷በምስጋና ያረገ።» /1ጢ.ሞ.3÷16/።

# ምድረ ፍልስጥኤም

ክርስትና ሲወለድ ምድረ ፍልስጥኤም እንደ ሌሎቹ የመካከለኛው ምሥራቅ፣ የሰሜን አፍሪካና የታናሽ እስያ አገሮች በሮም ቅኝ ግዛት ሥር ነበረች። በውስጧ የነበሩ ሕዝቦችም የተከፋፈለ የሃይማኖትና የፖለቲካ ቡድን ነበራቸው። ከነዚህም ዋናዎቹ የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን ቡድኖች ነበሩ። የሰዱቃውያን ቡድን የሀብታሞችና የካህናት ቡድን ነው። ይህ ቡድን ለባህል፣ ለሥነ ሥርዓትና ለሃይማኖት ግድ የሌለው፣ ከቅኝ ገዥዎች ጋር ተስማምቶ በእነርሱ ሥልጣኔ መጠቀምን ብቻ የሚፈልግ ቡድን ነበር። ከሃይማኖት መጻሕፍትም የሙሴን ሕግ ብቻ እንጂ የነቢያትን ትንቢትና ሌሎችንም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አይቀበሉም ነበር። የሙታንን ትንሣኤና የመሲሕንም መምጣት አያምኑም ነበር፤ ሌላው ቡድን የፈሪሳውያን ቡድን ነው። ፈሪሳዊ፦ «ፓራሽ» ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የወጣ ነው፤ ትርጉሙም «የተለየ» ማለት ነው።

እነዚህ ፈሪሳውያን ምንም የቅኝ አገዛዝ ቀንበር መላልሶ ቢያደቃቸውም «ባህልና ልምዳችን አይነካ» በሃይማኖትም «የሙሴን ሕግና የነቢያትን መጻሕፍት የምንጠብቅ እኛ ብቻ ነን» ባዮች ነበሩ። ስለዚህ ከአይሁድ ዘር ውጭ ከሆነ ከማንኛውም ጎሳና ዘር ጋር በባህልና በሥልጣኔ መቀራረቡን እንደ መርከስና ሕግን እንደ መተላለፍ ይቈጥሩት ነበር። የመሲሕንም መምጣት ነቅተውና ተግተው ይጠባበቁ ነበር። ለዚህም ዋናው ምክንያታቸው ሀገራቸው ፍልስጥኤምን ከሮም ግዛት ነጻ ለማውጣት የቆየ ጉጉት ስላላቸው ነው። እንደ ነሱ አስተሳሰብ መሲሕ ሲመጣ የጦር ኃይል አቋቁሞ÷ ራሱ የጦር መሪ በመሆን የሮማን የቅኝ ግዛት ቀንበር አውልቆ ጥሎ የዳዊትን ቤተ መንግሥት የሚያድስ መሲሕ ይጠባበቁ ነበር ማለት ነው። ምንም እንኳ «ከትንሣኤ በኋላ ሥጋዊ ኑሮ አለ» ብለው ቢያምኑም ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ያውቁ ነበር። ፈሪሳውያን በዕለታዊ ኑሮዋቸው ብዙ ሀብት የሌላቸውና በዕውቀትም መጠነኞች ነበሩ። «መሲሕ መጥቶ÷ የጦር ኃይል አቋቁሞ÷ በጦር ኃይል ፍልስጥኤምን ነጻ ያወጣል» የሚለውን የፈሪሳውያን እምነትና ተስፋ በመቃወም ሌላ ንዑስ ቡድን ከፈሪሳውያን ተከፍለው በሙት ባሕር አካባቢ ገዳም መሥርተው ይኖሩ ነበር። የእነርሱም ዓላማቸው እንደ ፈሪሳውያን መሲሕን መጠባበቅ ነው።

ኤሴይ በመባል የታወቁት እነዚሁ ክፍሎች ከፈሪሳውያን የሚለዩት ፈሪሳውያን፦ «በጦር ኃይል ነጻ እንወጣለን» ሲሉ ኤሴይ የሚባሉት ደግሞ «በተኣምራት÷ በእግዚአብሔር ኃይል ፍልስጥኤም ነጻ ትወጣለች» ብለው ያምኑ ነበር። በቤተ ልሔም በስተ ደቡብ ልዩ ስሙ ኩምራን በሚባል ቦታ የሚኖሩት እነዚህ ሰዎች መጻሕፍትን በመጻፍ÷ ጸሎትን በማድረስ ብዙ ጊዜ ቆይተዋል። ኤሴዎችና ፈሪሳውያን ባንድ አንድ አስተሳሰብ ቢለያዩም መሲሕ መምጣቱንና የተወሰኑ ምርጥ ገኅዎችን ነጻ እንደ ሚያወጣ÷ ዓለም አቀፋዊ መሲሐዊ መንግሥት እንደ ሚያቋቁምና እነርሱም የመንግሥቱ ባለሟሎች እንደ ሚሆኑ ሁለቱም ቡድኖች ያምኑ ነበር። በእስራኤል የሃይማኖትና የነገድ ቤተሰብ ውስጥ ይህ ልዩነት ተፈጥሮ መከራቸውን ሲያዩ በፍልስጥኤምና ከፍልስጥኤም ውጭ የነበረው የሮም መንግሥት ፖለቲካ ደግሞ ከቅኝ ግዛቱ ስፋት የተነሣ ያነገንግ ነበር። የነጻ አውጭ ግንባሮች በየጊዜው የሚጥሉትን አደጋና ግጭት ለመቈጣጠር እንዲያመች በየጊዜው የሕዝብ ቈጠራ እንዲደረግ ታዝዞ ነበር። /ሉቃ 2÷1/። ሕዝቡ በጠቅላላ ገበሬውም ሆነ ነጋዴው የመንግሥትም ባለ ሥልጣን በሚሠራው ሥራ ሁሉ ባለ ጸጋ ስለ ነበር የሮም ግዛት ተወዳዳሪ የሌላት ታላቅ አገር ነበረች። ታድያ ምን ያደርጋል እነዚህ ሁሉ ሀብታት ለሕዝቡ ደስታንና ውስጣዊ ዕረፍትን ሊያስገኙለት አልቻሉም። ሁልጊዜ በአካባቢው ከሚሰማው የሽብርና የሁከት ድምፅ የተነሣ <ባልታሰበ ቀን እንመሰሳለን> የሚል ቀቢጸ ተስፋ ገዝቶት ነበር፤ ያመልኳቸው ከነበሩ ጣዖታትም አንዳችም የተስፋ ድምፅ አልነበረም። በቀቢጸ ተስፋ ባሕር ውስጥ ገብቶ የሚማቅቀውና መውጣትም የተሳነው አማኞቻቸውን ሊያረጋጉት አልቻሉም።

ቅዱስ ዳዊት እንደ ተናገረው፦ «ዐይን እያላቸው የማያዩ፣ ጆሮ እያላቸው የማይሰሙ፣እጅ እያላቸው የማይዳስሱ፣ አፍ እያላቸው የማይናገሩ፣ እግር እያላቸው የማይሄዱ» /መዝ.113/ ግኡዛን ናቸውና። ከዚህም የተነሣ ማለት የሚያመልኳቸው ጣዖታት ሊያረጋጓቸውና ሊረዷቸው ስላልቻሉ ሕዝቡ «አማልክቶቻችን የዋሃንና ግድ የለሾች ናቸው» እያለ በጣዖታቱ ይዘብት ነበር። የሰው ልጅ ሥልጣኔም በክፋትና በደግነት መካከል ያለውን ልዩነት ለማመልከት አልቻለም። በዚህ አኳኋን ስለ ሰው ልጅ የወደፊት ዕድል ምንም የተስፋ ጭላንጭል አልነበረም።

ሰው በተፈጥሮው <ከወዴት መጣሁ? ወዴትስ ነው የምሄደው?> ብሎ ራሱን በራሱ የመጠየቅና የመመርመር ስጦታ ያለው ባለ አእምሮ ፍጡር ስለሆነ እነዚህ ጥያቄዎች ሁልጊዜ በፊቱ ይደ ቀኑበታል። ነገር ግን ለነዚህ ጥያቄዎች ከውስጥ ከራሱም ሆነ ከውጭ ከሌላ አጥጋቢ መልስ ስላላገኘ ከላይ እንደ ገለጥነው የደስታን ኑሮ ጣዕሙንና ምሥጢሩን ሊያውቀው አልቻለም። በሮም ቅኝ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ በዚህ ሁኔታ በቀቢጸ ተስፋ ስለ ተሞሉ እነርሱም ሆኑ ሥርዓተ ማኅበራቸው ጠባቂ እንደ ሌለው መንጋ ወይም ቀዛፊ /ሊቀ ሐመር/ እንደ ሌለው መርከብ አቅጣጫው የማይታወቅ ሆነ። ሕዝቡን ለማስደሰት በሮም የቴአትር ሰገነት /አሬና/ ላይ የሚቀርበው የጨዋታ ዓይነትም እንኳ ደም መፋሰስና መደባደብ ስለነበር በጨለማ ላይ የዛፍና የገደል ጥላ ሲጨመር ጨለማው እንደሚጸና ሰቀቀኑን አባብሶት ነበር። ሀብታሙ በሀብቱ ደስታን ለመሸመት አልሆንለት ብሎ ሲጨነቅ ሲጠበብ በዝቅተኛው ሕዝብ ዘንድ ደግሞ ዕጓለ ማውታንና መበለታትን ወዴት ወደቃችሁ የሚላቸው አልነበረም።


በሽተኞችና ረኀብተኞች ጥርኝ ጥሬ፣ ኩባያ ውኃ የሚላቸው አጥተው በረኀብ ይተላለቁ ነበር። ሲሞቱም ያውሬ ራት ይሆናታል እንጂ የሚቀብራቸው አልነበረም። በአጠቃላይ «ፍርድ ጎደለ÷ ድኻ ተበደለ» የሚል ታዛቢ ተመልካች የሌለበት የአስረሽ ምችውና የብላ ተባላ ዘመን ነበር። «የሰው አውሬው ሰው ነው» /homo homini lupusest/ የሚባለው የሮማውያን ተረት የተፈጸመው በዚህ ጊዜ ነበር። እነ አውግስጦስ ቄሣር «የሰላም እመቤት» ብለው የሰየሟት ወይም ራሷን «ሰላም» ብለው የጠሯት ፓክስ ሮማና /Pax Romana/ ፍቅርና ሰላምን አላስገኘችላቸውም። ይህ ሁሉ የሁከ





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org



# በገና ዋዜማ

ትና የሽብር ጥላ ባንዣበበበት ወራት፣ የቤተ ክርስቲያን መሠረት፥ የአሕዛብ ብርሃን፥ የእስራኤል ዘነፍስ ክብር መድኀን ዓለም በሮም ቅኝ ግዛት ሥር በነበረች በፍልስጥኤም ልዩ ስሟ ቤተ ልሔም በምትባል በይሁዳ ክፍል /በደቡብ/ ተወለደ:: ማቴ.2÷1:: ሉቃ.2÷11::

በተወለደም ጊዜ ትንቢት ያልተነገረላቸው፥ ሱባኤ ያልተቈጠረላቸው፥ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰብአ ሰገል መድኀን መወለዱን ዐውቀው ከምድረ አሕዛብ እጅ መንሻውን:- ወርቅ ዕጣን ከርቤ ይዘውለት መጡ፥ ገበሩለትም:: ማቴ.2÷11:: የመወለዱም ዓላማ የሰውን ዘር ከጠፋበት ለመፈለግ፥ ወደ ፊተኛው ክብሩ ለመመለስ፥ ስለ ጽድቅ ለማስተማርና ለመመስከር ነው:: ማቴ.1÷21፤ ሉቃ.1÷31፤ ዮሐ.18÷37:: በመድኀን መወለድ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ መላእክትም ተደስተዋል:: «በሰማይ ለእግዚብሔር ምስጋና ይገባዋል፣ በምድርም ሰላም» እያሉ ዘምረዋል:: ሉቃ.2÷13-14:: ይህ ሁሉ ባንድ ወገን የነበረው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ሲሆን በሌላ በኩል የነበረው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ደግሞ የሚያሳዝን ነበር:: ለምሳሌ:- «ሥርዓተ ኦሪትን ትንቢተ ነቢያትን በሚገባ እንከታተላለን» ይሉ የነበሩ ፈሪሳውያን ክንዱ የሚያደቅ ግርማው የሚያንቀጠቅጥ ሮማውያንን አባሮ አገራቸው ፍልስጥኤምን ነጻ የሚያወጣ ኃይለኛ መሲሕ ሲጠባበቁ ይኖሩ እንደ ነበር ተገልጧል:: የኛ መሲሕ «ክርስቶስ» ግን እነርሱ እንደ ጠበቁት ሆኖ አልመጣም:: እንደውም ከላይ እንደ ተገለጸው ዘመኑ የሁከትና የሽብር ዘመን ስለ ነበር አውግስጦስ ቄሣር ለጸጥታ አጠባበቅ እንዲያመች በየጊዜው ዜጎቹን ያስቈጥር ነበርና ድንግል ማርያም ለመመዝገብ፥ ለመቈጠር አገር ጥላ ስንቋን ቋጥራ በሄደችበት ቦታ መጠጊያ እንኳ በሌለበት በተጨናነቀ አካባቢ ከብቶች በሚያድሩበት ቦታ መሲሕ ተወለደ:: ሉቃ.2÷1-7:: በዚያም የሀብታሞች የነገሥታት ልጆች ሲወለዱ በሚነጠፍላቸው ወርቀ ዘቦ ግምጃ ሳይሆን ሉቃስ እንደ ነገረን እናቱ በጨርቅ ጠቀለለችው:: ሉቃ.2÷12:: ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ «በለሰን በሚባል ቅጠል ሸፈነችው» ይላል:: /ድጓ፥ የልደት ዋዜማ ተመልከት/:: በዚህ ምክንያት ማለት እነርሱ እንዳሰቡትና እንደ ተጠባበቁት ሁኖ ስላላገኙት ፈሪሳውያንም ሆኑ ሰዱቃውያን መሲሕነቱን አልተቀበሉትም:: ....

የክርስቶስ መወለድና ትምህርቱም ያላስደሰታቸው የቤተ እስራኤል ተመጻዳቂዎች ብቻ አልነበሩም:: የሮማ መንግሥትም በበኩሉ ክርስቶስን በጥላቻ ዐይን ይመለከተው ነበር:: የሮማ ቄሣር ወዳጅ በመሆኑ በገሊላ የነገሠው ሄሮድስ መሲሕ «ክርስቶስ» በቤተ ልሔም መወለዱን ከሰብአ ሰገል እንደ ሰማ የራሱንና መላዋንም የቄሣር ግዛት የሚቀናቀን ንጉሥ የተወለደ መስሎት ደነገጠ:: የመሲሕ መወለድ ስላስደነገጠው ሕፃኑን መሲሕ ለመግደል ሙከራ አደረገ፣ ነገር ግን ሕፃኑ መሲሕ የነቢያትን ትንቢት ለመፈጸም ከእናቱ ጋር ወደ ግብፅ ተሰደደ:: ሆሴዕ 11÷1፤ ማቴ.2÷15:: የሄሮድስ ሰይፍ በአንገቱ ላይ አልወደቀችም::

ነገር ግን በሄሮድስ ተንኰል ብዙ የገሊላ ሕፃናት በሰይፍ አለቁ፣ ደማቸውም እንደ ውኃ ፈሰሰ:: ማቴ.2÷16:: የብዙ እናቶች እንባ በግፍ ፈሰሰ:: ኋላም መሲሕ በማስተማር ጉዞው እንደ ፈሪሳውያንና እንደ ሰዱቃውያን የሄሮድስን ባለሥልጣኖችና ራሱንም ሄሮድስን በግብዝነቱ በይፋ ስለሚገሥጸው /ሉቃ.13÷31 32÷2/ «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» እንደ ሚባለው በክርስቶስ ላይ ለማደም አመች ሆነ:: ሉቃ.21÷11:: ጌታ ግን የሮማ ቅኝ ገዥዎችና የቤተ እስራኤል የሃይማኖት ሰዎች መሲሕነቱን ባያውቁለትም ለበቀል ሳይሆን ለምሕረት፥ ለማዳን የመጣ እውነተኛ መሲሕ እንደ መሆኑ መጠን በነቢያት ስለሱ የተነገረውንም ለመፈጸም ድውያነ ሥጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን በትምህርት እየፈወሰ የማስተማር ሥራውን ቀጠለ:: ማቴ.8÷16-17:: ኢሳ.13÷4:: የቃሉን ትምህርት ሰምተው፥ የእጁን ተአምራት አይተው የአመኑበትን የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ ለመሆን አበቃቸው:: ዮሐ. 1÷12:: እነርሱ ግን ጥላቻቸውን ወደ ግቡ ለማድረስ የተነሡና በሰይጣን የሚገፋፉ ስለሆኑ የእርሱ ትሕትናና ፍቅር ቅንዓታቸውን አባባሰው እንጂ አልቀነሰውም::

ስለዚህም በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን ከሳሽነት፥ በሮማውያን ዳኝነት ክስ ተመሠረተበት:: ክሱም ሃይማኖትንና ፖለቲካን የሚመለከቱ ጣምራ ነገሮችን የያዘ ነበር:: ከነዚህም አንደኛው «በሃይማኖት የሙሴን ሕግ ይሽራል» የሚል ነበር፣ የሮማ መንግሥት «የዜጎቹን እኩልነት ያከብራል» እንዲባል በቅኝ ግዛት ውስጥ ለሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ የሃይማኖትና የባህል ነጻነት ሰጥቷቸው ነበር፣ አንዱ የሌላውን ሃይማኖት ቢነቅፍና ቢያዋርድ ወይም ከዚያው ከአንዱ ሃይማኖት ውስጥ አንዱ አዲስ ሐሳብ ቢጨምር ወይም ቢቀንስ ራሳቸው እንዲቀጡት፣ ቅጣቱ በሕይወት ላይ የሆነ እንደ ሆነ ግን ወደ መንግሥት ባለ ሥልጣን አቅርበው እንዲያስፈርዱበት ሕግ ተሠርቶ ነበር:: ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም በክርስቶስ ላይ ክስ የመሠረቱበት «ይህ መብታችን ተነክቷል፣ በቀላል ቅጣት የሚታለፍ ስላልሆነ በሞት ይቀጣልን» ብለው ነው:: «በፖለቲካ» መንፈስ የተመሠረተበት ሁለተኛው ክስ ደግሞ:- «እኛ ያለ ቄሣር ንጉሥ የለንም፣ እርሱ ግን ንጉሡ አይሁድ ነኝ እያለ ያስተምራል፣ ሕዝቡ ለቄሣር እንዳይገብር ያሳድማል::» /ሉቃ. 23÷1/ የሚል ነበር:: እንዲህ ማለታቸው በእውነት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ለሮማ መንግሥት አስበው አይደለም::

ይልቁንም የሮማ ባለ ሥልጣኖች ነገሩን ይዋል ይደር ሳይሉ እንዲያፋጥኑትና ጉዳዩ ሃይማኖትን ብቻ ሳይሆን የሮማንም የአገዛዝ አውታር የሚነቀንቅ ስለሆነ መንግሥት ለራሱም ጭምር ሲል ባስቸኳይ ርምጃ እንዲወስድ ለዘዴ ነው እንጂ:: እነርሱ ሰው ሰውኛውን ይህን ያህል ደከሙ እንጂ መሲሕ እንደ ሆነ «በሃይማኖት የሙሴን ሕግ ይሽራል» የሚለው ክስ ሳይመሠረትበት በፊት «የሙሴን ሕግ ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» እያለ ሲያስተምር እንደ ነበር በጆሯቸው ሰምተዋል:: ማቴ.6÷17:: በማቴዎስ 19÷11-22:- «እድን ዘንድ ምን ላድርግ» ብሎ ለጠየቀው አሪታዊ ባለጸጋ እንኳ የሙሴን ትእዛዛት እንዲጠብቅ አዘዘው:: ፍጹም እንዲሆን ቢፈልግ፥ ርግጥ በትሩፋት ላይ ትሩፋት ለመጨመር ቢፈልግ ሀብቱን ለነዳያን ሰጥቶ እሱን ቢከተል የሚሻለው መሆኑን አልሰወረውም:: እነርሱ የሚጠቅሱትን ሙሴም ስለ ርሱ የጻፈ፥ ስለ እርሱ የተነበየ መሆኑን ነግሯቸዋል:: ዮሐ.5÷36-37:: በፖለቲካም «ለቄሣር ግብር አትስጡ ብሎ ሕዝቡን ያሳምጻል» ተብሎ ከመከሰሱ በፊት «ለቄሣር ግብር መስጠት ይገባል ወይስ አይገባም?» ብለው በተንኰል ቢጠይቁት «የመንግሥታችሁን ለመንግሥታችሁ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ::» ብሏቸዋል:: ማቴ.22÷15-22፤ 17÷24-27::

ምንጭ:- ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥ 1978 ዓ.ም፥ ገጽ 20-26::





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org



የቅዳሴ አገልግሎት- በኦስትርያ ቪየና የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን

# ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ

/ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን አገዘ/

ባለፈው ትምህርታችን ኅብስቱና ወይኑ ከቤተ ልሔም ጀምሮ እስከ መንበረ ክብሩ ድረስ እንዴት እንደ ሚከናወን ከምሳሌውና ከምሥጢሩ ጋር ተመልክተናል፡፡ የሚቀጥለው ሥርዓት ደግሞ እንደ ሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሥርዓተ ጸሎት፡- «አቤቱ÷ የባሕርይ አምላክ የምትሆን ጌታችን ክርስቶስ የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና ወደ ሰርግ ቤት ተጠርተህ የሄድህ÷ ውኃውን ለውጠህ ጠጅ እንዳደረግህላቸው ይህን ወይን ለውጠህ ያንተን ደም አድርገው፡፡» በማለት ሠራኢው ካህን በኅብስቱና በወይኑ ላይ ይጸልያል /ይባርካል/፡፡

የጸሎተ ቅዳሴው ዋና ዓላማም ኅብስቱን ለውጦ ሥጋ መለኮት፣ ወይኑን ለውጦ ደመ መለኮት ማድረግና ለምእመናን ማቀበል ስለሆነ የተአምር መጀመሪያ የሆነውን የቃናን ዕለትና የተደረገውን ተአምር እያሳሰበ ይጸልያል፡፡ ምክንያቱም ኅብስቱ ወደ ሥጋ መለኮት፣ ወይኑ ወደ ደመ መለኮት የሚለወጠው በካህኑ ጸሎትና በፈቃደ እግዚአብሔር ነው፡፡ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ የሐዲስ ኪዳንን መሥዋዕት በራሱ ሥጋና ደም በመሠረተበት በምሴተ ኀሙስ ኅብስቱንና ወይኑን በጸሎትና በቡራኬ አክብሮ ለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደመ ወልደ እግዚአብሔር አድርጎ ለሐዋርያት የማቀበሉ ታላቅ ምሳሌነት ለዚሁ ለካህናቱ ሥርዓት መሆኑን መታወቅ አለበት፡፡

«ሲበሉም ኢየሱስ ኅብስቱን አንሥቶ ባረከ፣ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፡፡ ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖ ሰጣቸው፤ እንዲህም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ...፡፡» ማቴ.26÷26፡፡ ካህኑም በዚህ ሥርዓት መሠረት «ለውጠው፤ አክብረው» እያለ አሰምቶ ይጸልያል፡፡

እጁንም በትእምርተ መስቀል አመሳቅሎ «ሁሉን የሚገዛ፣ ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር... ምስጉን ነው» እያለ «ኅብስቱንና ወይኑን በእግዚአብሔር ስም ይባርካል፡፡ በጊዜ ቅዳሴ የሚከናወኑ አርባ ሁለት የአፍአና የውስጥ ቡራኬያት አሉ፡፡ በዚህ የቡራኬ ሥርዓት መሠረት ቅዳሴው እስከ ሚያልቅ ድረስ ሃያ አንዱ የውስጥ ቡራኬያት በእጅ ብቻ ሲከናወኑ ሃያ አንዱ ቡራኬያት ደግሞ በመስቀል ከመቅደሱ ወደ ውጭ /አፍአ/ የሚደረጉ ቡራኬያት ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሠራኢው ካህን በአጠገቡ የቆሙ አባቶችንና ወንድሞችን የጸሎት ተራድኦ ይጠይቃል፡፡ «ዳግመኛም ወንድሞቼና አባቶቼ ከቀሣፊ መልአክ እንዲሰውረኝ፣ እንደ በቃ፣ መሥዋዕቴን እንዲለውጥ ልኝ ከቀሣፊ መልአክ ሰውረው፣ አብ ቃው፣ መሥዋዕቱን ለውጥለት ብላችሁ ጸልዩልኝ» በማለት ያሳስባል፡፡ በዕድሜ በመዓርግ የሚበልጡትን÷ አበው /አባቶቼ/፣ የማይበልጡትን ደግሞ÷ አኃው /ወንድሞቼ/ በማለት መንፈሳዊው አገልግሎቱ ይከናወንለት ዘንድ በጸሎታቸው እንዲያግዙት ርዳታ ይጠይቃል፡፡ በእምነትና በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰሉ አባቶች ብቻቸውን የሚሠሩት ሥራ ፍጻሜ እንደ ሌለው ስለሚረዱ የአባቶቻቸውን፣ የወንድሞቻቸውን የጸሎት አጋዥነት በጣም ይፈልጉታል፡፡ ለዚህም ታላቅ አብነት የሚሆነን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ «ወንድሞች ሆይ÷ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ... በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ፡፡» /ሮሜ.15÷30/ እንዲል፡፡

ተራዳኢው ካህንም ሠራኢው ካህን ላቀረበለት የጸሎት ተራድኦ ጥያቄ እንዲህ በማለት ይመልሳል፡- «እግዚአብሔር ይስማዕከ ኵሎ ዘሰአልከ ወይ ትወከፍ መሥዋዕተከ ወቍርባነከ ከመ ሙሥዋዕተ መልከ ጼዴቅ ወአሮን ወዘካርያስ ካህናተ ቤተ ክርስቲያኑ ለበኵር፣ የመልከ ጼዴቅን፣ የአሮንን፣ የዘካርያስን መሥዋዕት እንደ ተቀበለ /እንደነዚህ መሥዋዕት አድርጎ/ መሥዋዕትህን ጸሎትህን ይቀበልልህ» በማለት የጸሎት ተራዳኢነቱን ይገልጣል፡፡

ከላይ ስማቸው የተገለጠውን አበው÷ ካህናተ ቤተ ክርስቲያን አላቸው፡፡ ምክንያቱም መልከ ጼዴቅ በኅብስትና በወይን÷ አሮንና ዘካርያስ በዕጣን ያስታኩቱበት የነበረበት ቅዱስ መካን /ቦታ/ የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነችና ነው፡፡

በኵር የተባለም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በኵር የተባለበት ምክንያት በተለያዩ መጻሕፍት የተገለጠ ስለሆነ በዚህ ላይ ብዙ ማለት አስፈላጊ አይደለም፡፡ እዚህ ምንባብ ላይ በኵር መባሉ ግን በቀደሙት ካህናት ላይ በረድኤት አድሮ ዛሬም በሥጋ ወደሙ ይቅር ይላልና ነው፡፡

ሠራኢው ካህን «ጸልዩልኝ» ብሎ በጠየቀው መሠረት እዚህ ከተራዳኢው ካህን በተጨማሪ ሁሉም አቡነ ዘበሰማያትን ይደግማሉ፡፡ በጸሎት መተባበር ልማደ አበው÷ ልማደ ክርስትና ነው፡፡ «እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡፡» ማቴ.6÷9፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሠራኢው ካህን እጁን አመሳቅሎ ከተራዳኢው ካህን እጅ ጋር አገናኝቶ « ተዘከረኒ አ አቡየ ቀሲስ በጸሎትከ ቅድስት፤ አባቴ÷ ክብርት በምትሆን በአንተ ጸሎት አስበኝ» ይላል፡፡

ካህኑ እጁን ማመሳቀሉ፡- «በእምነቴ ጽንዓት የተነሣ መከራ መቀበል አለብኝ» ሲል ነው፡፡ ከተራዳኢው ካህን እጅ ጋር እጁን ማገናኘቱ በሃይማኖት



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

በምግባር አንድ መሆናቸውን ለማጠየቅ ነው።

ተራዳኢው ካህንም ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው ሁሉ ለተጠየቀው የጸሎት ተራድኦ ጥያቄ እንዲህ በማለት የጸሎት መልስ ይሰጣል። እግዚአብሔር ይዕቀባ ለክህነትከ ወይትወከፍ መሥዋዕተከ ወቁርባነከ በብሩህ ገጽ፤ ከቀሣፊ መልአክ ይሰውርህ፤ ከሾመ አይሻርህ፤ መሥዋዕትህን ÷ጸሎትህን በባለሟልነት ይቀበልልህ» በማለት ይጸልይለታል። ተራዳኢው ካህን በጸሎቱ ላይ ሁለቱን ታላላቅ ምሥጢራት እያነሣ «ክህነትህን ይጠብቅልህ፤ መሥዋዕትህን ቍርባንህን ይቀበልልህ» በማለት የሁለቱም ምሥጢራት ሰጭና ተቀባይ እግዚአብሔር መሆኑን እያመለከተ ይጸልያል። ምክንያቱም «እውነት እላችኋለሁ÷ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ተብሎ በተነገረው መሠረት ከምድር እስከ ሰማይ የማሰርና የመፍታት ኃይል ያለው የካህናት ሥልጣን በፈቃደ እግዚአብሔር የሚጠበቅ ታላቅ ሀብት ስለሆነ «ክህነትህን ይጠብቅልህ» እያለ በጸሎት ያስበዋል።

ከእግዚአብሔር የሚገኝ መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ሀብት ሁሉ የጸጋ ነው። የባሕርይ ያልሆነ ሁሉ በጸሎትና በጥንቃቄ ካልተያዘ ይወሰዳል። አስተማሪውና ተማሪው፣ ተጋቢውና ጋብቻው፣ አስተዳዳሪውና ተዳዳሪው የተሰጣቸውን ጸጋ ለመጠበቅ በጸሎት ካልተጉና ለአባቶ ቻቸው «ጸልዩልን» የሚል ተማኅፅኖ ካላቀረቡ አንድ ቀን አጥተ ውት ባዶ ይቀራሉ። «ክብርት በምትሆን በአንተ ጸሎት አስበኝ» የሚለው የሠራኢው ካህን የጸሎት ተራድኦ ጥያቄ መቅረቡ ለሚከተለው ምክንያት ነው።

አንደኛ፦ የትሕትና አነጋገር ነው። ቅዱሳን ከራሳቸው ክብር ይልቅ የወንድሞቻቸው ክብር ቢገለጥ ይወዳሉና። ለዚህም «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና» /1ቆሮ. 15÷9/ የሚለው የሐዋርያው አነጋገር ምስክር ነው።

**«ከእግዚአብሔር የሚገኝ መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ሀብት ሁሉ የጸጋ ነው። የባሕርይ ያልሆነ ሁሉ በጸሎትና በጥንቃቄ ካልተያዘ ይወሰዳል። አስተማሪውና ተማሪው፣ ተጋቢውና ጋብቻው፣ አስተዳዳሪውና ተዳዳሪው የተሰጣቸውን ጸጋ ለመጠበቅ በጸሎት ካልተጉና ለአባቶቻቸው «ጸልዩልን» የሚል ተማኅፅኖ ካላቀረቡ አንድ ቀን አጥተውት ባዶ ይቀራሉ።»**

ሁለተኛ፦ የአንዱ ክብር ከሌላው ክብር እንደ ሚበልጥ ለማጠየቅ። «በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያልና» እንዳለ መጽሐፍ። 1ቆሮ.15÷41። ከዚህም በተጨማሪ የቅዱሳን ጸሎት በሁሉም ቦታ ለሁሉ ሁሉም ነገር አስፈላጊ በመሆኑ ነው። «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።» ተብሎ ተጽፏል። ያዕ.5÷16። ከዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምድ በመነሣት ነው ካህኑ ተራዳኢውን ካህን «በጸሎትህ አስበኝ» የሚለው። በመቀጠልም «ሥመር እግዚኦ ከመ ታድኅነኒ፤ አቤቱ÷ ይቅር ትለኝ ዘንድ /ይቅር ማለቱን ውደድልኝ/» እያለ ሦስት ጊዜ ሠራኢው ካህን ለተራዳኢው፣ ተራዳኢው ካህን ለሠራኢው /አንዱ ለአንዱ/ ይጸል ይለታል።

ቃሉ ሦስት ጊዜ መባሉ /መጸለዩ/ የሦስትነት÷ ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ ሲሆን ጸሎትን መላልሶ መጸለይ እንደ ሚገባም ያመለክታል። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው።

«ኤልሳዕም ወደ ቤት በገባ ጊዜ እነሆ ሕፃኑ ሞቶ በአልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር። ገብቶም በሩን ከሁለቱ በኋላ ዘጋ÷ ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ።... ደግሞም ወጥቶ ሰባት ጊዜ በሕፃኑ ላይ ተጋደመ፤ ሕፃኑም ዐይኖቹን ከፈተ /ከሞትም ዳነ/።» /2ነገ. 4÷32–35/።

7. <u>አፈጻጸሙ</u>

ሠራኢው ካህን ከላይ የተመለከተውን ሥርዓተ ጸሎት ከፈጸመ በኋላ ሁለት እጆቹን በመዘርጋት ከወደ ኋላው ጥግ /ድጋፍ/ ከወደፊቱ መቋሚያ ሳይሻ ቀጥ ብሎ ቆሞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ አሰምቶ ያዜማል።

ይህም ምሳሌ አለው። ካህኑ ፊቱን ወደ ምሥራቅ ዞሮ መቆሙ ስለ ሕዝቡ /ምእመናን/ እግዚአብሔርን እንደ ሚለምንላቸው /እንደ ሚጸልይላቸው/ ለማጠየቅ ነው። ልዑል እግዚአብሔር በዓለም የመላ ከዓለምም ውጭ በሁሉ ያለ ቢሆንም ወደ ምሥራቅ ዞሮ መጸለዩ ግን ሥርዓትም ነው። «እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በዔደን ገነትን ተከለ÷ የፈጠረውንም ሰው ከዚህ አኖረው» ዘፍ.2÷8፤ «መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደ ሚታይ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና።» ማቴ.24÷27። ወደ ምሥራቅ ዞሮ ማመስገንና መጸለይ ከላይ በተገለጸው መሠረት የክርስቶስን ዳግም ምጽአትና ሰማያዊ አገርን እያሰቡ መጸለይ ነው። ካህኑ ይህን ለማጠየቅ ወደ ምሥራቅ ዞሮ ያመሰግናል።

ሁለት እጆቹን ዘርግቶ መቆሙም፦ አንደኛ÷ በዕለተ ዓርብ በመስቀሉ ላይ የተፈጸመውን ድኅነት እያሰቡ መጸለይ እንዲገባ፣ ሁለተኛ÷ ጠላትን /ዲያብሎስን/ ድል የማድረግ ምልክት ስለሆነ ነው። «እንዲህም ሆነ÷ ሙሴ እጁን ባነሣ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር።» ዘጸ.17÷11፤ራእ. 3÷12። ሦስተኛ÷ ለእግዚአብሔር በቅንነት የመገዛት ምልክት ነው። «እጃችሁንም ለእግዚአብሔር ስጡ ÷ ወደ ተቀደሰው ወደ መቅደሱም ግቡ፤ /2ዜና 30÷8/ የሚሉት ምንባባት እጅን ዘርግቶ የመጸለይን ሥርዓት የሚገልጹ ናቸውና ካህኑ እጁን ዘርግቶ ወደ ምሥራቅ ዞሮ ያመሰግናል። ሠራኢው ካህን ወደ ምሥራቅ ዞሮ ሥርዓት ሲያከናውን ሠራኢው ዲያቆንም ወደ ምዕራብ /ሕዝቡ ወደ አሉበት/ ፊቱን አዙሮ ይቆማል። ይህም በጸሎተ ቅዳሴ እየተሳተፈ ያለውን ምእመን «ተንሥኡ ÷ጸልዩ» እያለ በመቀስቀስና በማትጋት ካህኑ ለሕዝቡ÷ ሕዝቡም ለካህኑ የሚያደርጉትን የመረዳዳት አገልግሎት በትጋት እንዲፈጽሙ ለማድረግ ነው።

ሠራኢው ካህንና ሠራኢው ዲያቆን በዕለተ ትንሣኤ በጌታችን መቃብር ላይ የታዩት ሁለት መላእክት ምሳሌ /አምሳል/ ናቸው። ምክንያቱም ሁለቱ መላእክት ከጌታችን መቃብር አንዱ በራስጌ አንዱ በግርጌ ሆነው ነበር ለቅዱሳት አንስት የታዩት። «ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በግርጌ ተቀምጠው አየች።» /ዮሐ.20÷11-13/ እንዲል።

«ወበከመ ነበሩ መላእክት በውስተ መቃብር ኀበ ነበረ ሥጋሁ ለእግዚእነ አሐዱ መንገለ ትርአስ ወአሐዱ መንገለ ትርጋፅ ከማሁ ይቁም ካህን መንገለ ትርአስ ወዲያቆን መንገለ ትርጋጽ፤ ሁለት መላእክት የጌታችን ሥጋ በነበረበት መቃብር አንዱ በራስጌ አንዱ በእግርጌ እንደ ነበሩ ሁሉ እንዲሁም ሠራኢው ካህን በራስጌ፣ ሠራኢው ዲያቆን ከመሠዊያው በግርጌ ይቁሙ።» በዚህ ሐተታ ራስጌ የተባለው ወደ ምሥራቅ መቆምን ሲሆን ግርጌ የተባለው ደግሞ ወደ ምዕራብ መቆምን እን ደሆነ ልብ ማለት

ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መንግሥትና

በሥነ መንግሥት ምሥረታ ዘርፍ÷ ህልውናው በሃይማኖት ትምህርትና ሥርዓት ላይ የተመሠረተ፣ ከተቋማቱም ጋር መዋቅራዊ ግንኙነት ያለው መንግሥት «ሃይማኖታዊ መንግሥት» «Religious goverment or theocratic state» ይባላል:: ሁኔታው በፍልስፍና፣በፖለቲካና በታሪክ መስኮች አከራካሪ ቢሆንም በሃይማኖት ትምህርትና ሥርዓት ላይ ያልተመሠረተ መንግሥት ደግሞ «ዓለማዊ መንግሥት» /Secular state/ ይባላል::

የዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ሚያስተምረን የክርስትና ሃይማኖት /ቤተ ክርስቲያን/ እና የመንግሥት ግንኙነት የተጀመረው ቤተ ክርስቲያን ጭቆናንና የግፍ አገዛዝን በማውገዝ ስለ ነጻነትና ስለ እኩልነት ስታስተምር ነበር:: ይህ መርዶ የሆነባቸው አምባገነን መንግሥታት ደግሞ በፊንታቸው እርስዋን ሲያሳድዱና የመከራ ዶፍ ሲያዘንቡባት ነበር:: በኋላ ዘመን የተነሡት «ሃይማኖታዊ መንግሥታት» /heocratic state/ ግን ከዚህ በተቃራኒ ክርስቲያኖች ሆንን ብለው ወደ ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ሕይወት ገቡ:: እርስዋን በመሣሪያነት ተጠቅመው የፖለቲካ ቃል ኪዳን አባላቸው /subordinate/ በማድረጋቸው ለእምነቷና ለቀኖናዋ መፋለስ፣በዘር ልዩነትና በሥልጣን ትግል ሳቢያ በተፈጠረ ግጭት ለአንድነቷ መናጋት ምክንያት ሆነዋል::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ÷ የክርስትና ሃይማኖት ወደ ሃገራችን የገባውና የተስፋፋው ከቤተ መንግሥቱ ጀምሮ ነው:: የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት እንዲሆን የታወጀው በ350 ዓ.ም. ነበር:: ይህ ዐዋጅ በ1967 ዓ.ም በወጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ማቋቋሚያ ዐዋጅና በ1979 ዓ.ም በጸደቀው የኢ.ሕ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት እስከ ተሻረበት ጊዜ ድረስ ቢያንስ ለ1600 ዓመታት የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ጸንቶ ቆይቷል:: በ1948 ዓ.ም በተሻሻለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 126 የሚከተለው ቃል ሰፍሯል፡- « በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱስ ማርቆስ ትምህርት መሠረት የተቋቋመችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መሠረታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት:: ስለዚህ በመንግሥቱ የተደገፈች ናት:: የንጉሠ ነገሥቱ ሃይማኖት ሁልጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሆን አለበት:: » በ1987 ዓ.ም በጸደቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 11/1/ ደግሞ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸው ተደንግጓል:: ሃይማኖት በመንግሥት ጉዳይ÷ መንግሥትም በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ ሕገ መንግሥቱ በግልጽ ይከላከላል::

በሕገ መንግሥቱ ጥበቃ ከተደረገላቸው የዜጎች ሰብአዊ መብቶች አንዱ የሃይማኖት ነጻነትና እኩልነት ነው:: በመሆኑም በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የሕግ አስፈጻሚ፣የሕግ አውጭና የዳኝነት አካላት ይህን መሠረታዊ የሰው ልጆች መብት ከማክበር ባሻገር የማስከበር ሓላፊነትና ግዴታ ተጥሎባቸዋል:: አንቀጽ 13/1/:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ካሳለፍነው የ1997 ዓ.ም ክረምት ወራት ጀምሮ ኢሕአዴግ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ከመንግሥት ሠራተኞች ጋር ውይይት ማካሄዱ ይታወሳል:: በውይይቱ ሂደት በተለይ «ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ» በሚለው ጽሑፍ መነሻነት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በታሪክ የነበራቸውን ግንኙነት አስመልክቶና በተጓዳኝ የተነሡ ነጥቦች በአወያዮችና በውይይቱ ተሳታፊዎች መካከል ሰፊ ክርክር እንደ ተደረገባቸው ተሰምቷል:: ጉዳዩ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናንም ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ ሰንብቷል::

በዚህ ረገድ ለተፈጠረው የግልጽነት ችግር የበኩሉን መፍትሔ ለመሻት የዝግጅት ክፍላችን ከአወያዮቹ አንዱ የነበሩትን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የአቅም ግንባታ ሚኒስትር ክቡር አቶ ተፈራ ዋልዋን አነጋግሯል:: ከክቡር ሚኒስትሩ ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስ ያልተጠናቀቀ ቢሆንም ለጊዜው በተገኘው የቃለ ምልልሳቸው ይዘት ላይ ግን በመመሥረት የተለያዩ ወገኖችን አስተያየት ለማጠናቀር ተሞክሯል:: ከቃለ ምልልሱና ከአስተያየቶቹ በማስቀደም የቃለ ምልልሱንና የአስተያየቶቹን ጭምቅ ሐሳብ በመግቢያ መልክ አቅርበናል:: ለዚህ እትማችን ይህንኑ እንድትከታተሉ እያጋበዝን ለመጽሔታችን ተከታታዮችና ተሳታፊዎች በሙሉ በተነሡት ሐሳቦች ዙሪያ እርስ በርስ እንድትወያዩና የበኩላችሁን እንድታካፍሉን ከወዲሁ ለማስታወስ እንወዳለን:: መልካም ንባብ::

በኢትዮጵያ÷ የአይሁድና የክርስትና ሃይማኖት ታሪክ ከአቅኚዎቿና በየጊዜው ከተነሡ ነገሥታቷ የሕይወት ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው:: «ኢትዮጵያን ያቀኑት የመምለኬ እግዚአብሔር የኖኅ የልጅ ልጆች ሳባ እና አቢስ /ሰብታ/ ስለኾኑ የአያታቸውን አምላክ አንድ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር ቢባል እውነት ይመስላል::» /የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ÷ ገጽ 13/:: በኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት ኢትዮጵያውያን ለዘንዶ ይገብሩ፡- ዘንዶ ያመልኩ እንደ ነበር ተጽፏል:: በአንድ አምላክ ማመን የተጀመረውም በ984 ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ንግሥተ ሳባ ከጠቢቡ ሰሎሞን የወለደችው ቀዳማዊ ምኒልክ የአባቱን አገር ኢየሩሳሌምን ጎብኝቶ ሲመለስ ታቦተ ጽዮንንና ካህናተ ኦሪትን እንዲሁም አያሌ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ከሊቃቻቸው ጋር ይዞ ከመጣና ብሉይ ኪዳን ወደ ግእዝ ቋንቋ ከተመለሰ በኋላ መሆኑን ታሪክ ነገሥቱ በሰፊው ይተርካል::

በተመሳሳይ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሚለው ኢትዮጵያና የክርስትና ሃይማኖት የተዋወቁት ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ÷ በገንዘብዋም ሁሉ የተሾመ ባለሥልጣንዋ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሰግድና ሊጸልይ ሄዶ ሲመለስ በፊልጶስ በተጠመቀ ጊዜ ነው:: /ግብ.ሐዋ.8÷26/:: ይህም የኾነው ከጌታ ልደት በኋላ በ34 ዓ.ም ነው:: የንግሥት ሕንደኬ በጅሮንድ /የገንዘብ ሚኒስትር/ ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ አዲሱን ሃይማኖት ለሀገሩ ሕዝብ አስተምሯል:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት የሚባለው አውሳብዮስ፡- «ሕፅው /ጃንደረባው/ ለወገኖቹ ሐዋርያ ኾነ፤ የኢትዮጵያ ሐዋርያ እርሱ ነው::» ብሏል:: /Eusebius, Church History/

ኢትዮጵያችን ክርስትናን የተቀበለችው በመጀመሪያው ምእት ዓመት ይሁን እንጂ በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስ መንበር የተሰጣት በአራተኛው ምእት ዓመት ነው:: ይኸውም አይዛና ወይም ኤዛና /የአብርሃና የአጽብሐ አባት/ በአክሱም ነግሦ በነበረበት ወቅት በቤተ መንግሥቱ ተከባክቦ ካሳደጋቸው ሁለት ሶርያውያን ምርኮኞች አንዱና የንጉሡ በጅሮንድ የነበረው ፍሬምናጦስ በአክሱም ቤተ መንግሥት ወደ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተልኮ፡- ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ÷ የክህነትንና የቁርባንን ሕግ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል:: ከዚያ በኋላ የወንጌልን ትምህርት በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ለማዳረስ የሚረዱ ቁሳውስትና ዲያቆናት ተሾሙ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ከሱርስት÷ ከዕብራይስጥና ከጽርእ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተመለሱ:: በዚህ አኳኋን በ350 ዓ.ም ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ኾነ:: ኢትዮጵያችንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያን አገር እንደ ኾነች ታወቀች:: በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል ሓላፊ የሆኑት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፡- «በኢትዮጵያ የሰማዕታት ዘመን ያልነበረው ክርስትናው የነገሥታቱ እምነት ሆኖ ከቤተ መንግሥቱ ጋር በነበረው የጠበቀ መስተጋብር ነው:: በሃገሪቱ ክርስትናው ከቤተ መንግሥቱ /ከነገሥታቱ/ ጀምሮ ነው ወደ ሕዝቡ የተስፋፋው:: በሌላው ዓለም ዘመነ ሰማዕታት የሚባለው ክርስትና ከተራው ሕዝብ ተነሥቶ ወደ ነገሥታቱ /ቤተ መንግሥቱ/ እስኪዘልቅ ድረስ ያደረገው ጉዞ ነው:: ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በ311 ዓ.ም ክርስቲያን በመሆኑ የዘመነ ሰማዕታት ፍጻሜ የሆነው ለዚህ ነው::» ይላሉ::

በፊት በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተሰበከችልን በኋላም በቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንና በተከተሏቸው ቅዱሳን አበው የጸናችልን የክርስትና ሃይማኖታችን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ትባላለች:: ለልዑል እግዚአብሔር መመስገኛ ቤተ መቅደስን ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው ንጉሥ ሰሎሞን ለግብጻዊት ሚስቱ መስገጃ ቤተ ጣዖት አሠርቶ ነበር:: በከነዓን ምድር በነገሥታቱ ዘንድ የአሕዛብን ልማድ በማደጎ መውሰድ የተለመደ ነበር:: ነገር ግን የእስራኤል መንግሥትና ሕዝብ እምነት የሚነገረው በአንድ አምላክ ስለ ማመናቸው ነው፤ መታወቂያቸውም ይኸው ነው:: በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብም ዘንድ ላለፉት 3000 ዘመናት /እስከ 1967 ዓ.ም/ የኾነው እንዲሁ ነው:: በ10ኛው መ.ክ.ዘ የዮዲት ጉዲትን የ40 ዓመት፤ በ15ኛው መ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ

ክ.ዞ የግራኝ አሕመድን የ15 ዓመት የወረራና የጥፋት ዘመናት ጨምሮ ብዙ የተለያዩ መሪዎች እየተነሡ ለፖለቲካ አመራር እንዲመቻቸው ሲሉ በርካታ ነገሮችን ቢለውጡና ቢያዳቅሉም የሀገሪቱንና የሕዝቡን ታሪክ ለመለወጥ፥ ክርስትናውን ጨርሰው ለማሸነፍ አልተቻላቸውም።

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት እንደሚያስረዱት፡- የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ጊዜ ከመንግሥት ጋር በነበራት ግንኙነት ጸንታ በመቆየት ከሌሎች የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ቀዳሚውን ሥፍራ ትይዛለች።

የስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዐረቦች ወረራ፣ የ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢንዱስትሪ አብዮት /ዘመነ አብርሆት/ ከእስልምና እምነት መስፋፋት ጋር ተያይዞ በተለይ ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ አብዛኞቹን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከመንግሥታቸው ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አውኮታል፤ ለያይቶታል። የቦልሼቪክ አብዮት ደግሞ ብዙዎቹን የምሥራቅ አውሮፓ መንግሥታት ከሃይማኖትና ከሃይማኖተኝነት ለያይቷቸዋል፤ ፀረ ሃይማኖት እንዲሆኑም አድርጓቸው ነበር። ከእነዚህ አኳያ ስትነጻጸር በዓለም ላይ በተለይ ከኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያና ሁሉ ይልቅ ለረጅም ጊዜ ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት /Official and State established religion/ ሆና ጸንታ በመቆየት የምትታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። ብዙ ክርስቲያኖችና መምህራንም በሌላው ዓለም ሥቃይ ሲጸናባቸው ጥግ ለመሻት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት፣ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝበ ክርስቲያኑም ከአባት በወረደው ደግነቱና እንግዳ ተቀባይነቱ በፍቅር የተ ቀበላቸው፣ እነርሱም አገሪቷን እንደ ተወለዱባት አገር ቆጥረው ክርስትናን ያስፋፉት፣ ገዳማትን የመሠረቱት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን የተረጎሙት በዚህ ምክንያት እንደ ነበር ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ጽፈዋል። /የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ገጽ 23/።

የመንግሥት ህልውና በሃይማኖት ተቋማት ላይ የተመሠረተበት፣ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች፣ ዐዋጆች፣ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች ለመንግሥት ፖሊሲዎች መሠረት ኾነው በሃይማኖታዊ ተቋማት የሚመሩበትና የሚፈጸሙበት የመንግሥት ቅርጽና ባሕርይ ***ሃይማኖታዊ መንግሥት*** (theocracy) **ይባላል።** (Wikipedia, the free encyclopedia). በመድኃኔ ዓለም ከፍተኛ



ቅዱስ ፊልጶስ ኢትዮጵያ ጃንደረባ እንዳጠመቀው (የሐዋ.8፥34)

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የታሪክ መምህር የኾኑት ዲ/ን መንግሥቱ ጎበዜ፡ - በዓለማችን ጥንታዊ የሥልጣኔ አካባቢዎች የተ መሠረቱ መንግሥታት ሃይማኖታዊ (theocratic states) እንደ ነበሩ ያስረዳሉ። ይህም ነገሥታቱን መለኮታዊ አድርጎ ከማምለክ ጀምሮ የሃይማኖት ተቋማትና ከተቋማቱ ተምረውና ተሹመው የሚወጡ ሊቃውንት በመንግሥት የላዕላይና ታሕታይ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ሚና እስከ መጫወት ደርሶ የሚገለጽ ነው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያን ጨምሮ የሮም ቄሣርን ግዛተ መንግሥትና ጥንታዊውን የእስራኤል መንግሥት እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ይህ ሁኔታ በመካከለኛው የታሪክ ዘመን ቀጥሎ «ሥዩመ እግዚአብሔር» የሚባሉ ነገሥታት (Monarchs who ruled by divine right) እና «ራሳቸውን የማይሳሳቱ የክርስቶስ እንደራሴዎች» /God's earthly authority/ አድርገው የሚመለከቱ የሃይማኖት መሪዎች በተለይም በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከሥተዋል። በዘመናዊው የዓለማችን ታሪክም የመንግሥትና ሃይማኖት ግንኙነት መጠን የተለያየ ይሁን እንጂ ሁኔታው በሥልጣኔ ኃያላን በኾኑትና በበለጸጉት የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አራማጅ አገሮች ዘንድም በተለያየ መልክ መቀጠሉ እሙን ነው። የፖለቲካ ሳይንስ ባለሞያ የኾኑት አቶ ፍቅረ ሥላሴ አርአያ ይህን ሲያስረዱ፡ –በአንድ አገር ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት መኖር የዚያን አገር መሠልጠን ወይም አለመሠልጠን፥ ዴሞክራሲያዊ መሆን ወይም አለመሆን አያመለክትም። በኢንግላንድ የአንግሊካን እምነት መንግሥታዊ ሃይማኖት ( state established church) ሲሆን በእምነቱ አስተምህሮ፥ ሥርዓትና መዋቅር ላይ የሚደረግ መሠረታዊ ለውጥ የፓርላማውን ይሁንታ ማግኘት አለበት። የኢንግላንድ ንግሥት ወይም ንጉሥ የእምነት ተቋሙ የበላይ ገዥ ( Supreme Governor)፥ የእምነቱም ጠባቂ (Defender of the Faith) ናቸው። የብሪታንያ ርእሰ መንግሥት /Head of State/ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ከመሆን ይከለከላል። ታላላቅ የእምነቱ ጳጳሳትም በብሪታንያ ላዕላይ ምክር ቤት /House of Lords/ የመቀመጥ መብት አላቸው። እንደ ሮም ካቶሊክ ሁሉ በአንግሊካን እምነት /Church of England/ የሚተዳደሩ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች አሉ።

በስዊድን የሉተራን እምነት ተቋም ከመንግሥት ጋር ባላት ግንኙነት እ.ኤ.አ በ1999 መጠነኛ ልዩነት እንዲኖራት ቢደረግም ከሌሎቹ እምነቶች ግን ልዩ መብት እንዲኖራት ተደርጓል። በኖርዌይ ደግሞ የኢቫንጀሊካል - ሉተራን እምነት ከ1537 ዓ.ም ጀምሮ በጀቷ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት የሚሸፈንበትና መሪዋም ሳይቀር በመንግሥት የሚሾምበት ሁኔታ ነው ያለው። ርእሰ መንበሯም የሀገሪቱ ንጉሥ ናቸው። በሩሲያ ፌዴሬሽን እ.ኤ.አ በ1990 የሩሲያ ፓርላማ ባወጣው የእምነት ነጻነት ሕግ /Freedom of Conscience/ አንድ እምነት ብሔራዊ /Official religion/ ለመሆን ለ50 ዓመት በሀገሪቱ መቆየት ይጠበቅበታል። ይሁንና ጥንታዊቷ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሀገሪቱ ከቆዩት የአይሁድ፣ የካቶሊክ፣ የሉተራንና የባፕቲስት እምነቶች በተለየ መልኩ ልዩ መብት አላት።

በቫቲካን የመንግሥትና የሃይማኖት /ካቶሊክ እምነት/ ግንኙነት ፍጹም አንድ (theocratic) ሆኖ የሚታይበት ነው። በእስልምናውም በኩል የሳዑዲ ዐረቢያና የኢራን መንግሥታት ከቫቲካኑ ጋር ተመሳሳዮች ናቸው። በቱርክ የሃይማኖትና የመንግሥት ግን



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ኙነት በተፀቅቦ (Separation) እንደ ሆነ የቱርክ መንግሥት በተደጋጋሚ ይገልጻል:: በተግባር ግን ብዙኀኑ የሱኒ እስልምና በመንግሥታዊው የሃይማኖት ጉዳዮች ዲፓርትመንት የሚታገዝበትና በገንዘብ የሚደገፍበት፣ ከዲፓርትመንቱ ቁጥጥር ነጻ የኾኑና ግንኙነት የሌላቸው የሱኒ እስልምና ማኅበራት ሕገ ወጥ የሆኑበት፣ በቁጥር አናሳተከታይ ላላቸው የሶርያ፣ የአርመንያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ የግሪክ አርቶዶክስና የሮም ካቶሊክ ሃይማኖት ማኅበራት ብዙም ነጻነት ያልተሰጠበት፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ለመቀጠር ለሙስሊም ባለሞያዎች ቅድሚያ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው ያለው::

ከላይ ከተጠቀሱት አገሮች በመለስ ደግሞ የሃይማኖት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርትን ቀርጸው ትምህርትን በማስፋፋት፣ ልማታዊና ማኅበራዊ ሚናን በመጫወት የላቀ ድርሻ የያዙባቸው፣ ከመንግሥታት በብዙ መንገድ የሚደጎሙባቸው፣ ከተከታዮቻቸው ግብር እስከ መሰብሰብ ድረስ መብት የሚሰጥባቸው አገሮች አሉ:: ለዚህም:- ካናዳን፣ ፈረንሳይን፣ ጀርመንን ወዘተ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይበቃል:: በተናጠል በአገሮች ደረጃ ያለው ሁኔታ በተወሰነ መልኩ ይህን ሲመስል በአህጉር ደረጃ አንድን ሃይማኖት ትውፊታዊ መለያ /ማንነት/ አድርጎ ለማሳየትና ሌላውን ለማግለል የተሞከረበትን ሁኔታ ደግሞ በቅርቡ ታዝበናል:: ይኸውም በኋላ ላይ እንዲቀር ተደረገ እንጂ የአውሮፓ ኅብረት ሕገ መንግሥት ሲረቀቅ የክርስትና እሴቶችን የኅብረቱ መለያ ታሪካዊ ውርስ የሚያደርግ ሐሳብ በረቂቁ ውስጥ ነበረበት:: በቅርቡ ደግሞ ኦስትርያ የኅብረቱ ሙሉ አባል አገር ለመሆን ለ42 ዓመታት ጥረት ያደረገችውን ቱርክን «በኦቶማን ቱርክ ወረራ ወቅት ተፈጽሟል» ከምትለው በደልና ቀደም ሲል ከተገለጸው እስላማዊ ማንነቷ ጋር በተያያዘ የሙሉ አባልነት ጥያቄዋን በመቃወም የተባባሪ /አጋር/ አባልነት /«favored nation»status/ እንዲሰጣት ጠይቃለች:: ኦስትርያ በቅርቡ ባካሄደችው ሕዝበ ውሳኔ 70 ከመቶ የሚሆኑት የኦስትርያ ዜጎች ይህንኑ አቋሟን ደግፈዋል:: ኦስትርያ ከእስላማዊዋ ቱርክ ይልቅ በአመዛኙ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ለሚበዙባት ክሮሽያ የአባልነት ንግግር /accession talks/ ቅድሚያ እንዲሰጣት ተከራክራለች:: ብዙዎች የኦስትርያን አቋም አሳፋሪ ብለውታል:: የቱርኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ይህ ሁኔታ:- «ኅብረቱን የክርስቲያኖች ክበብ ብቻ አድርጎ የሚያስቀር÷ በምዕራቡና በእስላሙ ዓለም መካከል ያለውን የሥልጣኔ ግጭት የሚያካርር ነው::» ብለውታል:: የወቅቱ የአውሮፓ ኅብረት ፕሬዝዳንት የኾነችው የብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጃክ ስትሮው በበኩላቸው:- «በቱርክ የአባልነት ጥያቄ ላይ መግባባት ካልተደረሰ ሁኔታው የክርስቲያንና የእስላም መንግሥታትን



አቡነ ፍሬምናጦስ - ከሣቴ ብርሃን

ግንኙነት ይጎዳል:: ነገረ መለኮታዊ - ፖለቲካዊ ክፍፍሉ /theological – political divide/ ክርስቲያናዊ ውርስ ባላቸው መንግሥታት /Chri stian heritage states/ እና እስላማዊ ውርስ ባላቸው መንግሥታት /Islamic heritage states/ መካከል ያለውን ልዩነት ያሰፋዋል::» በማለት ስጋታቸውን ገልጸዋል:: ከ25ቱ የኅብረቱ አባል አገሮች አንዷ ፈረንሳይ የቱርክን የሙሉ አባልነት ጥያቄ ብትደግፍም ይህን ያህል የእስልምና እምነት ተከታይ ሕዝብ ካላት አገር ለተሻለ ኑሮ ወደ እርሷ ሊጎርፉ በሚችሉ ሙስሊም ስደተኞች የመጥለቅለቅ ስጋት እንዳለባት ይነገራል::

ከላይ ከተዘረዘሩት አገሮች ብዙዎቹ በመንግሥታዊ ቅርጻቸውና ባሕርያቸው ዓለማዊ /Secular states/ ሲሆኑ ከሃይማኖት ተቋማት ጋር ያላቸውን የተፀቅቦ ግንኙነት /Separation/ በሕገ መንግሥታቸውና በሕገ መንግሥታቸው በታቀፉ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ቀርጸዋል:: ይሁንና ሃይማኖትን መንግሥታዊ፣ ብሔራዊ ወይም ሁለቱንም ባደረጉት አገራት /ፊንላንድ፣ ኖርዌይ፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ግሪክ፣ ዴንማርክ፣.../ ውስጥ ያሉ የሌሎች እምነቶች መብት የተገፈፈበት ወይም የእምነት ነጻነታቸው የተጨቆነበት የጎላ ሁኔታ ግን አይታይባቸውም::

በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ዞን የሰላሌ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ:- «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት ሆና መኖሯ የሚያስወቅስ አይደለም:: በሌሎችም ሀገሮች ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት ነበረ፣ ዛሬም አለ:: ሌሎች ከእርሷ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ሳትቃወም አክብራ ተቀብላቸዋለች» በማለት ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ለመጀመሪያዎቹ የእስልምና እምነት ተከታዮች ያደረገውን አቀባበል ያስታውሳሉ:: የፖለቲካ ሳይንስ ባለሞያው አቶ ፍቅረ ሥላሴ አርአያ ደግሞ:- «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት ሆና ለዘመናት ኖራለች:: ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር የነበራት ግንኙነት በሁለት ደረጃዎች ሊታይ ይችላል:: የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያኒቱን ወክለው በአመራር ደረጃ በሚሠሩት ሰዎች የነበረው ግንኙነት ሲኾን ሌላው ደግሞ በመንግሥትና በምእመኑ መካከል የነበረው ግንኙነት ነው:: በመንግሥትና በአመራሩ መካከል በነበረው ግንኙነት አንዱ ሌላውን የመጥቀም ሁኔታ ነበር:: እንደ አጠቃላይ ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ለቤተ መንግሥቱ የነበራትን ቅርበት ያህል መጠቀም የምትችለውንና የሚገባትን ያህል ግን አልተጠቀመችም::» ይላሉ:: አቶ ፍቅረ ሥላሴ:-«በአመራር ደረጃ የሚደረግ ተቋማዊ ግንኙነት» ብለው ያስቀመጡት ነጥብ ዲያቆን ዳንኤል:- «ከእስክንድርያ ተሹመው ይመጡ የነበሩት ግብጻውያን ጳጳሳትና የአስተዳደር ሥራውን የሚመሩት ዕጨጌዎች ከመንግሥት ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት» ማለት እንደ ኾነ ይገልጻሉ:: «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መሠረታዊት የመንግሥት ሃይማኖት ነበረች» ስንል የበለጠ ትርጉም የሚሰጠው ጳጳሳቱና ዕጨጌዎቹ ከቤተ መንግሥቱ ጋር ለነበራቸው ግንኙነት ነው:: ይኸውም ቤተ ክርስቲያኒቱ በማዕከል የተዋቀረ አስተዳደር ስላልነበራት የየክፍለ ሀገሩ ምእመን የጠበቀ ግንኙነት የነበረው ከደብሩ ካህንና መሪጌታ፣ ከገዳሙ መነኮስና ባሕታዊ ጋር ነበር:: የጳጳሱ አስፈላጊነት ጎልቶ የሚታየው በሚሰጠው የክህነት ሹመት ነበር:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድነት መገለጫዋ ማዕከላዊ የአስተዳደር መዋቅር ስለ ነበረ ሳይሆን የትምህ ርተ ሃይማኖቷ፣ የሥርዓተ እምነቷና የክርስቲያናዊ ትውፊቷ ሥምረት ነበር:: ነገሥታቱና ዕጨጌዎቹ ለታላላቅ ገዳማትና አድባራት አበምኔቶች ሹመት የሚሰጡ ቢሆንም ከምእመናኑ ጋር መደበኛና የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ግን ካህናቱና መነኮሳቱ /Monastic and Secular Clergies/ ነበሩ:: ስለዚህ በአውሮፓ ብሔራዊና የመንግሥት እምነቶች ከመንግሥት ጋር የነበራቸውን የግንኙነት ሁኔታ በመጥቀስ በኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደ ተጠቀመች አድርጎ ማቅረብ አስቸጋሪ ነው::» በማለት ዲያቆን ዳንኤል ያብራራሉ:: የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራትም <Church and State in Ethiopia, 1270-1527> /1972/ በተሰኘው መጽሐፋቸው:- «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር የነበራት ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንኳ የተፈጠረላትን መልካም ዕድል ተጠቅማ ክርስትናውን ለማስፋፋት የሚያስችላት ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር /Organizational structure/ አልነበራትም:: ከዚያ ይልቅ ክርስትና በኢትዮጵያ የተስፋፋው በባሕታውያንና በመነኮሳት ሐዋ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ርያዊ ትጋት እንዲሁም በሕዝቦች እንቅስቃሴ ነው።» የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።

ባሳለፍነው የ1997 ዓ.ም የክረምት ወራት ጀምሮ እስከ 1998 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች ለሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ከላይ የገለጽነውን የመሰሉና ሌሎች ለውይይት የተዘጋጁ ጽሑፎች ቀርበው ውይይት እንደ ተካሄደባቸው ይታወሳል። ጽሑፉንና እርሱን መሠረት አድርጐ ከተደረገው ውይይት ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ እምነት እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችን በታሪክ ከመንግሥት ጋር በነበራት ግንኙነት ላይ የተመሠረቱ ጉዳዮች ተነሥተው በአወያዮችና በውይይቱ ተሳታፊዎች መካከል ሰፋ ያለ ክርክር መካሄዱ ተሰምቷል።

በየክልሉ በተካሄዱት ውይይቶች ቤተ ክርስቲያናችንን አስመልክቶ የተነሡ ጉዳዮች ለሦስትና ለአራት ቀናት ያህል ቆይታ የተደረገባቸው ነበሩ። የዝግጅት ክፍላችን በተለይ «ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ» በሚል ርእስ ለውይይት የተሰናዳውን ጽሑፍ ለማጤን ሞክሯል። የውይይቱ ተሳታፊዎች የነበሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን በማግኘት፣ በጉዳዩ ዙሪያ በተለያየ መንገድ ሲዘግቡ የነበሩ የኅትመትና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃንን በመከታተል ተጨባጭ ሐሳቦችን ለማሰባሰብ ጥረት አድርጓል። ችግሩ የነበረው በአመዛኙ በሁሉም ክልሎች በተካሄዱ ውይይቶች ላይ ይሁን እንጂ ጎልቶ የታየባቸው ክልሎች ግን ነበሩ። ከእነርሱም አንዱ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው። ውይይቱ በፕላዝማ ቴሌቪዥን በመታገዝ የተካሄደ ሲሆን አወያዩም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የአቅም ግንባታ ሚኒስትር አቶ ተፈራ ዋልዋ ነበሩ። የዝግጅት ክፍላችን ለምእምናን ግልጽ እንዲሆኑ ካሰባሰባቸው ከ10 በላይ ጥያቄዎች መካከል በተፈቀደለት ግማሽ ሰዓት ውስጥ ለክቡር ሚኒስትሩ አቅርቦ መልስ ለማግኘት የቻለው ከአራት ለማይበልጡ ጥያቄዎች ብቻ ነው። ይኸውም ክቡር ሚኒስትሩ በወቅቱ በነበረባቸው ከፍተኛ የጊዜ መጣበብ ነበር። የዝግጅት ክፍሉ ከሚኒስትሩ በተሰጠው ተስፋ መሠረት በድጋሚ ቀጠሮ ተገናኝቶ ዋነኛ ለሚላቸው ቀሪ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ጥረት ያደረገ ቢሆንም ክቡር ሚኒስትሩ በነበረባቸው የጊዜ መጣበብ ምክንያት ለዚህ እትማችን ሊደርስልን አልቻለም። ይሁንና በዚህ እትማችን የክቡር ሚኒስትሩን ምላሾች በመያዝ ከተለያዩ ወገኖች ያሰባሰብናቸውን አስተያየቶች ከቃለ ምልልሱ በማስከተል አቅርበናል። ወደፊት ምናልባትም ለቀጣዩ እትማችን በሚደርስበት ሁኔታ ክቡር ሚኒስትሩ ለቀሪ ጥያቄዎቻችን ምላሽ እንደ ሚሰጡን ተስፋ በማድረግ በበዐለ መስቀል ዋዜማ፥ በዕለተ ደመራ፥ከቀትር በኋላ ከክቡር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የአቅም ግንባታ ሚኒስትር አቶ ተፈራ ዋልዋ ጋር ያደረግ ነውን ቃለ ምልልስ አቅርበንላችኋል።



ክቡር አቶ ተፈራ ዋልዋ ከዝግጅቱ ክፍሉ ጋዜጠኞች ጋር ቃለ ምልልስ ባደረጉበት ወቅት

«ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያ እንዴት ተፈጠረች ሲወራ፥ ፖለቲካው ሲተነተን፥ እንዲህ ዓይነቷን ትልቅ ተቋም ወደ ጎን መተው አይቻልም።» /አቶ ተፈራ ዋልዋ/

ሐመር፡- ክቡር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ አቅም ግንባታ ሚኒስትር አቶ ተፈራ ዋልዋ፥ ከሁሉ አስቀድሞ ለቃለ ምልልሳችን ፈቃደኛ ኾነው ጊዜዎትን ስለሰጡን እናመሰግናለን። እንደ ሚታወሰው፥ ኢሕአዴግ ባሳለፍነው የ1997 ዓ.ም የነሐሴ ወር አጋማሽ አንሥቶ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አዋሳ ከተማ ከክልሉ ተወላጆች፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች ጋር ለሳምንታት የዘለቀ ውይይት ሲያካሂድ ቆይቷል። በዚህ ውይይት ሂደት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ እምነት እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችን በታሪክ ከመንግሥት ጋር ከነበራት ግንኙነት አኳያ የተያያዙ ጉዳዮች በእርስዎ በኩል መነሣታቸው በውይይቱ ተሳታፊዎችና በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን መነጋገሪያ ኾኖ ሰንብቷል። እርስዎ የተናገሩት ነገር ምንድን ነበር? በተናገሩት ነገር ለማስተላለፍ የፈለጉት መልእክትስ ምንድን ነው?

አቶ ተፈራ፡- መልካም፥ የግል ጋዜጦች ብዙ ነገር ማለት እንደ ጀመሩ ሰምቼአለሁ። እያንዳንዳቸውን አላየሁም። ግን ያዩ ሰዎች ሲነግሩኝ፡- <ቤተ ክርስቲያንን በተለይም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ምን ብለህ ነው የሰደብኸው?> እያሉ ነው የጠየቁኝ። ይህን ከየት ነው የሰማችሁት ብላቸው፡- <ከግል ጋዜጦች ነው፤ ከአዲስ አበባ ነው> ሲሉኝ እኔ ምንም አልገረመኝም። ለምንድን ነው ያልገረመኝ.... ያው በእነዚህ ጋዜጦች የተባለም ያልተባለም ብዙ ነገር ስለሚባልባቸው ብዙም አልደነቀኝም። ለማንኛውም ዛሬ የመስቀል ደመራን በዓል በምናከብርበት ዕለት <የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋዜጠኞች ይፈልጉሃል> ሲባል በደስተኝነት ነው..... በዚህ ደረጃም ወደ ተደራጀ የጋዜጠኝነት ቡድን መድረስ፣ ቤተ ክርስቲያኒቷ መሥራቷን ስሰማ ደስ ስላለኝ ነው ያገኘኋችሁ። ለማንኛውም ወደ ጥያቄው ለመምጣት.... በአዋሳ ለረጅም ጊዜ የቆየ ስብሰባ ነበረን። በዚህ ላይ ስንወያይ የነበረው፡- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት መገንባት ይቻላል ነው። የተወያየነው ከወጣት ምሁራን፣ ከዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና ከሌሎችም ጋር ነው። ስንወያይ እንግዲህ፥ ድሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አልነበረም፤ አሁን ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት ተጀምሯል። ድሮና ዛሬ ልዩነቱ ምንድን ነው? የሚለውን ነው የምንወያየው። ልዩነቱን በምንወያይበት ጊዜ በጥሩም ይሁን በመጥፎ ኢትዮጵያ ስትነሣ የኢትዮጵያ ነባር ሃይማኖቶች አብረው ይነሣሉ። አንድዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖትም አብሮ ይነሣል። ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያ እንዴት ተፈጠረች ሲወራ፥ ፖለቲካው ሲተነተን፥ እንዲህ ዓይነቷን ትልቅ ተቋም ወደ ጎን መተው አይቻልም። ፊትና ዛሬ ልዩነቱ ምንድን ነው? ብለን ስንነጋገር፥ ፀረ ዴሞክራቲክ በነበረው ሥርዓት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ሃይማኖቱ የመንግሥት ሃይማኖት ተደርጎ ነበር። ሌላው ቀርቶ ሲሶ ሥልጣን፣ ሲሶ የመሬት ባለቤት የሚሉ ነገሮች በቀድሞው የአገራችን የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ እንደ ሥርዓት ነበር። ከዚህም ተነሥቶ የመንግሥት ሥልጣንም በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ጣልቃ ይገባ ነበር። ሌላው ቀርቶ እጅግ የሚያስገርመው «ከሃይማኖት ነጻ ነኝ» የሚለው የደርግ መንግሥት ሳይቀር ለቤተ ክህነቱ ሥራ አስኪያጅ ይሾም ነበር። እናንተ ታውቁ ይሆናል..... ለማንኛ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ውም <የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ነው> ተብሎ በፍትሐ ብሔር ሕጋችን ውስጥ አለ:: ስለኾነም በመጀመሪያ ደረጃ መንግሥትና ሃይማኖት ያልተለያየ ነበር:: ሁለተኛው ነገር የዚያን ጊዜ በነበሩ ፖለቲካዊ ሥርዓቶች የአገራችን ነባር ሃይማኖቶች ሁሉ እኩል አይታዩም ነበር:: ይህ ምን ማለት ነው? በአውሮፓ ክርስትና ከመስፋፋቱ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትና ተስፋፍቶ እንደ ነበር ያው ከቤተ ክህነት የተማርነው ነው፥ እናውቃለን:: በተመሳሳይ ሁኔታ የእስልምና ሃይማኖት ሲፈጠር፤ ዛሬ የእስልምና ሃይማኖት የሚከተሉትን ሳዑዲ ዐረቢያን ሌላም ሌላም ብንወስድ እስልምናን የተቀበለ ሰው ሳይኖራቸው በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የእስልምና ሃይማኖት ተቀባይነት አግኝቶ እንደ ነበር ዛሬ ግልጽ ኾኖ እያወቅነው የመጣነው ነገር አለ:: የመጀመሪያው ሂጅራ የተደረገው ከመካ ወደ መዲና ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ነበረ ነው የምናውቀው:: ይኼ እንግዲህ በእውነት ለመናገር ታላቅ ታሪክ ነው ለኢትዮጵያ፥ በእውነት ለመናገር:: ክርስትና በአውሮፓ ሳይስፋፋ በኢትዮጵያ ውስጥ መስፋፋቱ ታላቅ ታሪክ ኾኖ እንደ ምንኮራበት ኹሉ በእስልምናም ሃይማኖት የመጀመሪያው ሂጅራ ወደ ኢትዮጵያ መኾኑን ብዙ ኢትዮጵያውያን ያውቃሉ ብዬ አልገምትም:: እናም ነባሮቹንም ኾነ በየጊዜው የሚኖሩትን ሃይማኖቶቻችንን በእኩል ያለ ማየት ችግር ነበር:: እንግዲህ ሃይማኖት የፈለገውን የማመን ነጻነት መገለጫ ነው:: ይህ የዜጎች ነጻነት መጓደሉን ጭምር ነው የምናነሣው:: አሁንስ ልዩነቱ ምንድን ነው? የሚለውን ስናነሣ ልዩነቱ፥ አሁን የመንግሥት ሃይማኖት የሚባል ነገር የለም:: ሁሉም ሃይማኖት፥ ማንኛቸውም፥ የመንግሥት አይደለም:: የመንግሥት ሓላፊነት የሁሉንም ሃይማኖቶች መብቶች ማስከበር ነው::

ስለዚህ በዚህ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ተደርጎ ይወሰድ የነበረው መቅረቱ አንዱ ልዩነት ነው:: ሁለተኛው ልዩነት ደግሞ ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል ይከበራሉ:: የእስልምናም፣ የክርስትናም ሃይማኖቶች መብታቸው እኩል ይከበራል:: ዛሬ፥ ዛሬ ብዙ ዓይነት ክርስትና አለ:: ስለዚህ የሁሉንም ሃይማኖት እኩልነት የሚያስከብር መንግሥትና ፍላጎት፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ስለ ተጀመረ ልዩነቱ ይኼ ነው:: ከዚህ ሌላ እንግዲህ ቀድሞ ይኽ ሃይማኖት «የመንግሥት ነው» ተብሎ ስለ ነበር የፖለቲካ ሥርዓቱ በሕዝብ ላይ በደል ሲያደርስ ወደድንም ጠላንም የመንግሥት ሃይማኖት የተባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አብሮ ተጠያቂ ነው የሚደረገው:: ለምሳሌ:- የሃይማኖት እኩልነት ባለ መከበሩ ምክንያት «የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የመንግሥት ነው» ተብሎ መንግሥት ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት አድልዎ አደረገ:: ጥሩ ነገር አደረገ ወይም መጥፎ ነገር አደረገ ሌላ ጉዳይ ነው:: አደረገ ሲባል ግን ሌላው የሚከፋበት፥በግልጽ ለመናገር የእስልምና ሃይማኖት የሚከፋበትን፥ ሲከፋ ደግሞ «ይኽ ፖለቲካዊ ሥርዓት እንዲህ ዓይነት ጉዳት አደረሰብኝ፤ የሃይማኖት እኩልነቴ እንዲከበርልኝ አላደረገልኝም» ብቻ አይደለም የሚለው፤ መንግሥት ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት የመጠጋትና ጣልቃ የመግባት ችግርም ስለ ነበረ ሌላው ወገን እኩልነቱ ስላልተከበረ አብሮ ነበር ቅሬታ የሚያድርበት:: በመኾኑም ሃይማኖት እያንዳንዱ ዜጋ የሚረካበትና ነጻነቱን የሚገልጽበት ኾኖ ሳለ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ላይ ችግር ያስከተለ ነው:: ለዚህም የደርግ ጊዜ ጥሩ ምሳሌ ነው:: በአንድ በኩል የደርግ መንግሥት አንድ ነገር ይፈልጋል:: በሌላ በኩል ደግሞ በነጻነት መንቀሳቀስ፣ማድረግ፣ መሥራት፣ ምእመናንን ማርካት፣ ሌሎች ምእመናንን ማፍራት የምትፈልገውን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ እንቅፋት ይሆንባት ነበር::



ክቡር አቶ ተፈራ ዋልዋ

እንግዲህ የምንነጋገር የነበረው በአጭሩ:- ዴሞክራሲያዊ ባልኾነ ሥርዓት ውስጥ በሃይማኖት በኩል በአገራችን የነበረው ችግር፥ ፖለቲካዊ ሥርዓቱ ያመጣው ችግር እና ዴሞክራቲክ ሥርዓቱ ደግሞ ሃይማኖቶች እያንዳንዱ ዜጋ በነጻነት የሚያምንበትና እንደ ፈለገው የሚያበለጽግበት፣ የማይገደብ መኾኑን ልዩነቱን የሚያሳይ፥... እንግዲህ ብዙ ዝርዝር አለው፤ እዚያ ውስጥ አንገባም፤ ልዩነቱን የሚያሳይ ነገር ነው የምንወያይ የነበረው:: ይኼ እንዴት አድርጎ ስድብ እንደ ኾነ በፍጹም ሊገባኝ አልቻለም::

በአጋጣሚ ትላንት ይሁን ከትላንት ወዲያ አንድ ጋዜጣ /መስከረም 14 ወይም 15 ቀን 1997 ዓ.ም የወጣ / የግል ጋዜጣን ማለታቸው ነው/ አይቻለሁ፤ እና «ተፈራ ዋልዋም ይሁን ኢሕአዴግ ከቤተ ክርስቲያናችን እጁን ያንሣ» የሚል ነው:: በነገራችን ላይ በዚህ አገር ታሪክ ውስጥ እኔ እንደ ፖለቲከኛ የማውቀው ለመጀመሪያ ጊዜ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ እጁን ያነሣ መንግሥት፥ እጁን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳያስገባ ያደረገ ቢኖር ኢሕአዴግ የሚመራው መንግሥት ነው:: ኢሕአዴግ 'ኮ የሚመራው መንግሥት በደርግም ጊዜ በኃይለ ሥላሴም ጊዜ እንደ ሚታቀው «የቤተ ክርስቲያን ሥራ አስኪያጅ ሹምልን» ተብሎ ተጠይቆ «የለም፥ ራስዋ ቤተ ክርስቲያኒቱ ትሾማለች እንጂ እንደ ቀድሞው መንግሥት አይሾምላችሁም» የሚል መልስ የሰጠ መንግሥት ነው:: ይህ የእኔም እምነት ነው:: እና ምን ላይ፥ የቤተ ክህነቱ፥ የሃይማኖቱ ጉዳይ ላይ እኔም እጄን እንዳስገባሁ አይገባኝም:: ይኼ ተሳድቧል፥ ምን... የሚለው ትርፉ ጨዋታ ስለኾነ እርሱን ንቆ፥ መተው ጥሩ ነው:: ቁም ነገሩ በአጭሩ፥ ለጠየቃችሁት መልሱ ይኼ ነው ለማለት ነው:: የቀረ ጥያቄ ካለ ልታነሡልኝ ትችላላችሁ::

ሐመር:- ከእዚሁ ጋር አያይዘን የምናነሣው:- ከታሪክ እንደ ምንረዳው፥ እርስዎም ቀደም ሲል እንደ ገለጹልን ቤተ ክርስቲያናችን የነገሥታቱ የፖለቲካ መሣሪያ ከመኾን በቀር የሚነገረውን ያህል የተጠቀመችበት ባይሆንም «ሲሶ መንግሥት» ነበረች:: የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትም ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት ነበር:: ከዚህ ነባራዊ እውነትና ሐቅ በመነሣት በታሪክ የተፈጸመውን ነገር አሁን ባለው አስተሳሰብ መዝነን ስሕተት ወይም ትክክል ነበር ለማለት እንችላለን? ወይም በታሪክ

ቀድሞ ይኽ ሃይማኖት «የመንግሥት ነው» ተብሎ ስለ ነበር የፖለቲካ ሥርዓቱ በሕዝብ ላይ በደል ሲያደርስ ወደድንም ጠላንም የመንግሥት ሃይማኖት የተባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አብሮ ተጠያቂ ነው የሚደረገው::



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የተፈጸመውን ነገር ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ልዩ መገለጫ አድርገን መገምገም ወይም መስጠት እንችላለን ወይ? ለምሳሌ:- በአውሮፓ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በ<መስቀላውያን> ዘመቻ ወቅት፣ በመካከለኛው ምሥራቅ እስልምናን ብናይ ከዚህ የተለየ ስላልኾነ ማለት ነው:: በመኾኑም በጊዜው በየአህጉሩ ከነበረው እውነታ አኳያ ጥንታዊትዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር የነበራትን ግንኙነት በስሕተትነት መፈረጅ እንችላለን ወይ?

አቶ ተፈራ:- ቆንጆ ነው:: እንግዲህ ፖለቲካዊ ጉዳይ በምንነጋገርበት ጊዜ ወይም ያለፈ ታሪክን ስንነጋገር እውነታው ምን ነበር? እያልን ማንሣታችን የማይቀር ነገር ነው:: ጥሩ ምሳሌ አንሥተሃል:: አሁን በአውሮፓ <ክሩሴድስ> የሚባለው ጦርነት ነበር:: የክርስትና ሃይማኖትን በመላው ዓለም ለማስፋፋት የተካሄደ ጦርነት ነው:: በዚያ ጦርነት ጊዜ ምን ኾነ የሚለውን ነገር ከፈለግነው የታሪክ መጽሐፍ እናገኛለን:: ሰው ሞቷል፥ውድመት ነበር:: በተመሳሳይ የጅሃድ ጦርነት ተካሂዷል:: ይኼን እንግዲህ መጻሕፍት ጽፈው ጽፈው አስቀምጠዋል:: እውነትም ነው:: የሰው ልጅ ያለቀበት ታሪክ ነው:: በዚህ ታሪክ ውስጥ ደግሞ ጥሩ ነገር ምን ነበር? ምንድን ነበር ችግሩ? የሚባለው ነገር ሁሉ ይታያል:: ይኼ ብቻ አይደለም:: ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአንድ አገር መሠረትን ስንል ከበፊቱ በምን ይለያል፤ በብዙ ነገር ይለያል:: በዴሞክራሲ የመረጡትን መከተል መብት ነው፤ የዴሞክራሲያዊ መብት አንዱ መገለጫ እኮ በሃይማኖት የፈለግነውን እምነት የመቀበል፣ የማስፋፋት፣ የማራመድ ነጻነት ማግኘት ማለት ነው::

በመጀመሪያ:- በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስለ ሃይማኖት ነጻነት፣ ስለ ሃይማኖቶች እኩልነት፣ የእያንዳንዱ ዜጋ የፈለገውን የመቀበልና የማራመድ መብቱን ሳናወሣ፣ ከድሮው ጋር ፀረ ዴሞክራሲያዊ እና ዴሞክራሲያዊ የነበረውን ሥርዓት ሳናነጻጽር ምንድን ነው የምንነጋገረው ታድያ? ስለዚህ መነሣቱ የማይቀር ነው:: ስሕተት ነበር፥ አልነበረም፤ ስሕተት የነበሩ ነገሮች ተገቢ የነበሩ ነገሮች ይነሣሉ:: ለምሳሌ:- የኢትዮጵያን ነባር ሃይማኖቶች ብንወስድ በፀረ ቅኝ አገዛዝ ንቅናቄ ቅኝ አገዛዝን በመዋጋት የታወቁ ሃይማኖቶች ናቸው:: የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በዚህ ላይ ትልቅ ሚና እንደ ነበራት፤ ሌሎችም ብዙ መልካም ነገር እንደ ነበራት ልናወራ እንችላለን:: ከዚህ ሌላ ደግሞ የዛሬ 100 ዓመት 200 ዓመት .....ከዚያም በላይ ለረጅም ዓመታት ተቆጥሮ ወደ ተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍሎች የኦርቶዶክስ እምነትን ለማስፋፋት የተካሄደ ብዙ እንቅስቃሴ ነበር፤ እኔ በራሴ ዕድሜ ስመለከት፥ በአጭር ጊዜ ውስጥ፥ 50 ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የመጡና ብዙ ሰው የሚከተላቸውን ሃይማኖቶች እናገኛለን:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን እኛ ከመወለዳችን በፊት ለረጅም ጊዜ በዚያ ቦታ ላይ ነበረች:: ለምንድን ነው በዚያ አካባቢ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ለረጅም ጊዜ ቆይቶ በስፋት፣ የአብዛኛው ዜጋ ሃይማኖት መኾን ያልቻለው የሚል ጥያቄ ማንሣት ይቻላል:: ለማንኛውም፥ አሁን እዚያ ግምገማ ውስጥ ለመግባት አይደለም:: ግልጽ ነው..... ጉዳዩ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ፀረ ዴሞክራሲያዊ የኾነ ሥርዓት ለሃይማኖቶች ምን ነጻነት ይሰጣል፤ ያኛው ነጻነት ይነፍጋል፤ ነባር ሃይማኖቶች እዚህ አገር ውስጥ እንደ ነበሩ እነዚህ ሃይማኖቶች በእኩል .... የየዜጋው እኮ ናቸው፤ በነገራችን ላይ የእስልምና ሃይማኖትን የሚከተለው፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትንም የሚከተለው ኢትዮጵያዊ ነው፤ ሌላም ሃይማኖት የሚከተል ብዙ አለ... ኢትዮጵያዊ ነው:: ይህን ሁሉ ኢት ዮጵያዊ በዘመኑ እኩል አለማድረጉ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዐይን ሲታይ ስሕተት ለመኾኑ ምን ጥያቄ አለው? ያ ፖለቲካዊ ሥርዓት የሃይማኖት ነጻነትንና እኩልነትን አላስከበረም ማለት ነው በአጭሩ:: አንዱ ቁም ነገር ይኼ ነው::

አሁን በተካሄደው ውይይት ይኼ ጉዳይ የመነሣቱ ጠቀሜታ ምንድን ነው? ለምን ይጠቅማል? ከተባለ፥ አንድ ነገር አለ:: አዲስ ነገር ስንገነባ፥ የነበረውን ነገር ስንተው ለምንድን ነው የምንተወው? ምክንያት ሳይኖረን ልንተወው ነው እንዴ? ለምሳሌ:- የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ተደርጎ ቆየ፤ አሁን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተውነው፤ ለምንድን ነው የተውነው? ምክንያት ሳይኖረን የምንተወው ከኾነ ጠቀሜታውን ወይም ጉዳቱን ሳናውቀው ነው የምንተወው ማለት ነው:: ስለዚህ መነሣት አለበት:: ሁለተኛ፥ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የዜጎች የእምነት ነጻነት ሙሉ ነው ወይ? የፈለገውን የማመን፤ አሁን ለምሳሌ:- በአውሮፓም በአሜሪካም ሄደን የእምነት ነጻነት ገደብ ስለሌለበት እጅግ በጣም የሚጠሉትን ኮምኒዝምን የሚያምን ሰው «ኮምኒዝም ነው ትክክለኛው» ብሎ የማመን መብት አለው:: የሚከለክለው የለም:: መብት በተሟላ ሁኔታ በተከበረ ልክ ዜጎች ይረካሉ፤ ዜጎች በረኩ ልክ አገራቸውን ይገነባሉ:: ራሳቸውን ይገነባሉ:: ይህን ጠቀሜታ ለማየት ጉዳዩን ማንሣት የግድ ነው:: አለ በለዚያ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ገብተን ስለ ሃይማኖት መብት፥ ጠቀሜታ ሌላም ነገር ሳናነሣ ከሄድን አገባብ አይሆንም:: እንዲያውም ሌላም ነገር ተነሥቶ ነበር፥ ብነግራችሁ..... «ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ናቸው ትላለህ፤ ግን የቤተ ክህነቱ መሪዎች ግን የኢሕአዴግ ካድሬዎች አይደሉም ወይ?» የሚል ነገር አንሥቷል:: እኔ የመለስኩት ምንድን ነው..... «ልክ አይደላችሁም፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በሌላም ሃይማኖት ውስጥ የኢሕአዴግ ፖለቲካ የሚጥመውና የሚ ደግፍ ሰው ሊኖር ይችላል፤ የኢሕአዴ ግን ፖለቲካ ደግሞ የማይደግፍና የማይቀበል ሰው አለ፤ ሁሉም ዓይነት ሰው ነው እዚያ የሚኖረው፤ በእምነቱ ሄዶ ነው እንጂ የሚገናኘው በፖለቲካ አቋሙ አይደለም:: ከዚህ ውጭ ቤተ ክህነቲቱ፥ አባታችንም፥ ጳጳሳቱንም ቢሆን እኔ የማውቀው ቤተ ክርስቲያናችን ለሰላም፣ ለልማት፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ሲጥሩ ነው የማውቀው እንጂ የኢሕአዴግን ፖለቲካ የኢሕአዴግ ካድሬ ኾነው ሲያራምዱ አላውቅም ብዬ ሁሉ አስረድቼአለሁ:: አሁን እንግዲህ ይህ የማይጥማቸው ሰዎች ይኖራሉ:: ምክንያቱም ሌላው የሚጥማቸው ስለኾኑ:: ይህ ደግሞ ሁሉም ጋር የሚያጋጥም ነገር ነው::

ሐመር:- እርስዎ ባነሡት ሐሳብ መለስ ብለን ብንነጋገር፥ ለምሳሌ:- «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ቦታ ለብዙ ዘመን ቆይታ ሳለ የኖረችውን ያህል ሃይማኖቱን አስፋፍታ የብዙዎች ለማድረግ አልቻለችም:: እንዲያውም ከእርስዋ በኋላ የመጡቱ ብዙ ተከታዮችን አፍርተዋል» ብለዋል:: ይህ እንግዲህ በሌላ አነጋገር ቤተ ክርስቲያናችን አንድ ሕዝብ ወይም ወገን አስተምራ ስታበቃ ውሳኔውን ግን ለራሱ ፈቃድና ነጻነት የመተው አንጻች የዴሞክራሲ ጠረን ነበራት አያስኝም ወይ? በዚህ ረገድ በሌሎች ወገኖች ያለውን ልምድ ብናይ ወደ አንድ አካባቢ ገብተው ሲያስተምሩ የተለያዩ ሰብአዊና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎችን ተጠቅመው ሰዎችን ወደ እነርሱ ይገቡ ዘንድ የማገበር ዝንባሌ አላቸው፤ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያን ወገን ለራሱ ውሳኔ አይተዉትም:: ከአገራችንም ውጭ፥ እስልምና በመካከለኛው ምሥራቅ፣ ካቶሊክ በደቡብ አሜሪካ፣ በአፍሪካ፣ በሩቅ ምሥራቅ የተስፋፋበትን መንገድ ብናይ ከዚህ የተለየ አይደለም:: በአገራችን ግን ከጥንት ጀምሮ በአብዛኛው ማለት ይቻላል ኦርቶዶክሳውያን ሐዋርያት፣ መምህራን፣ መነኮሳት፣ ባሕታውያን ከዳር ዳር ተሠማርተው ባስተማሩበት፣ የእምነት ተቋማት በተተከሉበት ጊዜ ሁሉ ሁኔታው የተረጋጋ መልክ ነበረው:: እርስዎ የመጀመሪያው ሂጅራ ብለው በገለጹበት መንገድ ሙስሊሞች ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ የተቀበላቸው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ነበር:: እነርሱም ቆይተው ከመግባባት የተነሣ በቤተ መንግሥት ውስጥ እስከ ጋብቻ የደረሱበት ሁኔታ ነበር:: በአንጻሩ ከጥንት ጀምሮ ዛሬም ድረስ በአንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ሌላ እምነት ዘልቆ እንዳይገባና እንዳይስፋፋ እየተከላከሉ ነው ያሉት::

በቤተ ክርስቲያናችን የነበረው አመለካከት በውይይቱ ላይ እንደ ተነገረው ወይም በሌሎች እንደ ኾነው ቢኾን ኖሮ ዋና ዋና የሚባሉቱን እምነቶች አቆይተን በየጊዜው የመጡትን አካባቢያዊና ልማዳዊ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እምነቶች እንኳ ለምስክርነት ይገኙ ነበር ወይ? ቀደም ሲል <ከ100 እና 200 ዓመታት በፊት የኦርቶዶክስ ክርስትናን በተለያዩ ግዛቶች ስለ ማስፋፋት ዘመቻ> ሁኔታ ሲጠቅሱ.....

አቶ ተፈራ፡- አይ፥ ከዚያም በፊት ነው....

ሐመር፡- አዎ፥ ከዚያም በፊት /በተለይ በ14ኛው መ.ክ.ዘ/ በርካታ አካባቢያዊና ልማዳዊ እምነቶች ተስፋፍተው ነበር፤ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ለማስተካከል በይበልጥ ጥረት ያደረገችው ከኃይል ይልቅ መምህራኗንና ካህናትዋን በአገልግሎት በማትጋት፣ የትምህርት አድማስዋንና የማስተማርያ መንገዶቿን በማስፋፋትና በማጠናከር ነበር። በነገሥታቱ ኃይል ላይ ሳትመሠረት በመነኮሳት ዋና በባሕታውያኗ አማካይነት ቀድማ የሄደችባቸው በርካታ ሁኔታዎች ነበሩ። ከተባለው ነገር አንጻር ይህን እንዴት ነው የሚያዩት?

በሌላ በኩል «ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኢሕአዴግ ፖለቲካ የሚጥመውም ኾነ የማይጥመውና የማይደግፈው አለ፤ ያም መብቱ ነው፤» ብለውናል። ከዚህ ጋር አያይዘን የምናነሣልዎትና ይበልጥኑ አጠያያቂ የኾነው ንግግርዎ ግን «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምክህተኞችን አንድነት የምትሰብክ የነፍጠኞች ምሽግ ናት» ብለዋል የሚለው ነው። ምናልባት ይህ አባባል ከክርስቲያዊ ትውፊቷ፥ ከታሪኳ በአጠቃላይ ከአስተምህሮዋ ጋር ከኾነ ተያይዞ እየተሰጠ ያለው፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሃይማኖት ተቋም፥ ያ አንድነት በምንም መልኩ ይተርጎም መለያየትን እንድትሰብክ ይጠበቃል ወይ? በመሠረቱስ <ነፍጠኘነትና ትምክህተኘነት> ከሃይማኖትና ከሃይማኖተኘነት ጋር እንዴት ነው ተገናኝቶ የሚታየው?


አቶ ተፈራ፡- ከመጨረሻው ጥያቄ ልነሣና፥ አሁን እንግዲህ ወደ ፖለቲካ ውይይት አይደለም የምንሄድ ያለነው። ... ነፍጠኛ ምን ማለት ነው፤ በአንድነት ነው በሌላ ጥያቄ ነው የሚለውን ራሱን በቻለ መልኩ መወያየት እንችላለን። በአጭሩ ግን እኛ የነፍጠኛው ሥርዓት የምንለው በዚህች አገር የነበረውን ዴሞክራሲያዊ ያልኾነውን ሥርዓት ነው። ዴሞክራሲያዊ ያልኾነ ስንል ደግሞ ምን ማለት ነው ከተባለ ብዙ መለኪያ እናወጣለትና በዚያ መለኪያ ልንመዝነው እንችላለን፤ አንዱ መሠረታዊ ቁም ነገር ይህ ነው።

የነፍጠኛው ሥርዓት ራሱን የቻለ ሥርዓት ነው። በእኛ አመለካከት ለየትኛውም እምነት የበጀ ሥርዓት አይደለም። ለየትኛውም... ለየትኛውም ... የበጀ አይደለም። ሌላው እንግዲህ የምናነሣው በማንኛውም አገር ላይ አንድ ፖለቲካዊ ሥርዓት ለሃይማኖቱ ችግር የሚፈጥርም፥ ችግር የማይፈጥርም ሊኾን ይችላል። ስለዚህ አሁን እዚያ ዝርዝር ውስጥ አንገባም። በሌላም አገር ቢኾን ለሃይማኖቱ በነጻነት መንቀሳቀስ፣ ተቀባይነት ማግኘት ፖለቲካዊ ሥርዓት እንቅፋት የኾነበት ጊዜ የለም ብለን ልናስብ አስቸጋሪ ይምስለኛል። ሌላው አሁን ጥሩ ያነሣችሁት ምንድን ነው... በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነበረች አልነበረችም፤ የሚለው ነው። ኅብረተሰቡ እንደ ኅብረተሰብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አልነበረውም፤ ዴሞክራሲያዊ ነበር የሚል ኀበዝ ይምጣ። ፖለቲካዊ ሥርዓቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊፈጥር በማይችልበት ጊዜ፤ የፈለገ ተቋም በእኛ አገር ውስጥ ተነጥሎ ብቻውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊመሠርትልን አይችልም። በጥቅሉ «በዚህ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አልነበረም» የሚለው ላይ እንስማማ የለ፤ በርግጥ «አሁንም የለም የሚሉ አሉ» ግን አብዛኛው ሰው በአጭሩ አሁን የሚግባባው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምንድን ነው በሚለው መመዘኛ አሁን ከድሮው ጋር ሲነጻጸር በዚህ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ተጀምሯል፤ የሚያጠያይቅ አይደለም፤ በእኔም ኾነ በብዙ ሰው አቅዋም እንደዚያ ይመስለኛል። የማይስማሙም ይኖራሉ።

በዚህ ሁኔታ የተለየ ነገር በደግም በመጥፎም ለቤተ ክርስቲያኒቱ ማንሣት አይቻልም። ግልጽ ነው! ..... ቤተ ክርስቲያኒቱን ለብቻ ወስዶ ምን ነበረ ጥሩ፤ ምን ነበረ ድክመቱ የሚል ራሱን የቻለ ብዙ ነገር ሊነሣ ይችላል። አሁን ለምሳሌ እኔ ራሴ ደስ የሚለኝ፥ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማሻሻል የጀመረችው፡- ብዙ ነገሮች አሉ። የዛሬ አምስት መቶ ዓመት ከዚያም በላይ፥ በነገራችን ላይ 100፥ 200 ዓመት ብቻ አይደለም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት መስፋፋት የጀመረው፥ ለረጅም ጊዜ እንደ ኾነ ግልጽ ነው፤ ይኸ በኾነበት ሁኔታ አሁን እያሻሻለችው ያለችው ሁኔታ፥ በተለያዩ ቋንቋዎች መጻሕፍትን ማዘጋጀት፣ በተለያየ ቋንቋ ሰበካ ማካሄድ፣ እርሱ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ብሔሮች የሃይማኖት መሪዎችን መሾም መሻሻል አይደለምን? ከዚህ የበለጠ መሻሻል ማድረግ እንደ ምትችልም እገምታለሁ። ከዚህ በፊት ግእዝን ለማያውቅ ሰው በግእዝኛ ቢነገረው እንዴት ነበረ የሚሰማው? ኦሮምኛ ብቻ ለሚችለው ሰው በአማርኛ ቢነገረው እንዴት ነበር የሚሰማው?

በንጽጽር ብናይ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት፥ምናልባት ተሳስቼ ከሆነ እታረማለሁ ፥ ሰበካን በኦሮምኛ ቀድሞ የሰበከ፥የገለጸ ነው። ተሳስቼ ሊሆን ይችላል፤ እኔ እስከ ማውቀው ድረስ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ የሚፈልገውን ሃይማኖት በሚሰማው ቋንቋ፣ በሚያነበው ጽሑፍ ሲቀርብለት፣ ለጠቅላላ ሥራውና ሁኔታው በሚያመቸው መንገድ ሲቀርብለት ደስ ይለዋል። ዛሬ እንኳ፥ በመንገድ ስመጣ የሰንበት ተማሪዎችን እያየሁ ነው የመጣኹት፤ በጣም ደስ ይላል። ሴቶችም ወንዶችም ናቸው የሚታዩት፤ ሴቶች ልጆችም ከበሮ ይዘው እየመቱ ነው። እኛ ድሮ ልጆች ኾነን ወደ ቤተ ክርስቲያን በምንሄድበት ጊዜ ሴት ልጅ ከበሮ ይዛ አትመታም ነበር። የሰው ልጅ ምን ጊዜም መሻሻልና ወደፊት ማየት ነው ያለበት። እና ይኼ መሻሻል ለምንድን ነው የተደረገው? ባይሻሻል ኖሮ ችግር ነበረው። ሲሻሻል የበለጠ ጥሩ ነው እየተባለ ነው። በዚህ ሒሳብ ነው መታየት ያለበት። ከዚህ ውጭ እንግዲህ .... «ይኼ የነፍጠኛ መሸሸጊያ.....» ምናምን ስለሚለው ሁሉም ዓይነት ፖለቲከኛ እዚያ ሰፈር ሊኖር ይችላል፤ ምን ጥያቄ አለው። በእኛ አስተሳሰብ የትኛውም ሃይማኖት ላይ፥ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ብቻ አይደለም፥ የትኛውም ሃይማኖት ላይ «የኢሕአዴግ ፖለቲካ ይጥመኛል» የሚል ሰው፥ የሃይማኖቱ ተከታይ ይኖራል፤ «የኢሕአዴግ ፖለቲካ አይጥመኝም» የሚልም እንዲሁ ይኖራል። አሁን ኢሕአዴግ <ነፍጠኛ> የሚል ቋንቋ ይጠቀማል በፖለቲካትን ተናው፥ ይኼን ደግሞ «መስማት አልፈልግም» የሚል ሰው በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነትና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ አይደለም በእስልምናም፣ በካቶሊክም ፣ በፕሮቴስታንትም የሚወድም የሚጠላም አለ። ስለዚህ አንዱ ብቻ ተለይቶ የሚወስድበት አይደለም።

ባለፉት ታሪኮች ከወሰድን ግን <የመንግሥት ሃይማኖት ማን ነበር?> ቢ



አራቱ ቅዱሳን ነገሥታት፡- ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ቅዱስ ሐርቤ/ገብረ ማርያም ፣ቅዱስ ላልይበላ፣ ቅዱስ ነአኵቶ ለአብ /ከግራ ወደ ቀኝ/



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ባል የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ብንል ውሸት ይሆናልን? ሲሶ ሥልጣንና ሲሶ ሌላም ሌላም ነገር..... ሌላው ሃይማኖት ይህ አልነበረውም:: ይህን ታሪክ ስንወስድ ምንድን ነው የሚነግረን፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ መንግሥት በሚወስደው ጥሩና መጥፎ ርምጃ አብራ እንድትታይ ያደርጋታል:: ብንወድም፥ ብንጠላም:: ይህን እውነተኛ ታሪክ የዛሬዎቹ ወጣት ምሁራን ማወቃቸው ጉዳቱ ምንድን ነው? በዚህ ስብሰባ ላይ ለምን አነሣኸው የሚባለውን በተመለከተ.... ለምንድን ነው የማይነሣው? የማይነሣበት ምክንያት እኮ ነው ሊነገር የሚገባው:: ለምንድን ነው በታሪክ መጻሕፍት የሚጻፈው? በዚህ ሒሳብ ነው መታየት ያለበት:: የሚቀራችሁ አንድ ሁለት ጥያቄዎች ካሏችሁ....

<u>ሐመር</u>:- «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምክህተኞችን አንድነት የምትሰብክ የነፍጠኞች ምሽግ ናት» የሚለውን አነጋገር በራሱ ብናይ እርስዎ እንዳሉት «ካለፈው ታሪክ አንጻር ብቻ» ተወስኖ የተነገረ ነው ወይ? ክቡር ሚኒስትር፥ ይቅርታ ያድርጉልንና፥ እዚህ ላይ ርግጠኛ መሆን አለብን:: ያም ኾኖ ካለፈው ታሪክ ጋር ብቻ የተጠቀሰ ቢኾን እንኳ በጉዳዩ ላይ ከመንግሥትነትና ከመንግሥት ሥልጣን ጋር ተያይዘው ሊታዩ የሚችሉቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት ወይ? ......

<u>አቶ ተፈራ</u>:- የኢሕአዴግ ፖለቲካ የድሮ ታሪክ እኮ አይደለም:: አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ አይደለምን?

<u>ሐመር</u>:- አዎ!

<u>አቶ ተፈራ</u>:- አሁን የኢሕአዴግን ፖለቲካ የሚቃወም ሰው የትኛውም ሃይማኖት ውስጥ ይኖራል:: ኢሕአዴግ የሚያራምደውን ፖለቲካ የሚቃወምም የሚደግፍም በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ ይኖራል:: አይደል እንዴ.....

<u>ሐመር</u>:- እኽ.....

<u>አቶ ተፈራ</u>:- ስለዚህ እዚህ ቦታ ላይ ነው የሚገኘው ብሎ ለይቶ አንድ ቦታ ላይ ወስኖ ማስቀመጥ ይቻላል ወይ? አይደለም....

<u>ሐመር</u>:- አይቻል ይሆናል..... ለማለት የፈለግኹት፥ ለምሳሌ:- ከታሪክ አኳያ ብቻ የዮዲት ጉዲትንና የግራኝ አሕመድን የ40 እና የ15 ዓመት የወረራ ዘመናትን /እንደ ቅደም ተከተላቸው/ መመልከት እንችላለን:: ሌሎችም ከመንግሥትነትና ከመንግሥት ሥልጣን ጋር በተያያዘ በወረራም ይሁን ራሳቸውን በማስፋፋት የተነሡ ነበሩ:: ስለዚህ የተባለውን ችግር ከዘመኑ አኳያ ለቤተ ክርስቲያናችን ልዩ መገለጫ አድርጎ፥ ወስኖ መናገር የሚቻል አይመስለኝም:: በሌላ በኩል በውይይቱ ላይ በእርስዎ በኩል እንደ ተነገረ የሚሰማውና በዚህ ቃለ ምልልሳችን ይበልጥ ማጥራት የፈለግነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከብሔር አንጻር ወስነው:- «የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የአማራና የጉራጌ ብሔር ነው» ብለዋል የሚለውን ነው::

<u>አቶ ተፈራ</u>:- እንግዲህ በዚህ አጋጣሚ ስላገኛችሁኝ በጣም ብዙ ጥያቄ ልትጠይቁኝ እንደ ምትፈልጉ ይገባኛል:: ነገር ግን የያዝነው ሰዓት ስላለቀ ነው የምንለያየው... ዋናው ቁም ነገር፥ ስላለፈው ታሪክ ብቻ አይደለም የምናወራው:: ያለፈው ታሪክ ለዛሬ ምን ተረፈን ነው፤ ታሪክ እኮ ዝም ብሎ ስላለፈ አይደለም የሚወራው፤ ለዛሬ ምን ጥሩ ነገር፥ ምን ችግር አስተላለፈ ነው፤ ሁለተኛ:- የእነ ግራኝ አሕመድ ዘመቻም በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ታሪክ ውስጥ ይታወቃል:: በተመሳሳይ የሌላውም ይታወቃል:: ሁሉም ይታወቃል:: አሁን ጥያቄው የእስልምና ሃይማኖት በኢትዮጵያችን ውስጥ የመንግሥት ሃይማኖት ኾኖ አያውቅም:: በዴሞ ክራሲያዊ ሥርዓት:- የመንግሥት ሃይማኖት የሚባል ነገር አይኖርም፤ መንግሥትና ሃይማኖት ይለያል፤ ዴሞክራሲያዊ በኾነው ሥርዓት ይለያል፤ አሁንም 'ኮ በዓለም ላይ አለ:: ለዚህ ንጽጽሩ ያለፈውን ካላየን የዛሬውን ማወቅ አንችልም:: በሌላ በኩል በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የእያንዳንዱ ዜጋ መብት እኩል ይከበራል:: ስለዚህ ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል መብት ይኖራቸዋል:: ይኽ መብታቸውን እኩል ማስከበር ለየእምነቱ በነጻነት መራመድ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: ነጻ ኾኖ ስለ ሚንቀሳቀስ:: ከመንግሥት ጋር ደርቦ ለመውቀስ ለሚፈልግም አይኾንም:: በዚህ ዐይን ነው የምንነጋገረው እንጂ ስለ ነፍጠኛው ሥርዓት ስናወራ የድሮ ታሪክ ብቻ አውርተን የምንተወው ጉዳይ አይደለም:: በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ታሪክ ውስጥና አሁንም የነፍጠኛው ሥርዓት ጉዳይ ቦታ አለው:: በዚህ ሒሳብ ነው.... ዞሮ ዞሮ የነገሩ ሁሉ ማጠንጠኛው፥ አትድከሙ፥ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና በፀረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ የሃይማኖትን ሚናና ልዩነት ማየት የግድ ይላል:: የመጨረሻ ጥያቄ.....

<u>ሐመር</u>:- «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የነፍጠኛው የአማራና የጉራጌ ሃይማኖት ብቻ ነው» ብለው መናገርዎን .......

<u>አቶ ተፈራ</u>:- የአማራና የጉራጌ የሚባለውን ደግሞ ከተመቻችሁ በሌላ ጊዜ እንወያያለን፤ የሚቀላችሁ መጽሐፍ አለ፤ መጽሐፉን ሄዳችሁ ማንበብ ነው::

<u>ሐመር</u>:- ይህን የመጨረሻ ጥያቄአችን ቢያደርጉልን ክቡር ሚኒስትር....

<u>አቶ ተፈራ</u>:- የለም፥ የለም በጣም አመሰግናለሁ፥ ፕሮግራም ስላለኝ ነው፥ አንተ ጥያቄ እየጠየቅኸ መልስ ሳይሆን የምትፈልገው ለማሳመን ነው የምትሞክረው.....

<u>ሐመር</u>:- ክቡር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአቅም ግንባታ ሚኒስትር አቶ ተፈራ ዋልዋ ጊዜዎትን ሰጥተውን ስላደረግነው ቃለ ምልልስ ከልብ እናመሰግናለን::

**ነገረ ድኅነት** ... ከገጽ ፱ የዞረ

ያስፈልጋል::

ከዚህ በኋላ ካህኑ በዐቢይ ዜማ አሰምቶ:– «አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፤ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ በህልውና አንድ የሚሆን አብ የተለየ የተመሰገነ ነው:: ከተወላዲነት ከሠራጺነት ውጪ ነው:: ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ በህልውና አንድ የሚሆን ወልድ የተለየ የተመሰገነ ነው:: ከወላዲነት ከአሥራጺነት ውጭ ነው:: ከአብ ከወልድ ጋር በባሕርይ በህልውና አንድ የሚሆን መንፈስ ቅዱስ የተለየ የተመሰገነ ነው:: ከአሥራጺነት፣ ከተወላዲነት፣ ከወላዲነት ውጭ ነው፤» በማለት የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት በመመስከር ምስጋናውን ይጀምራል::

ምክንያቱም የማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ መነሻ እግዚአብሔር ነው:: በተለይም የአንድነትና ሦስትነት

መገለጫ የሆነው ከላይ የተጠቀሰው ስም የሥራዎች ሁሉ መጀመሪያ ነው:: ቅዱሳን ሐዋርያት ለትምህርተ ወንጌል ወደ ዓለም ዳርቻዎች ሲላኩ የሥራ መጀመሪያቸው ይህ የአንድነትና የሦስትነት ስም ነበር:: «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው.. ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው::» /ማቴ.28፥19/::

ይህ ስም ውኃውን ወደ ማየ ገቦነት ይለውጣል:: ይህ ስም ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት ያደርጋል፤ ይለውጣል፤ ይቀድሳል፤ ያነጻል:: በመሆኑም ካህኑ ይህን ልዩ ስም በመጥራት፣ በማመስገንና በመመስከር የምስጋና ሥርዓቱን ይጀምራል:: በጸሎተ ቅዳሴው እየተሳተፉ በውጭም በውስጥም በአንቃዕድዎ ልቡና በሰቂለ ኅሊና ያሉ ምእመናንም ይህን የካህኑን የምስጋናና የምስክርነት ቃል በመቀበል:- «በአማን አብ ቅዱስ፣ በአማን ወልድ ቅዱስ፣ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፣ ንጹሕ፣ ክቡር፣ ጽኑ፣ ልዩ የሚሆን አብ በእውነት ወላዲ አሥራጺ ነው:: ንጹሕ፣ ክቡር፣ ጽኑ፣ ልዩ የሚሆን ወልድ በእውነት ተወላዲ ነው:: ንጹሕ፣ ክቡር፣ ጽኑ፣ ልዩ የሚሆን መንፈስ ቅዱስ በእውነት ሠራጺ ነው::» በማለት የካህኑን የምስጋናና የምስክርነት ቃል በመቀበል የምስጋናና የምስክርነቱ ተሳታፊ ይሆናሉ::

ወደ ገጽ ፳፫ የዞረ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት የነበረ መኾኑ አያስወቅስም»

/ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ/

## « በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለ ዕውቀት ያልተገባ ነገር የተናገሩ ካሉ ይቅርታ ሊጠይቁ አልያም በተናገሩት ላይ ማብራሪያ ሊሰጡበት ይገባል:: »

/ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የሰሜን ምዕራብ ሸዋ ዞን ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ/



ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ሊቀ ጳጳስ

ጥቂት በማይባሉ አገሮች የመንግሥትና ብሔራዊ ሃይማኖት አለ:: ዛሬም ቢሆን ወደ ሮም- ቫቲካን ብንሄድ ብሔራዊ ሃይማኖት ካቶሊክ ነው:: ሳዑዲ ዐረቢያ፣ ኢራን ብንሄድ ብሔራዊ ሃይማኖት እስልምና ነው::: አንዳንድ ሰዎች ለምንድን ነው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ብሔራዊ ሃይማኖት ሆና ኖረች ብለው የሚወቅሯት? ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት የነበረች መሆኗ ለምን ያስወቅሳል? ዛሬስ ቢሆን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ብሔራዊ ሃይማኖት ብትሆን የሚከፋ ነው ወይ?

«መንግሥት ሃይማኖት የለውም» ተብሎ ተነግሯል:: «ብሔራዊ ሃይማኖት የለም» ተብሏል:: «ጥንትስ ለምን እንደ ዚሀ አልሆነም» በማለት ስላልነበሩበትና ስላልተወለዱበት ጊዜ የሚቆጩ ሰዎች ካሉ እኛ እንደ እነሱ አንቆጭም:: ደግሞ እንደ መሰላቸው ካደረጉ በኋላ ከወቀሳ ውስጥ ምን ያገባቸዋል:: ለምን የመንግሥት ሃይማኖት ሆና ኖረች ብሎ «የነፍጠኛ ሃይማኖት» ማለትን ምን አመጣው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ነፍጠኛ የሚል የለ! በጣም ያሳዝናል እኮ!

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት የነበረች መሆኗ የሌሎችን መጨቆን በጭራሽ አያመጣም:: ሌሎች የራሳቸውን ሃይማኖት ይዘው ወደ ኢትዮጵያ እንግባ ሲሉ መች ተቃወመች? ሙስሊሞችን መች ተቃወመች? ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ጊዜ አክብራ አይደል እንዴ የተቀበለቻቸው? እኔ በነበርኩበት በፍልስጥኤም በቍርዓን አለ እየተባለ:- «ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ናቸው:: በስደታችንና በችግራችን ጊዜ የተቀበሉን ናቸውና በኢትዮጵያውያን ላይ እጆቻችሁን በጠብ እንዳታነሡ:: አክብራችሁ ተቀበሏቸው እንጂ» እያሉ ፍልስጥኤማውያን ሙስሊሞች እኔን አክብረው ነው የተቀበሉኝ:: እውነት እንደ ተባለው ጨቋኝ÷ ራሷን ብቻ የምትወድና ሌላው እንዳይስፋፋ የምትፈልግ ቢሆን ኖሮ ያኔ ሁሉንም ማገድና ማሳገድ ትችል ነበር::

«አገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው» ብሎ ያወጀው ማነው? ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ናቸው:: በዚህ እንኳን እኛም ቅር በመሰኘታችን ይህቺ አገር «የክርስቲያን ደሴት የምትባል ስትሆን እንዴት እንዲህ ያለውን ነገር ያመጣሉ» ብለን ነበር:: ነገር ግን ይኼ ለልዩ ልዩ እምነቶች ነጻነት ለመስጠትና በአገራቸው የጋራ ጉዳይ ግን እንዲተባበሩ ለማድረግ ይመስለኛል:: ቢያንስ በዚህ እንኳን የእምነት ነጻነትን የጀመሩት እርሳቸው ናቸው::

ለምሳሌ:– እኔ በሊቀ ጳጳስነት በነበርኩበት በሐረር÷በገጠርም ሆነ በከተማ እስላምና ክርስቲያኑ ጎረቤት ነው:: በአንድ ላይ ነው የሚኖረው:: አንዳንድ ችግር ፈጣሪዎች ቢኖሩም ጥቂት በማይባሉ ቦታዎች የጥንቱን አኗኗር ይዞ እየኖረ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግሥተኛና በልዩነቱ የሚቻቻል ደግ ሕዝብ ነው፤ ወንድማማች ነው::

ይህን የምላችሁ ከ1990 - 1993 ዓ.ም ድረስ የምሥራቅ ሐረርጌ ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ስለነበርኩ ካለኝ ተሞክሮ በመነሣት ነው:: እዚያ ሳለሁ በአንድ ገጠር ውስጥ የመቃብር ስፍራ ያለበት የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የሚርቃቸው ክርስቲያኖች ነበሩ:: ይህን የክርስቲያኖች ችግር ያዩት በአካባቢው ያሉ ሙስሊም ወንድሞቻቸው:- «ከእናንተ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ሟቹን ሳንቀብር እቤት አንውልም:: እንቅበር ስንል ደግሞ አስከሬን ተሸክሞ ያን ያህል ርቀት መጓዙ አስቸጋሪ ሆነ:: ከዚህ ችግር ለመላቀቅ ለምን በዚህ አካባቢ ቤተ ክርስቲያን አይሠራላችሁም የመቃብር ቦታስ ለምን አይሰጣችሁም?» ባሏቸው ጊዜ ክርስቲያኖቹ መልሰው «እንዴት አድርገን እንወጣዋለን?» ሲሉ መለሱላቸው:: «እኛ ቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ቦታ የለንም፤ እንሥራ እንኳን ብንል በቁጥርም አነስተኞች ስለሆን እንዴት አድርገን እንወጣዋለን» ሲሉ መለሱላቸው:: ሙስሊሞቹም «የመቃብርም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ቦታ እኛ እንሰጣችኋለን:: አስፈላጊውን ቁሳዊ ዕርዳታም እናደርግላችኋለን:: ወንድሞቻችን ናችሁ:: የኛ ችግር የናንተ÷ የናንተም ችግር የኛ ነው» በማለት ሐሳብ አቀረቡላቸው:: ይሄማ ከሆነ እሺ አሉ:: «እንግዲያውስ መሠረት እንዲጥሉላችሁ አባታችሁን ጥሩ» ተባሉ:: ጥሪ ደረሰኝና ሄድኩኝ:: ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድነት ሆነው ተሰልፈው ጠበቁኝ:: ለመቃብር የከለሉትንና ቤተ ክርስቲያኑ የሚሠራበትን ቦታ ካሳዩኝ በኋላ መሠረት ጣልኩኝ:: ድግስ ተደግሷል:: በአንድነት ነው የሚበሉት:: ወደ እኔም ቀርበው ግማሾቻችን ከክርስቲያኖች ግማሾቻችን ደግሞ ከሙስሊሞች ተውጣጥተን በሰበካ ጉባኤነት ተዋቅረናል:: እርስዎም መሠረት ስለጣሉልን እግዚአብሔር ይስጦት» ብለው ምስጋና አቀረቡልኝ:: በአባቶቻችን ጊዜ:- «ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች ከመሆናቸው የተነሣ በሃይማኖት ቢለያዩ እንኳን ሰርግ ሲሰረግ ለክርስቲያኖች አንድ ሰንጋ ለሙስሊሞች አንድ ሰንጋ በመጣል ወንድማማችነታቸውን ይገልጡ ነበር::» የሚለውን ታሪክ ተፈጽሞ ስላየሁ እግዚአብሔርን አመሰገንኹ::

ወሎ ውስጥ ብንሄድ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ገዳምን ጠብቆ የሚኖረው ሙስሊሙ ነው:: «ይህ ጥንታዊ ገዳማችን ነው፤ መዘጋት የለበትም» በማለት ጠብቀውት እንደ ሚኖሩ በዝና ሰምቻለሁ:: አሁን ደግሞ በእኔው ሃገረ ስብከት ውስጥ /ምሥራቅ ሐረርጌ/ በዐይኔ አሳየኝ:: በርቱ÷ የአባቶቻችን ሥርዓት ይህ ነው፤ አንድነታችሁን አጽኑ» ብዬ አጽናንቼ ለመሄድ ተነሣሁ:: የሄድኩባት መኪና በኋላዋ ክፍት ነበረችና የበግ ሙክት ጐትተው ሲጭኑ ድንገት አየሁ:: እናንተ ለራሳችሁ ምንም ምን የሌላችሁ እንዴት ለእኔ ሙክት ትጎትታላችሁ? በእግዚአብሔር÷ አውርዱ ብዬ ስጮኽ ክርስቲያኖቹ እንዲህ አሉኝ:- «አባታችን÷ እኛ አይደለንም፤ አባታችሁ ጥሪያችሁን አክብሮ መጥቶ ሲመለስ አንድ የሚያርደው ሙክት ይገባዋል ብለው የሰጡት ሼሁ ናቸው:: ስለሆነም አሁን እርስዎ ቢመልሱ እርሳቸው ይቀየሙብናል» አሉኝ:: ስጦታቸውን አክብሬ ሙክት ይዤ መጥቼ ለሃገረ ስብከቱ ሠራተኞች ካሳረድኩ በኋላ ለእነርሱና ለአካባቢው ሰዎች ትምህርት ሰጥቼበታለሁ:: በዚህ



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ጉዳይ ፍልስጥኤም ድረስ ሰብኬበታለሁ:: ኢትዮጵያውያን እንዲህ ተስማምተው የሚኖሩ ሰዎች ናቸው:: ይህቺ ቤተ ክርስቲያን አንድነትን ሰበከች ተብሎ የምትወቀስ ከሆነ ዛሬ ምን ለማድረግ ታስቦ ነው? ይሄ ነው የሚገርመኝ፤ ተነጣጥሎ በሰይፍ እንዲቀራደድ ነው እንዴ የሚፈለገው? አሁንም አንድነት ያስፈልጋል፤ አንድነነት ከሌለ መንግሥት የለም፤ ኢትዮጵያ አንድነትን ትፈልጋለች:: አሁንም በየክልሉ ያለው አደረጃጀት ለሥራ እንዲያመች ተብሎ እንጂ «በሰይፍ እንሰነጥቅሃለን» ቢሉት እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ ነው:: አንድነትን መስበክ ትምክህተኝነት ወይም ነፍጠኝነት አይደለም:: እንዴ÷ ያለ አንድነት ምን መጽናት አለ? ያለ አንድነት ምን ሃገር አለ? የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ በመሆኑ አይደል እንዴ ወራሪን አሳፍሮ የመለሰው? አንድነት ከሌለማ በዚያ በተገነጣጠለው ገብቶ ቅኝ ተገዥ ያደርገዋል::

ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ ሕዝቡ የሚጠቀምበትን የሃይማኖት ክፍፍል ሳያደርግ ተከባብሮ የሚኖርበትን ትምህርት ስታስተምር ቆይታለች:: ወደፊትም ይህን ከማስተማር አትቆጠብም::

ደግሞ የአገር ወሰን እንዳይታለፍ÷ ነጻነት እንዳይገፈፍ÷ ድንቁርናና በቅኝ አገዛዝ መረገጥ እንዳይመጣ፤ ታቦት ተሸክማ ከአርበኞች ጎን በመሰለፍ ወደ እግዚአብሔር ትጮኽ ነበር:: «የኢትዮጵያን አንድነትና ነጻነት ጠብቅ» ማለት ጨቋኝነት ነው እንዴ? ይኼ አነጋገር በእውነት ያሳዝነኛል::

**«ሥልጣንን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለተቀበሉ ሰዎች ታዘዙ» ማለት ኃጢአት አይደለም::**

አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ እንደ ምሰማው:- «ቤተ ክርስቲያን÷ መሪዎች የእግዚአብሐር እንደራሴዎች ናቸውና ስገዱላቸው÷ አምልኳቸው ብላ የሰበከችበት ጊዜ ነበረ» በማለት በሐሰት ይናገራሉ:: በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል «ለገዢዎች÷ ለባለሥልጣናት ታዘዙ» ይላል:: ይህን አምላካዊ ቃል መነሻ አድርጋ «እግዚአብሔር የሥልጣን ሰይፍ ያስታጠቃቸው ያለ ምክንያት አይደለምና ልትታዘዙ ይገባል:: ምክንያቱም ሥልጣን የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነውና::» እያለች ታስተምራለች::

በመሆኑም «ሥልጣንን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለተቀበሉ ሰዎች ታዘዙ» ማለት ኃጢአት አይደለም:: ይህም ሲባል «ባለሥልጣኖቹ ይጨቁኑ» ማለት አይደለም:: ጨቋኝ ገዥዎችንም ቢሆን:- «ለምን ትጨቁናላችሁ፡ የሕዝቡ እምባ እሳት ሆኖ ይበላችኋል:: ምክንያቱም ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳልና» እያለች ከመገሠጽ የበለጠ ምን ታድርግ? ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ከጨቋኞች ጋር አይደለም የተሰለፈችው:: ጨቋኞችን የምትዘልፍና የምትገሥጽ እንጂ:: «በትክክል ፍረዱ እንጂ፤ መድልዎ አታድርጉ» የምትል ቤተ ክርስቲያን ናት:: እኔ የማውቀው ይህን ነው:: ሰዎቹ በሐሰት ነው የሚመሰክሩባት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነገሥታቱን ተከትላ ሰው እንዲጨቆን ያደረገችበት ጊዜ የለም:: በመሠረቱ ነገሥታቱ እምነታቸው ክርስትና ነበር:: በግድ ከክርስትና ውጡ ተብለው አይሰበኩም:: በሃይማኖታቸው ጸንተው እንዲኖሩ እንጂ::

**«ቤተ ክርስቲያን ኩላዊት እንደ መሆኗ በሁሉም ቋንቋ ስታስተምር ኖራለች»**

በሐዋርያቷና ሊቃውንቷ ቅትልት /ተጋድሎ/ እስከ አገሪቱ ጠረፍ ድረስ ወንጌል ተሰብኳል:: የተሰበከውም በተለያየ ቋንቋ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስፋፋትና ሁሉን አቀፋዊነት ያልተገነዘቡ ሰዎች ተልእኮዋን ለማስተንኰል መጣደፋቸውን ሳይ በጣም አዝናለሁ::

ዛሬ በጥረትና በትግል ካልሆነ የቋንቋው ክህሎት አይገኝም:: የዛሬውን አያድርገውና ያኔ አባቶቻችን እነ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሰባ ሁለት ቋንቋ ተገልጦላቸው በየቋንቋው ያስተምሩ ነበር:: ከዕብራይስጥ፣ ከሮማይስጥ፣ ከዐረብ ወደ ግእዝ እየተረጎሙ ያሠራጩ የነበሩ የቀድሞዎቹ አባቶቻችን ናቸው::

አሁን በዘመቻ መልክ ልዩ ልዩ ተልእኮ ይዘው የመጡ «ሰባክያን» አሉ:: ገንዘብ ጭነው በሕዝቡ ደካማ ጎን በኩል እየገቡና ገንዘብ እየሰጡ ብዙ ሰው አግኝተው ይሆናል:: በዚህ መልክ ያገኙትን አገኙ እንጂ አሁንም ቢሆን ከ 45 ሚልዮን በላይ የሆነ ምእመን ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት::

እንዲያም ሆኖ ያገኘችውን በእኩልነት ነው የምታካፍለው:: መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባለው ቃል መሠረት ስትመጸውት እስላም ክርስቲያን አትልም:: ለዚህም «ቀኝ እጅህ የምትሰጠውን ግራ እጅህ አትወቅ» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል መመሪያዋ ታደርጋለች:: አንዳንዶቹ ግን ለተልእኳቸው እንዲመቻቸው «የእኛ እምነት ተከታይ» እያሉ ለመለየት ነው የሚሰጡት:: ምን አልባት በዚህ ምክንያት አንዳንድ ቦታ ላይ በርከት ብለው ቢታዩ አያስደንቅም::

**«ቤተ ክርስቲያን ለአገልጋዮቿ የተሰጠውን መሬት እያለማች ተልእኮዋን ስትፈጽም ኖራለች»**

መሬትን አስመልክቶ ለተነሣው ጥያቄ «የመስቀል መሬት፤ የሰሞንኛ መሬት» የሚባል ነበር:: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፎ የሚገኘውና ከዐሥር አንድ የሚለው ሥርዓት በተፈጻሚነት ደረጃ አልተለመደም ነበር፤ በሚገባም አልተሰበከም ነበር:: ነገር ግን በዚያ ፈንታ ካህኑ መሬት እያረሰ ራሱን እንዲያስተዳድር «የመስቀል መሬት፣ የሰሞንኛ መሬ» እየተባለ ተለይቶ ይሰጠው ነበር:: ካህኑ ሌሊት ሰዓታት ቆሞ ካደረ በኋላ ጠዋት በሬዎቹን ጠምዶ ሲያርስ ይውላል::

የቅዳሴ ሰዓት ሲደርስ ደግሞ በሬዎቹን ፈትቶ ወይም ለተተኪ ሰጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመጣ በኋላ ክርስትና አንሥቶ፣ ቀድሶና አቁርቦ ይመለሳል:: እስከ ዛሬ የቆየው የኢትዮጵያ ካህን አገልግሎት ይህ ነው:: ካህኑ በዘመኑ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የነበረውን የመሬት ሥሪት ተጠቅሞ ቤተ ክርስቲያን እንዳይዘጋና አገልግሎትዋ እንዲስፋፋ መከራውን እየተቀበለ ሠራ እንጂ «ቤተ ክርስቲያን ከነገሥታት ጋር አብራ ሲሶ መንግሥት በመያዝ ይህንና ያንን አድርጋለች» በሚባለው ሁኔታ አይደለም የኖረችው:: አገልጋዮቿ መከራ እየተቀበሉ ራሳቸውን ረድተው የሚኖሩ ናቸው እንጂ ከመንግሥት የሚያገኙት ነገር አልነበረም:: ቤተ ክርስቲያንም ብትሆን ለአገልጋዮቿ ካህናት በደመወዝነት የተሰጠውን መሬት እያለማች ተልእኮዋን ፈጽማለች::

**«እኔ በእነርሱ ፖለቲካ ውስጥ አልገባም፤ እነርሱም በእኔ ሃይማኖት ውስጥ መግባት የለባቸውም»**

...ሲኾን÷ ሲኾን አንድነትን አጠናክሮ:- «ይህቺ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ስትደክምና ብዙ አስተዋፅዖ ስታደርግ የኖረች ነች:: ዛሬም የተለያየ ሃይማኖት ያላችሁ ሁሉ ተባብራችሁ ለልማት ተሰለፉ:: የምንፈልገው ዳቦ ነው» ይባላል እንጂ «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነፍጠኞች ምሽግና ከጨቋኞች ጋር አብራ ሲሶ መንግሥት በመያዝ የኖረች ነች» እያሉ በመንቀፍ ምንም የሚመጣ ነገር የለም:: በእውነቱ በዚህ በኩል እኔ አስጠነቅቃለሁ::

እኔ እነርሱ ፖለቲካ ውስጥ አልገባም:: እነርሱም እኔ ሃይማኖት ውስጥ መግባት የለባቸውም:: «ሌላውን ሃይማኖት አትንኩ» እየተባለ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ሥርዓትን እንዲያንኳስሱና ያልተደረገውን ተደረገ እንዲሉ ማን ፈቀደላቸው? ይህ ሕዝብንና መንግሥትን የሚያጋጭ ነገር ነው::

በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለ ዕውቀት ያልተገባ ነገር የተናገሩ ካሉ ይቅርታ ሊጠይቁ አልያም በተናገሩት ላይ ማብራሪያ ሊሰጡበት ይገባል እላለሁ::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



«ኢየሱስ ክርስቶስ ካህን ወንጉሠ ሰላም ሞዐ አንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ፤ ከይሁዳ ነገድ የሆነው ÷ ድል የነሣው አንበሳ ኢየሱስ ክርስቶስ ካህንና የሰላም ንጉሥ ነው።» /ራእ.5÷5/

## «በሁሉም ነገር ፍጹም ነበርን ብለን መከራከር መቆም ያለበት ይመስለኛል»

ፍቅረ ሥላሴ ኣርኣያ
/ቢ.ኤ ዲግሪ በፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት/

**የመንግሥትና ሃይማኖት ግንኙነት /Separation of Church and State/ በተለይ በኢትዮጵያ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ እንዴት ይታያል?**

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ነው የምናየው። አንደኛው በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ሊኖር የሚችለውን ነገር ነው። ሁለተኛው ደግሞ በታሪክ ሂደት በአገራችን ውስጥ የነበረውን እውነት በተጨባጭ ሚዛናዊ ሆኖ መመልከት ነው። የአንድ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት /State religion/ መኾን በኢትዮጵያ የመጀመሪያ አይደለም። እንኳንስ በጥንቱ ዛሬም ቢሆን የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችን ብንወስድ በአብዛኞቹ ዘንድ እስልምና የመንግሥት ሃይማኖት ነው። ሠለጠኑ በሚባሉቱ አገሮችም በአንዳንዶቹ በሕገ መንግሥት ደረጃ በይፋ÷በሌሎቹም ከመጋረጃው በስተጀርባ ተመሳሳይ ነገሮች እንዳሉ የምናስተውለው ሐቅ ነው። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያን የተለየች አድርጎ መመልከት ትክክል አይመስለኝም። አንዳንድ ጊዜ የምሰማው ክርክር ኢትዮጵያን ከተቀረው ዓለም የተለየች መኾን ነበረባት የማለት አዝማሚያ ነው። የተለየች አልነበረችም፤ ልትኾንም አትችልም። ለረጅም ጊዜ ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት ኾኖ ቆይቷል።

በታሪክ እንደ ምንመለከተው አንድ ሃይማኖት የመንግሥት ሲኾን ደግሞ አብረው የሚመጡ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ:- በሀገሪቱ ፖለቲካዊ አመራር ውስጥ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። የኢራንን እስላማዊ ሪፐብሊክ ብንወስድ <theocracy> /ሃይማኖታዊ ሥርዓተ መንግሥት/ የሚባለው ዓይነት አመራር ከየትኛውም አገር በላይ ጎልቶ የሚታይባት ናት። በኢራን ለፖለቲካ ሥልጣን ምርጫ ይካሄዳል። በአብዛኛው ነገር ላይ የሚወስነው ግን የ<ሊቃውንት ጉባኤ> /Clerics Council/ የሚባለው ነው። የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የወሰኑትን ውሳኔ እስከ መሻር ድረስ ሥልጣን ያላቸው ናቸው። ይኸ ትክክል ነው እያልኩ አይደለም። ይሁንና እንዲህ ዓይነት ግንኙነትም ሊኖር ይችላል።

አንድ ሃይማኖት ብሔራዊ የመንግሥት ሃይማኖት ሲኾን ከሌሎች ይልቅ ለመንግሥት የቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል። ቅርበቱ ለቤተ መንግሥቱ ነው። በታሪካችን ውስጥ በኢትዮጵያ ዓይነተኛ በኾነ መልኩ የምንመለከተው ነገር ይህን ነው። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት /Official and State established Church/ ሲኾን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለረጅም ጊዜ ለቤተ መንግሥት ቅርብ ሆና ነው የኖረችው። ይህም በሀገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ ሚና እንድትጫወት አድርጓታል። ፖሊሲዎች ሲወጡ፣ ባለሥልጣናቱ ሲሾሙ ተጽዕኖ ለማድረግ ትችላለች። ከሌሎቹ ሃይማኖቶች የበለጠ ለመንግሥት ቅርብ ነበረች። እውነቱን ለመናገር ደግሞ የበለጠ /የተሻለ/ ተጠቃሚ ነበረች። የነበራትን ዕድል ያህል ተጠቅማለች ወይ? ይህ ሁለተኛና ሌላ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ከሌሎቹ በተሻለ ተጠቅማለች። ለምሳሌ÷ ከቤተ ክርስቲያናችን በዓላት ብዙዎቹ ብሔራዊ በዓላት ተደርገዋል። ይኼ አንድ ጥቅም ነው፤ የሚያስወቅስ ጥቅም ግን አይደለም፤ በመሬት ይዞታም ተጠቃሚ ነበረች። ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ በየአካባቢው የምታገኘው ልዩ ልዩ እገዛም ነበር። ይህ እንግዲህ የነበረው የግንኙነት ሁኔታ የወለደው ጉዳይ ነው። በታሪክ አጋጣሚ የእስልምና ሃይማኖት ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት ቢኾን ኖሮ ሁኔታው የተለየ አይሆንም ነበር። በዚህ መሰሉ ታሪክ ችግሩ የቤተ ክርስቲያን መጠቀም አይደለም። ለእርሷ ጥቅም ሲባል ሌሎች ተጐድተው ከሆን ነው። እውነቱን ለመናገር ጥቅማቸው /መብታቸው/ ያልተጠበቀላቸው ወገኖቻችን ነበሩ። ለምሳሌ ÷ሙስሊም ወንድሞቻችን በዓላቸውን ማክበር አለመቻላቸው ትክክል አልነበረም። ሆኖም ዘመኑ ከዚህ የተለየ ሁኔታ የሚፈጠርበት ተጨባጭ መነሻም አልነበረም። ስለዚህም ስሕተት የነበረ ቢሆንም በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ነበረብን ማለት ነው።

ከመንግሥትና ሃይማኖት ግንኙነት ጋር በተያያዘ ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዴሞክራሲያዊ ወይም ኢ-ዴሞክራሲያዊ መሆን ወይም አለመሆን ጋር ተያይዞ ሲነሣ እሰማለሁ። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት የነበረች መሆኗ ቤተ ክርስቲያኒቱ ኢ- ዴሞክራሲያዊና ያልሠለጠነች÷ ሀገሪቱም ኋላ ቀር ከመሆንዋ ወይም አለመሆንዋ ጋር የተያያዘ አይደለም። በብዙ አገሮች የታለፈበት መስመር ነው። ይህን የታሪክ ሂደት ያላለፉ ሀገሮች <New States> /በቅርቡ የተቋቋሙ መንግሥታት/ የሚባሉቱ አገሮች ናቸው። በብዛት የሚገኙትም በአፍሪካ አህጉር ነው። ለምን? አገሮቹ ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ተላቅቀው የፖለቲካ ነጻነታቸውንና ሀገራዊ ህልውናቸውን ያገኙት በ1950ዎቹ መጨረሻና በ1960ዎቹ ስለሆነ ነው። ያን ጊዜ ደግሞ የመንግሥትና የሃይማኖት መዋቅር መለያየት /Separation of State and religion/ በንድፈ ሐሳብም በተግባርም የተሞከረበት ጊዜ ነበር። ስለዚህ ቢያንስ መንግሥትንና ሃይማኖትን ለመለያየት÷ ብሔራዊና የመንግሥት የሚባል ሃይማኖት እንዳይኖር ሙከራ ያደረጉ አገሮች አሉ።

ነገሩን ለማጠቃለል በአንድ አገር የመንግሥትና ሃይማኖት መዋቅሮች በሦስት ወይም በአራት የተከፈለ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል። የመጀመሪያው እስካሁን እንዳየነው




© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት የሚኖርበት ሁኔታ ነው:: ያ ሃይማኖት÷ ክርስትና ወይም እስልምና ወይም ሌላ ሊኾን ይችላል÷ ለመንግሥት ድጋፍ ይሰጣል:: መንግሥትም እንዲሁ ለሃይማኖቱ ድጋፍ ይሰጣል፤ ይጠቃቀማሉ ማለት ነው:: ሌላው ደግሞ መንግሥትና አንድ የሃይማኖት ተቋም ባላንጣ የሚኾኑበት ሁኔታ ነው:: ይኽ እንደ ጊዜው /ለረጅም ወይም ለአጭር ጊዜ/ ሊኾን ይችላል:: አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ ባደረጉት ትግል አብያተ ክርስቲያናት ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገዋል:: ማለትም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፀረ ቅኝ አገዛዝ አቋምን በማራመድ የነጻነት ትግሉን ደግፈዋል:: ሦስተኛው ዓይነት የመንግሥትና ሃይማኖት ግንኙነት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እንደ ማኅበራዊ ተቋማዊ ኃይል /Social force/ የምትታይበትና ከዚያ አኳያ ሚናዋን የምትጫወትበት ሁኔታ ነው::

አንድ የሃይማኖት ተቋም ባለበት አገር ሊኖሩት የሚችሉትን ሚናዎች የሚወስኑት ታሪካዊ ወይም ማኅበራዊ ምክንያቶች ናቸው:: የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ውስጥ ያላትን ሚና ስናይ በአብዛኛው ከታሪካዊ ምክንያቶች ጋር የተያያዘ ነው:: በእኛም አገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ መንግሥት ውስጥ የነበራትን ሚና ስንቃኝ ከታሪካዊ ምክንያቶች ጋር የተያያዘ ነው:: ይህ ደግሞ በአገሪቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሚና እንድትጫወት አድርጓታል::

## ማን በማን ተጠቅሟል?

ይህን በተመለከተ እውነቱን እያስቀመጥን መሄድ አለብን:: በኢትዮጵያ ታሪክ መንግሥትና ሃይማኖት የነበራቸውን ግንኙነት በሁለት መንገድ ማየት ይኖርብናል:: ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት እንደ ሚያስቀምጡት:- ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት ጋር በነበራት ግንኙነት ሁለት ደረጃዎች ነበሯት:: የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያኒቱን ወክለው በአመራር ደረጃ በሚሠሩት ሰዎች በኩል የነበረው ግንኙነት /institutional linkage/ነው:: በሌላ በኩል በምእመኑና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት ነው:: በመንግሥቱና በአመራሩ መካከል በነበረው ግንኙነት አንዱ ሌላውን የመጥቀም ሁኔታ ነበር:: ለምሳሌ: - እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ ነገሥታቱን «ሥዩመ እግዚአብሔር» በማለት የምትቀባቸው /የምታነግሣቸው/ ቤተ ክርስቲያን ነበረች:: ይህ ደግሞ ለአገዛዝ ሥርዓቱ /regime/ ርዕዮተ ዓለማዊ መሣሪያ /Ideology/ ይሰጠዋል:: ሕጋዊነትን /legitmacy/ ያላብሰዋል /ያጎናጽፈዋል/:: የመንግሥት ፖለቲካዊ ሥልጣን ቅቡል የሚኾነው በምርጫ ሥርዓት አልነበረም:: ቤተ ክርስቲያን ስትቀባው ግን ቅቡል legitmate ይሆናል:: ቤተ ክርስቲያን ይህ ሚና ነበራት:: ሌላው ቀርቶ መሳፍንቱን በኃይላቸው አሸንፈው ሥልጣን የያዙት ዐፄ ቴዎድሮስ እንኳን ግንኙነታቸው ምንም ይሁን ምን ለመንገሥ በቤተ ክርስቲያኒቱ መቀባት አስፈልጓቸዋል:: ቤተ ክርስቲያን ነገሥታቱን በእጅጉ ጠቅማቸዋለች:: አይዲዮሎጂና ሕጋዊነትን ሰጥታቸዋለች:: ነገሥታቱ ህልውናቸውን የሚተረጉሙበት የመጀመሪያ መሣሪያ ሃይማኖት ነበር:: ተርጓሚዋም ቤተ ክርስቲያን ነበረች::

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት ምን ተጠቅማለች? አሁንም እውነቱን ለመናገር በአንጻራዊነት ሲታይ ከሌሎቹ የእምነት ተቋማት የተሻለ ጥቅም አግኝታለች:: ያገኘችውን ዕድል ወይም የነበራትን ቅርበት ያህል ተጠቅማለች ወይ ቢባል ትክክለኛው መልስ አልተጠቀመችም ነው:: ብዙ መሥራት÷ ብዙ ማግኘት ትችል ነበር:: ይህም በመሠረቱ /Potentially/ በመንግሥት ላይ ከነበራት ተጽዕኖ ይመነጫል:: በየትኛውም አገር ነገሥታቱ አንድን ሃይማኖት ተቀብለው የመንግሥት ካደረጉት ያ ሃይማኖት መጠቀሙ አይቀርም:: ስለዚህ መጠኑ ቢለያይም አንዱ ለሌላው ጥቅም ሰጥተዋል ብዬ አምናለሁ:: በነገራችን ላይ የአብዛኞቹ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ሁኔታ ተመሳሳይ ነበር:: መንግሥትና ሃይማኖትን ለመለያየት ረጅም ጊዜ ወስዶባቸዋል:: አሁንም ቢሆን በእርግጥ ተለያይተዋል ወይ? ብለው የሚጠይቁ ተመራማሪዎች አሉ:: ጥያቄው ውስብስብ ነው::

## የእነዚህ መጠቃቀም /አጠቃላይ ግንኙነት/ ቅሪት /legacy/ ምንድን ነው?

እንግዲህ አሁን ትልቁ ነጥብ ይህ ነው:: አሁን በተለያየ መንገድ የሚገለጸውን መደናገር /Confusion/ የፈጠረው የዚያ ውርስና <ቅሬታ> /legacy/ ነው ብዬ አምናለሁ:: ቀድሞም በደርግ ጊዜ ትልቅ መምታታትና መደናገር ነበር:: አሁንም ቢሆን አለ ብዬ አምናለሁ:: ደርግ መጀመሪያ ሲነሣ ፀረ ሃይማኖት ሆኖ ነበር የተነሣው:: ይህም እጅግ ዐላዋቂነት ነበር:: የኅብረተሰቡን ሥነ ልቡናዊ አስተሳሰብ (Psychic) ያለመረዳት ትልቅ ስሕተት ነበር:: ቆይቶም ቢሆን ይኽ ችግር ወዴት እንደ ሚወስደው በመረዳቱ ቢያንስ ወዳለመቃወም ነበር የመጣው:: ቀጥሎ ደግሞ በሃይማኖቱ አስተምህሮና መዋቅር ወደ መጠቀም መጣ:: በጊዜው መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን ብዙ ዓይነት ጣልቃ ገብነት የምናስታውሰው ነው:: ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱን ማኅበራዊ, ተቀባይነት በመረዳቱ ሊጠቀምባት መፈለጉን ያየንበት ነበር:: ቀድሞ ግን ምንም የማታስፈልግ÷ ሌኒን እንደ ሚለው <Opium of the People> /ሕዝብን ያደነዘዘች ናት/÷ «ሕንፃ አብያተ ክርስቲያኒቱን ሚዚየም እናደርጋለን» ነበር የሚለው:: በኋላ ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሕዝቡ ባሕል፣ ሥነ ልቡናዊ አስተሳሰብ /Psychic/ ጋር ምን ያህል እንደ ተቆራኘች ሲያስብ ወደ መጠቀም÷ እንደሻው ወደ ማድረግ /manipulate/ ተመለሰ:: ከደርግ በኋላ የመጣውን ኢሕአዴግ መራሽ መንግሥትን ስናይ ገና ከጅምሩ <መንግሥትና ሃይማኖት መለያየት አለባቸው> ብሎ መነሣቱን ነው የሚገልጸው:: «ዓለማዊ የመንግሥት ሥርዓት» /Secularism/ ነው መመሪያችን ነው የሚለው:: በዚህ ደረጃ የግብረ ገብ ትምህርት በትምህርት ቤቶች እንኳ እንዳይሰጥ እስከ መከልከል ነው የተኬደው:: ከዚህ አኳያ በ«ዓለማዊ የመንግሥት ሥርዓት» /Secularism/ እና መንግሥትን ከሃይማኖት በመለየት መካከል መደናገር ያለ ይመስለኛል:: የሕፃናት በሃይማኖታዊ ምግባር እየታነጹ ማደግን ዓለማዊ የመንግሥት ሥርዓትን ይጻረራል /anti secularism/ ማለት <Secularismን> በሚገባ መረዳት ነው ብዬ አላስብም:: ለዚህ የሚዳርገው መሠረታዊ ምክንያት የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ /ሃይማኖት በኢትዮጵያውያን ሕይወት÷ አስተሳሰብ ውስጥ ምን ማለት ነው የሚለውን/ በቅጡ አለመረዳት ይመስለኛል:: ለእኔ የትኛውም ሃይማኖት ቢሆን ወደ ጫና እና ማስገደድ እስካልወሰደው ድረስ ወይም አብዛኞቹ እምነቶች የሚጋሯቸውን እሴቶች አውጣጥቶ በግብረ ገብ ትምህርትነት ተቀርጾ በየደረጃው ማስተማር <Secularism>ን መቃወም አይደለም:: በመሠረቱ <Secularism>ን በ<anti religionism> ለመደገፍ መሞከር በአውሮፓም ተሞክሮ ያልተሳካ ነው::

## <ነፍጠኛነት> እና ቤተ ክርስቲያን

«ነፍጠኛ» የሚለው ቃል ከሃይማኖትና ከሃይማኖተኛነት ጋር ተያይዞ በተነገረበት አገባብ ትርጉሙ አስቸጋሪ ነው:: <መሣሪያ የያዘ÷ ባለ መሣሪያ> ማለት ከኾነ ምናልባት ሽጉጥ ያለው ካህን ሊኖር ይችላል:: ቤተ ክርስቲያን ግን <ታጠቁ÷ ተሰማሩ÷ ውረፉ> የሚል ፖሊሲ የላትም:: ይህ ፖሊሲ ነበራት ከተባለ ማስረጃ መቅረብ አለበት:: ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት እንደ መሆንዋ መንግሥታት ያወጡት የነበረውን የመስፋፋት ፖሊሲ ልትቃወም አትችልም ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥታቱ የምታስፈልጋቸውን ያህል መንግሥታቱም ለቤተ ክርስቲያን ያስፈልጓት ነበር::

ይህ ደግሞ በየትኛውም አገር የነበረ ጉዳይ ነው:: ለእኔ አስተማሪ ባልኾነ መልኩ ታሪክን አንሥቶ መወቃቀሱ መቃቃርን ከመፍጠር በቀር /የቤተ ክርስቲያንን መልካም ገጽታ የሚያጠፋ ስለሆነ/ ለመንግሥት ምን እንደ ሚጠቅመው አላውቅም:: በእምነት ከማይመስሉን ጋር አብረን በሰላምና በፍቅር እንኖራለን:: የእነርሱ በዓላት ሳይከበሩ መቆየታቸው አያስደስተንም:: ይህን ደግሞ በሂደት ተምረ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ንበታል፣ ከሚያጋጥመን ነገርና ከታሪክ ስሕተት:: ስለዚህ ሐሳቡ በተነሣበት መንገድ በመራመዱ የሚጠቀም ወገን ይኖራል ብዬ አላምንም::

ቀደም ብዬ እንደ ተናገርኩት ትልቅ መደናገር አለ:: ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ መንግሥታት ርእዮተ ዓለም/ideology/ ሰጥታ ነበር:: ይህ ርእዮተ ዓለም /ideology/ የመንግሥቱን ቅቡልነት /legitmacy/ ብቻ ሳይሆን <አገር ምንድን ነው?> ለሚለው፣ ስለ ሀገር ፍቅር፣ ስለ አንድነት ከምንም በላይ ትርጉም የሰጠችው ቤተ ክርስቲያን ናት:: ትምህርት ስትሰጥበትና ስትጠብቀው የቆየችው ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይህ ነገር በሕዝቡ ውስጥ ሠርጿል:: አሁንም ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን የምታራምደው አመለካከት ነው:: በመሠረቱ ከነበራት ታሪካዊ ሚና አኳያ ከዚያ ውጭ ልታስተምር አትችልም:: ከዚህ ውጭ /ተቃራኒውን/ ቤተ ክርስቲያን ታስተምር ማለት ታሪክን 'redue' ለማድረግ /እንደ ገና ለመሥራት/ እንደ መቻል ይቆጠራል:: ቤተ ክርስቲያን አንድነትን፣ ፍቅርን፣ መተሳሰብን ስታስተምር ነበር:: ይህ ደግሞ ያለ ጥርጥር ነገሥታቱን ጠቅሟቸዋል:: ነገሥታቱን ባይጠቅማቸውም ይህ አቋሟ ስሕተት አልነበረም:: ለምን? የነበረችበትን ጊዜ እናስብ፣ በረጅሙ ታሪካችን ውስጥ ከመንግሥታት ጋር በነበራት ግንኙነት የነገሥታቱ የግዛት ማስፋፋትና የቁጥጥር አቅም እየሰፋ ሲሄድ ሃይማኖቱ ብሔራዊና የመንግሥት ሃይማኖት ነበር:: ስለዚህ የግዛት አንድነቱን ለማስጠበቅ <አንድነትን> ነው ልትሰብክ የምትችለው:: ነገሥታቱን <የለም÷ ግዛት አታስፋፉ> ብላ ልትከላከልና ልታስቆም አትችልም:: የግዛት ማስፋፋቱ ለህብት ፍሊጋ ነው:: በሌላ በኩል የአካባቢ መንግሥታትን /Regional Kingdoms/ በክፍለ አህጉሩ አስፍስፈው ከነበሩ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የታደገ ነው:: ፀረ ዴሞክራቲክ ነበር፣ ሊኾን ይችላል፣ በወቅቱ ግን እንዲያ ብለን ልንተቸው የምንችል አይመስለኝም:: ቤተ ክርስቲያን ይህን መስፋፋት ልታስቆም አትችልም ነበር፣ ምናልባት በግዛት ማስፋፋቱ ሂደት ነገሥታቱ አንዳንድ አካባቢያዊ የጎሳ መንግሥታትን በኃይል የመያዝ ሁኔታ ስለ ነበር ቤተ ክርስቲያኒቱን ደምሮ የማየት ነገር ሊኖር ይችላል:: ነገር ግን እኔ እስከ ማውቀው ድረስ ቤተ ክርስቲያናችን ሰዎችን በመሣሪያ ኃይል አስገድዳ አሳመነች÷ አጠመቀች ሲባል ሰምቼ÷ አንብቤ አላውቅም:: ምናልባት በጥቂት አካባቢዎች በተወሰኑ አገልጋዮች ተፈጽመዋል የተባሉ ነገሮች እንደ ማሳያ ይቀርቡ ይሆናል:: ይሁንና ቤተ ክርስቲያን ትምህርቴና ሥርዓቴ /ፖሊሲዬ/ ብላ የምትመራበት አይደለም::

«ነገሥታት /መንግሥታት/ በታሪክ ፈጽመውታል» በሚባለው ስሕተት «እነርሱን ቀብታ አንግሣለች፣ በነገራቸው ሁሉ አብራ ነበረች» የተባለችው ቤተ ክርስቲያናችን ምን ያህል ተጠያቂነት አለባት?

በመጀመሪያ መንግሥታቱ <ስሕተት ሠርተዋል> ስንል የትኛውን ስሕተት ማለታችን ነው? ለምሳሌ:- ዐፄ ቴዎድሮስ ለምን በምርጫ ሥልጣን አልያዙም፣ ማለታችን ነውን? ምክንያቱም በዝብዝ ካሣን <ዐፄ ቴዎድሮስ> ብላ ቀብታ ያነገሠችው እርስዋ ናት:: ይህን ስሕተት ካደረግነው «ዐፄ ቴዎድሮስ» ለምን በምርጫ ካርድ አልተመረጡም፣ በካርድ ላልተመረጡ መሪ ለምን ንግሥና ሰጠች» ማለታችን ነውን? በሌላ በኩል መንግሥታት ሊሠሩት የሚችሉት ብዙ ዓይነት ስሕተት ይኖራል:: «መንግሥት ይህን ስሕተት ሲሠራ ቤተ ክርስቲያኒቱ ደግሞ እንዲህ አድርጋ ነበር» ተብሎ በግልጽ ቢነገር በጉዳዩ ላይ ይቅርታ መጠየቅ ካለበት ይቅርታ የማይጠየቅበት ምክንያት የለም:: ለምሳሌ:- «በሮም አደባባይ የፋሽስት ኢጣልያ ሠራዊት ለወረራ ሲዘምት መድፉንና ታንኩን የሮም ፓፓ ባርከውታል፣ ለወታደሮቹና ለወረራውም ተልእኮ መሳካት ጸሎት አድርገዋል» ይባላል:: ይህ የተወሰነ ግን ግልጽ ጉዳይ ነው:: ለዚህ የታሪክ ስሕተት የሮም ካቶሊክ ተካፋይ በመሆንዋ ፖፑ ይቅርታ ጠይቀዋል:: ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ጉዳይ ቢቀርብ መልስ መጠበቅ ይቻላል:: የአንድ ነገር መልካምነቱ ወይም መጥፎነቱ እንደ ወቅቱ ሊሆን ይችላል:: ዋናው መመዘኛው ነው:: «ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ለምን በሕዝበ ውሳኔ ግዛት አላስፋፉም» ብንል ስሕተት የሚኾነው የራሳችን መመዘኛ ነው:: በዚያን ወቅት ስንኳን እርሳቸው አውሮፓውያን የሚያደርጉት አልነበረም:: እንደውም ለአካባቢ መንግሥታት ግብር ከመገበርና ጦር ከማዋጣት ውጭ የራስ ገዝ ሥልጣን የመስጠት የአስተዳደር ጥበባቸውና በዲፕሎማሲያዊ ብልሃታቸው ከአውሮፓውያኑ ይልቅ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ሳይሻሉ አይቀሩም::

ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥታቱ ርእዮተ ዓለምንና ሕጋዊነትን (Ideology & legitmacy) የማኅናጸፍ ጠቀሜታ ሰጥታለች:: ይህን መሥራት ስሕተት ነው ማለት አይቻልም:: ለምን? ይህን መመዘን ያለብን በወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ /ዓለም አቀፍ ልምድና አዝማሚያ/ ነው:: ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ውጭ መሆን አይቻልም:: «መንግሥታት በሠሩት ስሕተት ውስጥ አብራ ትታያለች» ከማለት ውጭ «ስሕተት ሲሠራ ለምን ዝም አለች» የሚል ክስ ከመጣም ስሕተት የሚባለው ነገር ተለይቶ የመቀመጡ አስፈላጊነት ቀዳሚ ጉዳይ ሆኖ በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ተለይታ የምትጠቀስበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም:: በወቅቱ ሌሎቹም የሚገኙበት ሁኔታ ይኸው ነበር:: በግራኝ አሕመድ ጊዜ የነበረውንም በተመሳሳይ መልኩ ማገናኘትም ያስፈልግ ይሆናል:: በአጠቃላይ ንግግሩን በጅምላ ከማድረግ ይልቅ ተናጠላዊ ጉዳዮች እየቀረቡ መወያየቱ ነው የሚበጀን::

**«ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ላይ እጁን ያነሣ መንግሥት ቢኖር ኢሕአዴግ የሚመራው መንግሥት ነው::»**

ይህን በአጭሩ ለማየት÷ ክቡር ሚኒስትሩ <እጅ> ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? <እጅ> እንደ ዘመኑ ይለያያል:: ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የነበራቸው እጅ፣ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት የነበረው እጅ አለ:: ሁሉም እጅ አለው:: እንግዲህ ክቡር ሚኒስትሩ «አሁን ያለው ሁኔታ ከእኒህ ከሁለቱ ይሻላል» ለማለት ከኾነ አዎ÷ በአንጻራዊ መልኩ ይሻላል ለማለት ይቻል ይሆናል:: እዚህ ድምዳሜ ላይ ግን መንግሥትና የሃይማኖት ተቋማት አንድ ላይ የመሥራታቸውን ነገር እንደ መጥፎ የማየት ችግር ያለብን ይመስለኛል:: እኔ ቢኾን እወድ የነበረው እንደ ነገሥታቱ ዘመን ብሔራዊና የመንግሥት የሚባል ሃይማኖት ሳይኖር፣ ነገር ግን መንግሥት አዎንታዊ በኾነ ግንኙነት ከሃይማኖት ተቋማት ጋር በይፋ አብሮ መሥራት ቢችል ነበር:: ይኸ በኢትዮጵያችን ነባራዊ ሁኔታ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነገር ነበር:: «ዓለማዊ (Secular) እሆናለሁ» እያሉ ነባሮቹን የሃይማኖት ተቋማት ወደ ጎን መግፋት አገባብ አይደለም:: በኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ነጻና ገለልተኛ ለመሆን ከቻሉ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ:: ለሁሉም ነገር ÷ለሰላም ለዴሞክራሲም፣ ለልማትም:: መንግሥትንም ሊያግዙ ይችላሉ::

**ጉዳዩ አይነኬ መሆን የለበትም:: የቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ግንኙነት ምን ዓይነት ነበር? ቤተ ክርስቲያን ምን ሚና ነበራት? ሚናዋን ስትጫወት ምን አማራጭ ነበራት? ከዚያ ሚና ተጠቀመች ወይ? እርስዋ በመጠቀምዋ የተጎዳ አካል አለ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን አንሥተን መወያየት አለብን::**



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## በአጠቃላይ በውይይቱ ሂደት ስለ ቤተ ክርስቲያን ተነግረው የተራመዱት ሐሳቦች በምእመኑ የእምነት ሞራልና በመንግሥት ላይ ምን ተጽዕኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ?

በመጀመሪያ ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገሩ ነገሮች ድንገት የተነገሩ ናቸው ብዬ አላምንም። ምክንያቱም በተለያዩ ክልሎች የተለያዩ አገላለጾች ይኑሯቸው እንጂ ተንጸባርቀዋል። ወደ ድንም ጠላንም ቤተ ክርስቲያን የውይይቱ አካል /ጉዳይ/ ሆናለች። ለእኔ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ ጉዳይ መነሣቷ ስሕተት ነው አልልም። ምክንያቱም ሁኔታው በአንድ በኩል የሚያሳየኝ ቤተ ክርስቲያኒቱ ዛሬም በአገራችን ካሉት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ኃይሎች አንድዋ ምናልባትም ዋነኛዋ መሆንዋን ነው። ብዙ ሺሕ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች በተሰበሰቡበት ሁኔታ ስለ ማይረባና ጥቅም ስለሌለው አካል ሦስትና አራት ቀናት እንዲሁ አይባክንም፤ ስለሚፈለግ ወይም ስለ ሚጎዳ፥ አልያም ስለ ሚጠቅም አንድ አካል ነው እንጂ። ይህ በእንዲህ እያለ ቤተ ክርስቲያኒቱ በውይይቱ ላይ ተነሥታ የተባለበት መንገድ ግን ተገቢ ነው ለማ ለት ይቸግረኛል። አንደኛ፡- የቀረቡቱ ትንታኔዎች ታሪክን ዳግም ለመሥራት እንደ መሞከር ያህል ነው። ሁለተኛ፡- ጉዳዩ የሚነሣበት መንገድ ከስሕተት ለመታረም ወይም ለሥራ ለመነሣሣት የሚያበቃ ገንቢ አቀራረብ ሊኖረው ይገባል። ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደ ተቋምና የቤተ ክርስቲያኒቱ ተከታዮች /ምእመናን/ እንደ ዜጋ በአዎንታዊነት ለአገራችን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ የሚያነሣሣ መኾን አለበት። በገጠርም ይሁን በከተማ ከኅብረተሰቡ ጋር በየደረጃው የተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች ቤተ ክርስቲያኒቱን በዘፈቀደ ከመውቀስና ከማጥላላት ይልቅ ሚናዋን ለመጠቀምና ለማሳሰብ ቢጥሩ መልካም ነው። በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ጉዳዩ መነሣቱ ጥሩ ነው፤ የተነሣበት መንገድ ግን ጥሩ አይደለም። ተጨባጭ ስሕተቶች አሉበት፤ ሰዎችንም እልህና ግራ መጋባት ውስጥ ይከታል። በጉዳዩ ላይ ቤተ ክርስቲያናችን ይፋዊ መልስ እንደምትሰጥ እጠብቃለሁ። የሚያሳዝነኝ የቤተ ክርስቲያኒቱን ስሕተት ለመንቀስ ይኼ ሁሉ ሲነገር የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ውለታ እንኳን አለመነሣቱ ነው። ዐድዋ ስለ ዘመቱት ካህናት 'ኮ ከእኛ በላይ የውጭ ታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል።

## በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ሲነገሩ ከቆዩትና ከተጓዳኝ ነገሮች በመነሣት ከሕዝብ ግንኙነት አንጻር ቤተ ክርስቲያን ምን መሥራት አለባት?

ሁለት ነገሮች ይታዩኛል። በቤተ ክርስቲያኒቱና በተከታዮቿ በኩል በሁሉም ነገር ፍጹም ነበርን ብለን መከራከር መቆም ያለበት ይመስለኛል። ነገሮችን እንደ ሚገባቸው በሚዛናዊነት /Objectively/ ለይተን ለማየት መቻል አለብን። የተካሄደው ውይይት የመሠረተ ሃይማኖት /ዶግማ/ ጉዳዮችን ያነሣል። እንደ አጠቃላይ ይህን በተመለከተ አንድን የመንግሥት አካል የሚመለከተው አይመስለኝም። ይህን በተመለከተ ቀጥተኛ መልስ መስጠት ያስፈልጋል። የመጀመሪያው የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ይህ መሆን አለበት። ሁለተኛው ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውይይት ማድረግ ይኖርብናል። እኔ ለምን እንደ ሚፈራ ባይገባኝም በኢትዮጵያችን <የመንግሥትና ሃይማኖት ግንኙነት እንደ ምን ነበር?> የሚለውን አንሥተን ለምን አንወያይም? ጉዳዩ አይነኬ መሆን የለበትም። የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ምን ዓይነት ነበር? ቤተ ክርስቲያን ምን ሚና ነበራት? ሚናዋን ስትጫወት ምን አማራጭ ነበራት? ከዚያ ሚና ተጠቀመች ወይ? እርስዋ በመጠቀምዋ የተጎዳ አካል አለ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን አንሥተን መወያየት አለብን። የምንወያየውም ለመማማርና ለመተራረም በሚያስችለን ገንቢ መንፈስ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ይጠብቀንና በመንግሥት አካላት በየስብሰባው በእኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተነገሩ የተባሉት ጉዳዮች በሌሎቹ ዘንድ ተነግረው ቢሆን ወደ ግጭት ይጋብዘን ነበር። በውስጣችን ስላለፈው ቁርሾ ረስተን አብሮ ስለ መሥራት የሚያነሣሣን ነገር ቢፈጠር መልካም ነው። ታሪክን የምንገመግመው <አንተ እንዲህ አድርገኸኛል> ለመባባል ሳይሆን ለመማማር ነው። ቤተ ክርስቲያን ይህን አስመልክቶ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሥራት፣ ታሪክ ጸሐፊዎች ይህን ከመጻፍ አልፈው ራስን ከመከላከል በላይ እውነታው ላይ በማተኮር ሞያዊ ትንታኔ መስጠት ይኖርባቸዋል። ውይይቱ የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮችንም ቢያሳትፍ ክፋት የለውም። ታሪኩ የጋራችን ነው። የሚና ልዩነት እንጂ ታሪኩ የጋራችን ነው። በዚህ ረገድ የሐመር መጽሔት ተገቢው የውይይት መድረክ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

## ነገረ ድኅነት ... /ከገጽ ፲፮ የዞረ /

ይህም የምስጋናና የምስክርነት ቃል ከባለቤቱ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር በጸጋ የሚወለድበትን ምሥጢረ ጥምቀት በመሠረተበት ዕለት ይህ የምስጋናና የምስክርነት ቃል ተሰምቷል። «በዚያም ወራት ኢየሱስ ከገሊላ ናዝሬት መጥቶ ከዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ፤ ወዲያውም ከውኃው በወጣ ጊዜ ሰማያት ሲከፈቱ ፥ መንፈስም እንደ ርግብ ሲወርድበት አየ፤ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ።» /ማር.1፥9።/

ልዑል እግዚአብሔርን በአንድነትና በሦስትነት ስሙ እየተቀባበሉ ማመስገንም ልማደ ውዳሴ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተመለከተው፡- «አንዱም ለአንዱ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር።» /ኢሳ.6፥3/ በማለት እየተቀባበሉ ልዑል እግዚአብሔርን ማመስገን የተጀመረው በመላእክት ከተማ መሆኑን ይህ ቃል በግልጽ ያመላክታል። ሥርዓተ መላእክት በሚከወንባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ካህኑ እየመራ ምእመኑ እየተከተለ የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎት ከላይ በተቀመጠው መሠረት ወደ ፊትም እየቀጠለ ይሄዳል።

ከዚህ በመቀጠልም ካህኑ በመዝሙር 116፥1 ላይ ያለውን የምስጋና ቃል በዜማ እያመሰገነ ምእመናንም እን ዲከተሉት ያዛቸዋል። እንዲህ በማለት፡- «ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ኵልክሙ አሕዛብ፤ አሕዛብ /ምእመናን ሁላችሁ/ እግዚአብሔርን አመስግኑት።» ምእመናንን ስለ ብዛታቸው አሕዛብ እያለ ይጠራቸዋል።

ምእመናንም የአባታቸውን የካህኑን ትእዛዝ ተቀብለው፡- «ወይሴ ብሕዎ ኵሎሙ ሕዝብ፤ ወገኖቹም /ሕዝቡም/ ያመስግኑት /እናመሰግናለን» በማለት ይሳተፋሉ። አሁንም ካህኑ «ምሕረቱ በእኛ ላይ ጸንታለችና» ብሎ ያዜማል። ይህም ማለት «በአምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንኃለሁ» ብሎ የገባልን ቃል ኪዳን በእኛ ጸንታለችና /ተፈጽማለችና/ ማለት ነው።

ምእመናንም ተቀብለው «የእግዚአብሔር ቸርነት ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል።» ብለው ያዜማሉ። ከዚህ በኋላ ካህኑ የመጀመሪያውን መጨረሻ ምስጋና እንዲህ በማለት በዜማ ያመሰግናል። «ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን፤ ሃሌ ሉያ ቅድመ ዓለም ለነበሩ፣ ዓለምን አሳልፈው ለሚኖሩ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ

/ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል/



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ነገረ ድኅነት ...

ከገጽ ፳፫ የዞረ

ቅዱስ ክብር ምስጋና ይግባቸው ሃሌ
ሉያ::» ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን
ይህን የኅብረት ምስጋና የተቀበለችው
ከዓለመ መላእክት ነው:: «እንደ
ብዙ ሕዝብም ድምፅ÷ እንደ ብዙ ውኃ
ዎችም ድምፅ÷ እንደ ብርቱም ነጎድ
ጓድ ድምፅ÷ያለ ድምፅ ሰማሁ:: እንዲህ
ሲል:-ሃሌ ሉያ፤ ሁሉን የሚገዛ ጌታ...»
እንዲል:: ራእ. 19÷6::

ከዚህ የምስጋና ጸሎት በኋላ ሠራኢ
ው ዲያቆን ለመጀመሪያ ጊዜ ምእመ
ናን በትጋትና በንቃት ጸሎተ ቅዳ
ሴውን እንዲከታተሉ የሚቀሰቅስበትን
ዜማ ያሰማል:: «ተንሥኡ ለጸሎት፤ ለ
ጸሎት ተነሡ::» የሚለውን ዐዋጅ ያው
ጃል:: ምእመናንም ተከትለው:- «እግ
ዚኦ ተሠሃለነ፤ አቤቱ÷ እዘንልን፣ ራራ
ልን፣ ይቅር በለን» በማለት ለዲያቆኑ
ትእዛዝ የተግባር መልስ ይሰጣሉ:: ሰባ
ኪው ካህንም «ሰላም ለኵልክሙ፤
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» በማለት በ
ጸሎት የተደገፈ የማጽናኛና የማረጋጊ
ያ መልእክቱን ያስተላልፋል::

ምእመናንም የካህኑን የሰላምታ
መልእክት በመቀበል:- «እንደ ይቅር
ታህ እንደ ቸርነትህ ይደረግልን» በማ
ለት የሰላሙን የምሥራች መቀበላቸ
ውን ያረጋግጣሉ:: ለመሆኑ «ለጸሎት
ተነሡ» የሚለው የዲያቆኑ ትእዛዝና
«ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» የሚለው
የካህኑ የምሥራች የት መጣው ምን
ድን ነው? የተጀ መረውስ መቼ ነው?
ለምንስ አስፈለገ? «ለጸሎት ተነሡ»
የሚለውን ቃል መጀመሪያ ጊዜ የተና
ገረው አባታችን አዳም ሲኾን «ሰላም
ለሁላችሁ ይሁን» የሚለውን የምሥራ
ች ቃል የሰበከው ደግሞ መድኃኒታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሊቃ
ውንተ ቤተ ክርስቲያን ይተረጉማሉ::
ቃሉ የተነገረውም በሲኦል ውስጥ ለነ
በሩ ነፍሳት ነው:: ይህ ቃል በመከራ
ውስጥ ለነበሩ ነፍሳት የድኅነታቸው
ምልክት፣ የቃል ኪዳን ፍጻሜና የትን
ቢተ ነቢያት ፍሬም ነበር::

የሰው ልጅ አባት አዳም «በአ
ምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወ
ልጄ አድንነሃሁ» የሚለውን የፈጣሪ
ውን ኪዳን ሱባዔ እየቆጠረ በተስፋ
ይጠባበቅ ነበር:: ጊዜው ደርሶ ፈጣሪው
በመልዕልተ መስቀል ውሎ የአዳምንና
የዘሩን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ
አስወግዶ በመጨረሻም በቅዱሳት
መጻሕፍት እንደ ተጻፈ ሆምጣጤውን
ከተቀበለ በኋላ «ተፈጸመ» አለ:: ራሱ
ንም አዘን ብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ::
ዮሐ. 19÷30:: ከዚያም ነፍሳትን ከሲ
ኦል ነጻ ያወጣ ዘንድ በአካለ ነፍስ ወደ
ሲኦል ወረደ፤ አዳምም ኪዳኑና ትንቢ
ቱ እንደ ተፈጸመ ዐውቆ ነፍሳትን «ለ
ጸሎት ተነሡ» አላቸው:: በማያያዝም



ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በቅዳሴ ጸሎት ላይ

መድኃኔዓለም ክርስቶስ «ሰላም ለሁላችሁ
ይሁን» በማለት መልኩን አሳይቷቸው
ልጅነት አግኝተዋል:: «በእርሱም ደግሞ
ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው::»
እንዲል:: 1ጴጥ.3÷19::

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃው
ንት ትርጓሜ መሠረትም «ለጸሎት ተነ
ሡ» የሚለው ዲያቆን የአዳም፣ «ሰላም
ከሁላችሁ ጋር ይሁን» የሚለው ካህን
የመድኃኔዓለም ክርስቶስ፣ «አቤቱ÷
ይቅር በለን፤ እንደ ቸርነትህ ይደረ
ግልን» በማለት የሚጸልዩ ምእመናን
በሲኦል የነበሩ ምሳሌ መሆናቸውን ያስረ
ዳሉ:: ጸሎቱ ደግሞ የድኅነት፣ የቸር
ነት የተስፋ፣ የምሥራች፤ የልጅነት
ጸሎት ስለሆነ በተለይ ለክርስቲያኖች የዘ
ወትር ጸሎታቸው ነው:: ከጥንታውያኑ
አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ጋር ኅብረት
መንግሥተ ሰማያት የሚገቡበት ጸሎት
ነውና::

ከዚህ በመቀጠል ሠራኢው ካህን
የቅዱስ ባስልዮስ ድርሰት የሆነውን የ
ጸሎት ክፍል በዜማ - ወይም በንባብ
በግእዝ ወይም በአማርኛ ንባብ ይጸል
ያል:: ጸሎቱ የምሥጋናም የምስክርነ
ትም የልመናም ጸሎት ነው:: በምስጋ
ናነቱ ነአኵቶ ለገባሬ ሠናያት ላዕሌነ፤
ለእኛ በጎ በጎውን ነገር ያደረገልን እግዚ
አብሔር አብን እናመሰግናለን::» ይላል::

በምስክርነቱም:- «ከመከራ ሰውሮ
ናልና፣ ጠብቆናልና፣ ወደሱ አቅርቦናልና
በረድኤት ተቀብሎናልና፣ አጽንቶ ጠ
ብቆናልና እስከዚች ሰዓት አድርሶናል
ወዘተ...» ይላል:: በልመናነቱም «በፍ
ጹም ፍቅር፣ በፍጹም ይቅርታ ይጠ
ብቀን፤ በዘመናችን ሁሉ ይጠብቀን» በማ
ለት በሦስት የተከፈለ ጸሎቱን ያቀር
ባል:: ይህም በአባቶች የጸሎት አቀራረብ
የተለመደ ነው:: «እግዚአብሔር ከክፉ
ሁሉ ይጠብቅሀል÷ ነፍስህንም ይጠብቃ
ታል:: ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚ
አብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠ
ብቃል::» መዝ. 120÷7::

በመቀጠልም ዲያቆኑ «ለጸሎት ተነ
ሡ» ብሎ ነበርና አሁን ደግሞ
«ጸልዩ» የሚለውን ዐዋጅ ያው
ጃል:: ሕዝቡም ተከትለው አቡነ ዘበሰ
ማያት ይደግማሉ:: «ጸልዩ» ሲል ተሰ
ጥዎ ካለው ተሰጥዎውን መቀበል÷ ተሰ
ጥዎ ከሌለው አባታችን ሆይ÷ ብሎ
መጸለይ ሥርዓት ነው:: በዚሁ የቅዱስ
ባስልዮስ ጸሎት ውስጥ ዲያቆኑ
«ጸልዩ» ከማለቱ በፊት በሩቅ አነጋገር
«ከመከራ ሰውሮናልና÷ ከመከራ ጠ
ብቆናልና÷ በረድኤት ተቀብሎናልና»
በማለት ይጸልይና ያመሰግን ነበር:: ዲ
ያቆኑ «ጸልዩ» ካለ በኋላ ግን በቅርብ
አነጋገር «ከመከራ ሰውረኸናልና፣ ከመ
ከራ ጠብቀኸናልና፣ በልጅነት አቅር
በኸናል» በማለት ካህኑ ይጸልያል::

ይህም ምሳሌ አለው፤ «ጸልዩ» እስ
ኪል ድረስ አርቆ መናገሩ አምስት
ሺሕ አምስት መቶ ዘመን ከእግዚ
አብሔር ርቀን ለመኖራችን ምሳሌ ሲ
ሆን «ጸልዩ» ካለ በኋላ አቅርቦ መና
ገሩ ከአምስት ሺሕ አምስት መቶ
ዘመን በኋላ በአምላክ ሰው መሆን ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት መቅረባች
ንን ለማሳየት ነው::

«እንዲሁ እኛ ሕፃናት ሳለን ከዓለም
መጀመሪያ ትምህርት በታች ... ባሪያ
ዎች ነበርን ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ
በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር... ከሕግም
በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» እንዲ
ል:: ገላ.4÷5::

ካህኑ ከዚህ የምስጋና ጸሎት ውስጥ
የእግዚአብሔርን ውለታ እያስ ታወሰ
ያመሰግናል:: «ነአኵተከ ላዕለ ኵሉ
ግብር፤ ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥ ረት
በመፍጠርህ፣ አራቱን ባሕርያት ፊጥ
ረህ በማስማማትህ ፤ /እሳት÷ውኃ÷ ነፋ
ስና መሬትን ማስማማት በተለይ
በሰው ባሕርይ ውስጥ አምላካዊ ግብር
ነው/::»

«እስራኤልን ከግብፅ ያወጣህ፣
መና ከደመና አውርደህ ውኃ ከጭ
ንጫ አፍልቀህ በመመገብህ፣ ለአዳም

/ወደ ገጽ ፴፰ ዞሯል/



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከሞት ባሻገር

ዲ/ን ሔኖክ ኃይሌ
ወንጌ ደ/ም/ቅ/ሚካኤል ሰንበት ት/ቤት

ዕለቱ ብሩህ ነው፤ ለእኔ ደግሞ ታላቅ ዕለት። ለብዙዎች ትምህርት ሊሆን በሚችል ውጣ ውረድ አልፌ ነው ለዛሬዋ ዕለት የደረስኩት። «የእኔ ታሪክ ለሌሎች ትምህርት ይሆናል» የምለው በሰው ፊት ሁሉ ብርሃን የሚሆን ተጋድሎን ፈጽሜ አይደለም። እንዲያውም በተቃራኒው ብዙ በድዬአለሁ፤ ግን የእግዚአብሔር ቸርነት ከከበበው የኃጥእ ሕይወትም ለካ ትምህርት ይገኛል?!

አሁን ያለሁት በእግዚአብሔር ቤት ነው። ይህ ዕለት ከቁም ሞት ተነሥቼ በሕይወት መኖር የጀመርኩበት ታላቅ ዕለት ነው። መለስ ብዬ የራሴን ታሪክ ስመለከት የእግዚአብሔርን ታላቅነት እረዳለሁ። በየደቂቃው ስለ አምላኬ ባሰብኩ ቁጥር የሚታየኝ ወሰን የሌለው ፍቅርና ምሕረቱ ነው። አባ ኖላዊ በአጠገቤ አልፈው በምልክት ሰላምታ ካቀረቡልኝ በኋላ በመቅደሱ መግቢያ አንጻር ሦስት ጊዜ ሰግደው ጸሎት ለማድረግ ቆሙ። እርሳቸው ጸሎታቸውን ሲቀጥሉ እኔ ስለ እርሳቸው ማሰብ ጀመርሁ።...

አባ ኖላዊ የቤተሰቤ መምህረ ንስሐ ናቸው። እኔ የማውቃቸው ወደ ቤታችን እየመጡ የአባትነት አገልግሎታቸውን ሲሰጡ ነበር። ጠይም ገጻቸው ከጢማቸው ጋር ግርማን ያላበሳቸው፣ ፊታቸው የማይፈታ፣ ብዙ ጊዜ ፈገግታ የማይታይባቸው ናቸው። ወደ ቤት ሲመጡ አንዳንድ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮች ሲደረጉ ከተመለከቱ ያለ አንዳች ማለሳለስ ጠንከር አድርገው በእግዚአብሔር ቃል ስለሚገሥጹና ሽንገላን ስለማይወዱ በቤተሰባችን ዘንድ የተፈሩና የተከበሩ ናቸው። እኔ «ዘመናዊነት ይሰማኝ» ስለ ነበር በጥሩ ዐይን አልመለከታቸውም ነበር። እርሳቸው ሲመጡ ካላገኙኝ በቀር መኝታ ክፍሌን ከውስጥ ቆልፌ እቀመጥና እንደሌለሁ እሆናለሁ እንጂ ላገኛቸው አልሻም ነበር። እርሳቸው ባሉበት ዘፈን መስማት እና ለእኔ የሚስማሙ ፊልሞችን መመልከት ስለማልችል ወደ ቤታችን መምጣታቸውን አልወደውም ነበር። ምንም እንኳን ምክርና ተግሣጽ ከሰጡ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ የሚሄዱ ቢሆንም እኔ ግን ለአፍታ እንኳ እርሳቸው እያሉ መቀመጥ አልፈልግም ነበር። ከሁሉም የሚያበሳጩኝ ጥያቄአቸው ነበር።

«ልጄ ትምህርት እንዴት ነው? መቼ ይሆን የምትመረቀው? ምን ያህል ይቀርሃል?» የዘወትር ጥያቄአቸው ነው። እኔም በመሰላቸት እየተንጠራራሁ «ይኸን ያህል ይቀረኛል» እላቸዋለሁ። እርሳቸውም ቀበል ያደርጉና፦

«ግዴለም አይዞህ በርታ እግዚአብሔር የራቀን የሚያቀርብ አምላክ ነው። እርሱ ይርዳህ፤ አንተም ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጣህ ጸልይ፤ ያለ እርሱ ፈቃድ የበላ÷ ደስ "ብሎትስ ተድላን የቀመሰ ማን አለ? ብሏል ጠቢቡ ሰሎሞን፤ እግዚአብሔር የሌለበት ዕውቀት የትም አያደርስም» ይሉኝ ነበር። በትምህርቴና በግል ሕይወቴ ዙሪያ ሲያናግሩኝ በጣም እናደድ ነበር። ቤተሰቦቼን ፈርቼ ዝም እላለሁ እንጂ ቀና መመለስ እንኳን አልፈልግም ነበር። ተመርቄ ሥራ ከያዝሁ በኋላ ምክራቸውን መስማት ብቻ ሳይሆን ለጥያቄአቸው መልስ መስጠትም ሞት ይመስለኝ ነበር። በዚህ ሁኔታ ሳለሁ ነበር ሕይወቴን የለወጠ አጋጣሚ የተፈጠረው።

የምሠራበት መሥሪያ ቤት የሥራውን አፈጻጸም ለማሻሻልና የሰው ኃይል ብቃቱን ለማሳደግ ለሠራተኞች የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል ይሰጥ ነበር። በአሁኑ ዙር ለዚህ ዕድል ከተመረጡት ሁለት ሠራተኞች አንዱ ሆንኩኝ። ደስታዬ ወሰን አጣ። የምይዝ የምጨብጠውን አጣሁ፤ ብቻ ሥራዬ ፈንጠዝያ ሆነ፤ እንኳን ምክንያት ተገኝቶ ወትሮም ለኃጢአት የፈጠነው እግሬ በተገኘው የትምህርት ዕድል ሰበብ ከጓደኞቼ ጋር በስካር፣ በዘፈንና በዝሙት ሰነበትኩ፤ ለጉዞዬ ዝግጅት ማድረግና በየዕለቱ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሟላት መሯሯጥ ጀመርሁ። ተማሪ ሳለሁ የማላውቃቸው ዘመድ ወዳጆች «እንኳን ደስ ያለህ» ለማለት ሲጎርፉ ሰነበቱ።

አንድ ሰንበት አባ ኖላዊ መጥተው የተለመደውን ምክርና ተግሣጽ ከሰጡ በኋላ እንደ ወትሮአቸው ረጋ ብለው፦ «ልጄ እንኳን ለዚህ አበቃህ» አሉኝና ምክራቸውን አከሉበት። «አየህ ልጄ÷ ለዚህ ክብር ያበቃህ እግዚአብሔር ነው፤ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። ምን ዐዋቂ ቢኮን እግዚአብሔርን መፍራት ካልተጨመረበት ከንቱ ነው። እናም በምትሄድበት ሁሉ እግዚአብሔርን አስብ» አሉኝና ተሰናበቱኝ። ምክራቸውን በቀና መንፈስ አልተረዳሁትም ነበር። እርሳቸው ሲናገሩ ስለ እኔ ጉብዝናና ችሎታ አንሥተው አያወድሱም፤ እንዲያውም ንግግራቸው አንዳች የበታችነት ስሜት እንዲሰማኝ ስለሚያደርገኝ በክፉ ዐይን እመለከታቸው ነበር።

ጊዜው በጨመረ ቁጥር የጉዞዬም ቀን እየተቃረበ መጣ። በዚህ ወቅት ነበር ነገሮች የተለዋወጡት። የደም ምርመራ ውጤቴን ለመቀበል ወደ አንድ ክሊኒክ ስሄድ በደሜ ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. እንዳለ ተነገረኝ። አእምሮዬ ሊሸከመው የማይችለው ድንጋጤና ሐዘን ወደቀብኝ። ራሴን አዞረኝና ወደቅሁ። ውጤቴን የነገረኝ ሐኪም ኅሊናዬ እንዲመለስ እና እንድረጋጋ የተቻለውን ሁሉ ርዳታ አደረገልኝ። ትንሽ መለስ ሲልልኝ የምክር አገልግሎት ተሰጠኝ። የምክር አገልግሎቱ ከጊዜያዊ ጭንቀትና ድንጋጤ ቢያረጋጋኝም ሐዘኔን ግን አላቃለለልኝም። ወደ ቤት ከገባሁ በኋላ የተነገሩኝን የማጽናኛ ሐሳቦች ሳሰላስላቸው ተስፋ እንድቆርጥ አደረጉኝ። ኅሊናዬን ለማረጋጋትና በራስ መተማመንን ለመፍጠር ተብለው የተሰጡኝ ምክሮች ክፉ ባይሆኑም የመኖሬን ተስፋ በቁሳዊ ነገሮችና በሕይወት ፍልስፍና ላይ መመሥረቱን ኅሊናዬ አልቀበለው አለ። ራሴን ማጥፋት ተመኘሁ፤ ግን ደግሞ ዘገነነኝ። ቤተሰቦቼ ተደናግጠዋል። ያን ሰሞን በደስታ ለሳምንታት የከረመ ቤተሰብ በሐዘን ተዋጠ። የዘመድ ወዳጅ ጋጋታ ቀርቶ ቤቱ መቃብር ይመስል ጭር አለ። በየሄድኩበት የሚያውቁኝ ሁሉ ሲንሾካሾኩብኝ፣ ከንፈር ሲመጡልኝ ውስጤ ተበጠበጠ፤ ሌላ ሕመም ሆነብኝ።

ወደ መሥሪያ ቤት ሄጄ የጉዞዬን መሰናከል ለማሳወቅ ወሰንኩ። ነገር ግን ወሬው ከእኔ ቀድሞ ተሰምቶ ኖሮ በእኔ ምትክ ዕድሉ ለሌላ መሰጠቱ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ጠበቀኝ፤ ባዶነት ተሰማኝ። ትላንትና እኔን ለማግኘት ይሻሙ የነበሩ ሁሉ ዛሬ የእኔን መምጣት ሲያዩ እንደ ቸኮለ ሰው ቶሎ ሰላምታ ሰጥተውኝ ያልፉ ጀመር። ትንሽ ሰብአዊነት የሚሰማቸው ጥቂት ሰዎች ቀርበው በያጽናኑኝም ያው «ራስህን ጠብቅ÷ ይህን ብላ÷ ያንን ጠጣ» ከማለት ያላለፈ ምክር ጭራሽ ልቤን በሐዘን ሰባበረው።

አንድ እሑድ በመኝታ ክፍሌ ሆኜ እንደ ወትሮዬ ስቆዝም ከወደ ሳሎን እናቴ መጥታ አንኳኳች። ተነሥቼ ከፈትሁ፦ «አንተ እንቅልፋም» አለችኝ በርኅራኄ ድምፅ፤ «ይኼ ነገር ማብሰልሰል አይቀርብህም፤ ይልቅ ተነሣ፣ አባ ኖላዊ መጥተዋል፤ የሆነውን ሁሉ ነግሬአቸዋለሁ። ጠበል ሊረጩ ወደዚህ ይመጣሉ፤ ትንሽ ጸሎት አድርገው ቢደባብሱህ÷ተነሥተህ ጠብቃ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቸው» አለችኝና ሄደች:: እናቴ ምንም እንኳ ልቧ በሐዘን ቢሰበር እኔን ላለ ማስጨነቅ ምንም እንዳልተፈጠረ ለማ ስመሰል ትሞክራለች:: ያው ግን እሷም ሆነች አባቴ በጨዋታ መሃል ሳያስቡት በሚጥሉት ንግግር ልቤን ማድማታቸው አልቀረም::

የአባ ኖላዊን መምጣት ሳስብ የምገባበት ጠፋኝ:: ከመቼውም ጊዜ በላይ ዐይናቸውን ማየት አስፈራኝ፤ «ያለ እርሱ ፈቃድ የበላ፥ ደስ ብሎ ትስ ተድላን የቀመሰ ማን ነው?» የሚል ንግግራቸው በኅሊናዬ እየመጣ አስጨነቀኝ፤ ከአፍታ ቆይታ በኋላ አባ ኖላዊ በለሆሳስ ጸሎት እየደገሙ መጡ:: መኝታ ቤቱንና እኔን ከረጩ በኋላ ከአልጋዬ አጠገብ ያለች ወንበር ላይ አረፍ አሉና:-

«እንደምን አለህ ልጄ?» አሉኝ በዚያ በረጋ ድምፃቸው:: ጥያቄአቸው አበሳጨኝ፤ እናቴ ያለሁበትን ሁኔታ ነግራቸው እያለ «እንደምን አለህ» ማለታቸው አናደደኝና «አለሁ» አል ኳቸው እንዳቀረቀርሁ::

«ደኅንነትህን ጠየቅሁ እንጂ መኖርህንማ ይኸው እያየሁህ ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገን ብትል አይ ሻልም?» አሉኝ በቅሬታ::

«አባ፥ እማዬ የሆንኩትን ነግራ ዎት የለ፤ ታድያ እኔ እግዚአብሔርን እንዳመሰግን ይጠብቃሉ?» አልኩኝ በምሬት:: አባ ኖላዊ ፊታቸውን መለስ አድርገው ተመለከቱኝ:: ገጻቸው በሐ ዘን ዳምኗል:: ወዲያው ጢማቸውን በእጃቸው እየዳበሱ የቅሬታ ፈገግታ ፈገግ አሉ::

«ልጄ! እንኳን ዛሬ በሐዘንህ ጊ ዜ፤ በደስታህስ ጊዜ መች እግዚአብሔ ርን አመስግነህ ታውቅና!» አሉና መል ሰው ተከዙ:: ቀጠል አድርገውም: - «ልጄ፥ እስቲ የሆንከውን ሁሉ ከአንተው አንደበት ልስማው፥ ንገረኝ» አሉኝ:: እንኳንስ ንገረኝ ተብዬ «እህ!» ብሎ የልቤን የሚያደምጠኝ ካጣሁ ሰን ብቼአለሁ:: የምርመራ ውጤቴን ከሰ ማሁ ጀምሮ እስከ አሁን ያለሁበትን አንድም ሳላስቀር የገጠመኝን ሁሉ ነገርኳቸው:: በዝምታ አዳመጡኝ:: የል ቤን ጭንቀት ስተነፍስ እፎይታ ተሰ ማኝ፤ አባ ኖላዊ በትካዜ ካደመጡኝ በኋላ ትንሽ ዝም ብለው ቆዩና መና ገር ጀመሩ::

«አየህ ልጄ፥ የሰው ልጅ ድክ መቱ ሞቱን መዘንጋቱ ነው:: በእን ግድነት የምንኖርባትን ምድር እንደ ዘላለም ቤታችን አድርገን ዕቅዳችንን፣ ፍጻሜአችንን፣ ተስፋችንን ሁሉ በዚ ህች ምድር ላይ አድርገን ስላሰብን መለየትን እንፈራለን:: ልጄ፥ ይህ ሕ መም በደምህ ውስጥ መኖሩን ከሰማህ በኋላ የተሰጠህም ምክር አጽንቶ ያላቆ መህ ከዚህች ምድር ያለፈ ተስፋን ስላልያዝህ ነው:: አየህ፥ እግዚ አብሔር ነገርን ሁሉ በምክንያት የሚያደርግ አምላክ ነው እንጂ ሰውን መበቀል ማሠቃየት የሚሻ አይደለም:: እግዚአብሔር ቅጣትን የሚወድድ አምላክ ቢሆንማ ማንም ባልተረፈ ነበር:: አንተ እስከ አሁን በኃጢአት ውስጥ ነበርህ:: ስለ እግ ዚአብሔርና ስለ ሃይማኖት ማሰብ እንኳን አትፈልግም ነበር:: ምድራ ዊው ጉዞህ ማቋረጫ የሌለው፤ ዕው ቀትህ ሁሉን ድል የሚነሳ ይመ ስልህ ነበር:: አሁን ግን በምድራዊ ጉዞህ የማታመልጠው፥ በዕውቀትህ ድል የማትነሳው ሞት በፊትህ መኖሩን ዐወቅህ:: ልቡና ካለህም ከዚህ ሞት በላይ ሌላ ኃይል እን ዳለ ትማርበታለህ» አሉኝና «ልጄ፥ ሞት የሁላችንም ዕጣ ነው፤ ያው ሆኖ የሚኖር፥ ሞትንስ የማያይ ማን ነው?» ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ተዋጡ:: «አንተ በእዚህ በሽታ ብትያዝም ባትያዝም መሞትህ አይቀርም:: አሁን ላንተ ከንፈር የሚመጡ፥ ጤነኞች ነን የሚሉ ግን ከአንተ ቀድመው የሚሞቱ አሉ:: ልዩነቱ አንተ የምትሞት መሆንክን የምታስታውስበት ምክን ያት ተፈጥሮልሃል» አሉ:: የሚና ገሩኝ ነገር ሁሉ ቁስሌ ላይ ሲያርፍ ይሰማኝ ነበር:: አቀርቅረው ከሚና ገሩበት ቀና ብለው ተመለከቱኝ::

«ልጄ፥ የሰው ልጅ እንዲሁ ዐ ይኑ ታውሮ አይታይህም» አሉኝና በአባባላቸው ግራ መጋባቴን ተመ ልክተው «የሰው ልጅ እይታና አስ ተሳሰብ በዐይኑ ከሚመለከተው ነገር አላልፍ ብሎ ዐይነ ልቡናው ታውሯል:: እምነት አለኝ የሚለው ክርስቲያን እንኳን ከሞት ባሻገር ማሰብ ተስኖታል:: የሰው ልጅ ሕይ ወት ከሞት በኋላ ነው:: የምድር ላይ ቆይታችን ለዘላለማዊው ሕይ ወት ለመብቃት የምንፈተንበት እንደ ድንኳን ያለ ጊዜያዊ ኑሮ ነው:: የሰው ልጅ ከዚህች ጊዜያዊ ምድር የሚለይበትን ሞት ይዘነ ጋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን በመቃ ቢያን ሣልስ ላይ «የምትሞቱባትን ቀን አስቡ» እያለ ያዘክረናል:: እናም ልጄ፥ እግዚአብሔር ከሰዎች ሁሉ የተለየ አንተን ለሰማያዊው ጉዞ እንድትዘጋጅ ቀስቅሶሃል::» አሉኝ::

አባ ኖላዊ በዚህ አላበቁም:: ስለ ሰማያዊው መንግሥትም በሰ ፊው ነገሩኝ:: ከመኖሬ ይልቅ መሞ ቴን እንድናፍቅ አደረጉኝ:: ለካስ ቅዱስ ጳውሎስ:- «ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ» ማለቱ ለዚ ህ ነው:: ያላየነውን የምናይባት፣ ያልሰማነውን የምንሰማባት፣ ክፉ ነገር የሌለባት የእግዚአብሔር መን ግሥትም በእውነት ሞትን ታስንቃለች:: ከዚህ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄ ድና ቃሉን መስማት ጀመርሁ:: የአባ ኖላዊ ምክር አዲስ አለመሆኑን ተገነዘ ብሁ፤ ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕ ለት የምታስተምረው መሆኑን ተረዳሁ:: ከሕይወታችን ጋር አላገናዘብ ነው ሆኖ ነው እንጂ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሁሉም ነገር ሳታስተምር የቀረችበት ዕለት እንደሌለ ገባኝ::

በየአጋጣሚው ስሰማው የኖርኩ ትና አሁንም የምሰማው ወንጌል ተገለጠ ልኝ:: ስለ ሕይወት የነበረኝ ግንዛቤ ተለ ወጠ:: ቤተ ክርስቲያን «ሕይወት» ብላ ስትናገር እኛ የሥጋዊ ኑሮ ተድላ ደስ ታን እናስባለን እንጂ መች ስለ ሰማያ ዊው ሕይወት አስበን እናውቃለን አል ኩኝ በልቤ:: ለውጭ ሀገር ጉዞ በምሰና ዳበት ወቅት ወደ ውጭ ሀገር ከምትሄድ እና ዘላለማዊ ሕይወትን፥ መንግሥተ ሰ ማያትን ከምትወርስ የሚል ምርጫ ቢቀ ርብልኝ የቱን እመርጥ እንደ ነበረ ሳስብ የራሴንና የአጠቃላይ የሰውን ልጅ ደካ ማነት ተመልክቼ አዘንሁ::

አንድ ጠዋት አባ ኖላዊ መዝ ሙር እያዳመጥሁ ሳለ መጡ:: መስቀል አሳልመው ሰላምታ ከሰጡኝ በኋላ:- «ልጄ ምነው ብቻህን ሆንክሳ?» አሉኝ:- በርኅራ ኄ:: «መዝሙር እየሰማሁ ስለሆነ ብቸኝነ ቴን አልጠላሁትም፤ እማዬ ጓዳ ሥራ ላይ ነች» አልኳቸው:: «ዘፈን ከማዳመጥ አው ጥቶ ጆሮህን ለምስጋናው አቀናው አይ ደል? እግዚአብሔር ይመስገን፤ ለመሆኑ እነዚያ ሁሉ ጓደኞችህ ምን ዋጣቸው? አይ ሰው ከንቱ! ».... ትንሽ ተከዝ ብለው: - «እውነተኛ ወዳጅ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ የእርሱን ወዳጅነት አትጣ እንጂ ሰውማ ደካማ ነው» አሉኝ::

በእግዚአብሔር ቃል የተሸለመ ምክ ራቸው ሰዎች በእኔ ላይ በሚያሳዩት አጉል ጠባይ ከመማረር ይልቅ ለሚጠቋቆ ሙብኝ ሰዎች እንዳዝንላቸው ብሎም ከቁ ም እንቅልፋቸው እንዲነቁ እንድ መክርና እንድጸልይላቸው አስተማሩኝ:: ከዚህ በኋ ላ ስለ ንስሐ ተማርኩኝ:: በሰው እጅ ከመ ውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻላልና ኃጢአቴን በንስሐ ታጠብሁ፤ ዳግመኛ ወደ ሥራ ዓለም መመለስ ስላል ፈለግሁ የትምህርትና የሥራ ማስረጃዬን ለማውጣት ወደ መሥሪያ ቤቴ አመራሁ::

መሥሪያ ቤት ስደርስ ግቢው ጭር ብሎ ጠበቀኝ:: ነገሩን ስጠይቅ ሠራተኞች ሁሉ ወደ ስብሰባ አዳራሽ እንደ ሄዱ ተነገረኝ:: ወደ አዳራሹ አምርቼ ልገባ ስል በሩ ላይ አንድ ወጣት አስቆመኝ::

«የኅሊና ጸሎት እየተደረገ ነው፥ ቆይ» አለኝ በሹክሹክታ:: ከአፍታ በኋላ ሁሉም ሲቀመጥ የኅሊና ጸሎትን ምን ነት እያሰላሰልኩ ወደ ውስጥ ገብቼ ተቀ መጥኩ:: ሠራተኛው ሲንሾካሾክ ይሰ ማኛል:: አንድ ወጣት ከሌሎቹ እንድ መሳሰል ጧፍና ካናቴራ ሰጠኝ:: ለካስ ስብሰባው የኤች አይ ቪ /ኤድስን ጉዳት



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

አስመልክቶ የተደረገ ነው። ዞር ዞር
ብዬ ሳስተውል አዳራሹ ካናቴራ በለ
በሱና ሟፍ በሚያበሩ ሰዎች መሞላቱን
ተገነዘብኩ። የሟፉ መባከን ቆጨኝ።
«ለአንድ ገዳም ቢሰጥ ለነፍስ በጠቀመ
ነበር» አልኩኝ በልቤ። ከመድረኩ የተ
ለያዩ ንግግሮችና ጽሑፎች ቀረቡ፤
የሁሉም ይዘት ከአሁን ቀደም በየመገ
ናኛ ብዙኀኑ በየመድረኩ ከቀረቡት
የተለዩ አልነበሩም። ይህ ሁሉ ሠራተኛ
ከዚህ ሥነ ሥርዓት በኋላ የት እንደ
ሚያመሽ ሳስብ አዘንሁ። በስብሰባው
ላይ አብዝተው ከሚናገሩት ሰዎች
አንዳች አዲስ ነገር አልታይህ አለኝ።
የመናገር ዕድል ባገኝ የምናገረውን አሰ
ብኩና በወረቀት አሰፈርሁት። «ንስሐ
ግቡ÷ የምትሞቱበትን ቀን አስቡ÷
ከኃጢአት ተለይታችሁ ወደ እግዚ
አብሔር ቅረቡ» የሚል ነበር። ግን
ይህን መልእክት በየዕለቱ በቤተ ክርስ
ቲያን ዐውደ ምሕረት እንደ ሚነገር
አሰብሁ። ያልሰማ ማን አለ፤ ያላስተዋለ
እንጂ፤ እኔን መመልከት ራሱ ትልቅ
ትምህርት ነበር። ወረቀቱን ሰጥቼ ወደ
ቤቴ አመራሁ።

አሁን ያለሁት በእግዚአብሔር
ቤት÷ በመቅደሱ ነው። የዛሬዋ ዕለት
የክርስቶስን ሥጋና ደም የምቀበልባት፤
የኃጢአት ስርየትን የማገኝባት ዕለት
ናት። ቅዳሴው ተጀመረ፤ በጥሞና
እየተከታተልኩ ነው። እያንዳንዱ ቃል
በልቤ ሲያርፍ ቁስሌም ሲሽር ይሰማኝ
ነበር። ዲያቆኑ «ለጸሎት ተነሡ» እያለ
ያውጃል። የዐዋጁ ጥልቅ መልእክት
ተሰማኝ። በዚህ ዘመን ለሰው ልጅ
ችግር ሊቀርብ የሚችል ጥሪ ቢኖር፣
«ለጸሎት ተነሡ፤ በእግዚአብሔር ፊት
ቁሙ፤ ከኃጢአት እንቅልፍ ተነሥታ
ችሁ ለይቅርታው ተዘጋጁ» የሚል
መኾን ይገባዋል።

የዚህ ዘመን ጸሎትስ «አቤቱ
ይቅር በለን» ነው። እያንዳንዱን የ
ጸሎት ክፍል ስሰማ እንባ ተናነቀኝ፤
«ወይ ቤተ ክርስቲያን÷ አላዳመጥንሽም
እንጂ፤ ሁሉንም ነገር ከአንቺ አግኝተን
ነበር» አልኩኝ በልቤ፤ ቅዳሴው
ተገባደደ፤ እኔም በክርስቶስ፤ ክርስ
ቶስም በእኔ ሊኖር በቃሁኝ፤ ዲያቆኑ
«ሥጋ ወደሙን ተቀበልን፤ ከቅዱስ
ምስጢር ተሳተፍን፣ ለነፍሳችን ቁስል
ፈውስ ሆነን፤ ለዚህ የተገባን ያደረገንን
እግዚአብሔርን እናመስግነው» በጥዑም
ዜማ እኛም «የሰማይ አባታችን ሆይ÷
ወደ ፈተና አታግባን» ብለን በሰማይ
በአባትነቱ መንግሥቱን እስከ ምንወርስ
ድረስ ከኃጢአት÷ ከርኩሰት÷ ከፈተና
እንዲጠብቀን ተማፀንን፤ በካህኑ እጅ
ተባርከን÷ ተሰናበትን።

በምድር ያለች የሰማይ ደጅ፤
የቁስላችንን መፈወሻ ቤተ ክርስቲያንን
የሰጠንን አምላክ ከልቤ አመሰገንኩት።
ያለ እረኛ ያልተወንን አምላክ አመሰ
ገንኩት። አዎ÷ ሞት ከእንግዲህ ለእኔ
ክብር ነው። ሰውነቴ ቢከሳ፤ ሥጋዬ ቢ
ጐዳ፤ እግዚአብሔር በምድርና በምድራ
ውያን መካከል ውበቴን አርግፎ በሰ
ማይ ሊያስጌጠኝ መሆኑን ስለማውቅ
ደስ ይለኛል። ሥጋዬ ሕመም ሲሰማው
እግዚአብሔር ከደዌ ነፍስ ሊሸሽገኝ
መሆኑን አስባለሁ። ምኞት ሲሰማኝ
ለምን እንደ ምተጋ ዐውቃለሁና መኀሳ
ቆሌ እግዚአብሔር ለማታልፈው መንግ
ሥቱ ሲያዘጋጀኝ፤ ከምታልፈው ዓለም
ቅልውጥ ሊነጥለኝ ነውና አልከፋም፤
የዘላለምን ሕይወት ተስፋ አደርጋለሁ
እንጂ። «ሥርዓትህን እማር ዘንድ
ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።»
መዝ.118÷71።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር


በአዲስ መልኩ የተዘጋጀውን የማኅበሩን ዌብ ሳይት ይጎብኙ

http://www.eotc-mkidusan.org

በማኅበረ ቅዱሳን
የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ

የተለያየ መልክና ዲዛይን ያላቸው÷ ለአልባሳት
መሥሪያ የሚሆኑ የግሪክ ብትን ጨርቆችን
እና የግሪክ ሪቫን በጣቃና በሜትር እናከፋፍላለን ፤
ይጎብኙን።

ስልክ:- 011-156-67-88/011-6551399


# አቡነ ዮሐንስ...

/ከገጽ ፳፱ የዞረ/

አንድ ዕድል ይሰጣል። እንዲያውም
ለደ ቡቡ የአገራችን ክፍል ሰፊ ዕድል
ይሰ ጣል። የሥራ ቋንቋችን አማርኛ
የማስተማሪያ ቋንቋችን እንግሊዘኛ
ነው። ቀደም ሲል ከትምህርት ቤቱ
ተመርቀው ዛሬ በታላቅ ደረጃ
የሚገኙ ሊቃውንትና መምህራን
አሉ። ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሳሉ ሙዓ
ለ ሕፃናቱ ጠንካራ ነበር። በዚያ
ወቅት ከነበሩት ዛሬ ብዙዎቹ
ካህናትና መሪጌቶች ናቸው፤
በታላላቅ የሐላፊነት ቦታ የተቀመጠ
ም አሉ። ዛሬ የኮሌጃችን የሐዲስ ኪ
ዳን መምህር የኾኑት ሊቀ
ሊቃውንት ያሬድ ካሣን ብንጠቅስ
ከልጅነታቸው ጀምረው ያስተማሯ
ቸው ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ናቸው።

ኮሌጅ በአሁኑ ወቅት 25 የዲ
ግሪ ደቀ መዛሙርት፣ 43 የዲፕሎማ
ደቀ መዛሙርት፣ 10 የመጻሕፍት
ትርጓሜ ደቀ መዛሙርት፣ 16
ሠልጣኝ ካህናት፤ በጠቅላላ 94 ደቀ
መዛሙርት ተቀብሎ በማስተማር ላይ
ይገኛል። በመደበኛ፣ በኮንትራትና
በትርፍ ጊዜ /Partime/ የሚያገለግሉ
68 የአስተዳደርና የአካዳሚክ ሠራ
ተኞች አሉት። ከነዚህ ውስጥ ሁለት
የውጭ አገር ዜጎች /ሁለተኛ ዲግሪ
ያላቸው አንድ ሕንዳዊ ቄስና አንድ
መነኩሴ መምህራን፣ ግሪክኛ
የሚያስተምሩ አንድ የውጭ ዜጋ/
ይገኙበታል። በሌላ በኩልም በሥሩ
በሚያስተዳድረው የከሣቴ ብርሃን
አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
ቤት ከአንደኛ እስከ 10ኛ ክፍል
2000 ያህል ተማሪዎችን በ56 አስተ
ማሪዎችና የቢሮ ሠራተኞች እያስተ
ማረ የአካባቢውን ኅብረተሰብ በማገል
ገል ላይ ይገኛል።

## ነገ

ለንስሐ ነገ
ለለውጥም ቀጠሮ
ምርጫዬ ኾኑና ፣
ድንገት ስጋት ገባኝ
ነገስ ያንተ ባይሆን
በሚሉት ፈተና።

ተክለ ጽዮን
ዘፈ/ገ/ቅ/ጊዮርጊስ

## ዘመን ሲታደስ

እኛ'ኮ ለዘመን
ክንፎቹ አይደለንም
ሰንኮፍ ነን ለገላው
በታደሰ ቁጥር
እምንቀር ከኋላው።

መ/ር ይርጋ ጥበቡ
ባሌ- ጊንር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org


# አቡነ ዮሐንስ እና ከሣቴ ብርሃን

/ካለፈው የቀጠለ/

*ባለፈው እትማችን ከትግራይ የጉዞ ዘገባችን የብፁዕ አቡነ ዮሐንስን ዜና ሕይወትና ሥራዎች ማቅረብ መጀመራችን ይታወሳል:: የአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንን ት/ቤት ስለ ማቋቋማቸው የተመለከተውን ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል እነሆ::*



አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን



ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ

ለተማሪዎች የሚበቃ ምግብ፣ ልብስ፣ ለመምህራን ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ የሚኾን ገንዘብ በብዛት ማስፈለጉ የሚያከራክር አይደለም:: ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር በነበራቸው ቅርበት ንጉሠ ነገሥቱ ትምህርት ቤቱን መርቀው ከከፈቱ በኋላ :- "ሲሆን ቋሚ በጀት ካልኾነ ደግሞ ለማቋቋሚያ የሚበቃ ገንዘብ ይመድቡልኝ" ብለው ነበር:: ንጉሡ ግን ተራ ርዳታ ለማድረግ እንኳ አልፈቀዱም:: ጋዜጠኛው ትምህርት ቤቱን ተዘዋውሮ ካየ በኋላ ይህን አስታውሶ ብፁዕነታቸውን:- «ይህን ሁሉ ሕንጻ ሠርተዋል፤ በጀት ግን አላገኙም፤ መተዳደሪያውን ይዘውለታልን?» ብሎ ጠየቃቸው:: ብፁዕነታቸው ሲመልሱ:- «ሕዝቡን አስተባብረን ለምነን ሕንጻውን አቁመነዋል፤ ሕንጻው ደግሞ በበኩሉ ቁሞ ይለምን እንጂ.» በማለት ሐዘናቸውን ገልጸዋል::

በወቅቱ ወደ ከሣቴ ብርሃን ሰላማ አዳሪ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚመረጡ ካህናት መመዘኛቸው:- በከፍተኛ ደረጃ በቂ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላቸው፤ ለመማር፣ለማወቅ ፍጹም ፍላጎት ያላቸው፤ ተምረውና ዐውቀው እስከ መጨረሻው ቤተ ክርስቲያናቸውን ለማገልገል ቁርጥ ሐሳብ ያላቸው፤ ቢያንስ የዲቁና መዓርግ ያላቸው እንዲኾኑ ታስቦ ነበር::

በአዳሪ ትምህርት ቤቱ እንዲሰጥ ታቅዶ የነበረው የትምህርት ዓይነት ብዙ ቢሆንም በቅድሚያ ግን:-

ሀ. የእንግሊዘኛ ቋንቋ፣የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታውያን ቋንቋዎች (የብሉይ ኪዳን ዕብራይስጥ፣የሐዲስ ኪዳን ግሪክ)

ለ. ትምህርተ ሃይማኖት÷ምሥጢረ መለኮት (Theology)

ሐ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን ልዩነትና ግንኙነት የሚያስረዳ በየጊዜው የተፈጸመ ታሪክ፤

መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

በጠቅላላው ዘመናዊውን ትምህርት ከመንፈሳዊ ትምህርት ጋር አዋሕዶ÷ አስማምቶ መስጠት የሚል ዕቅድ ነበር:: ይህ በዘመናዊ ትምህርት በኩል ያለው ነው:: በጥንታዊው ትውፊታዊ ሥርዓተ ትምህርት ለመስጠት የታሰበው አራቱ ጉባኤያት (መጻሕፍተ ብሉያት፣መጻሕፍተ ሐዲሳት፣መጻሕፍተ ሊቃውንት፣ መጻሕፍተ መነኮሳት)፣ድጓ፣ቅኔ፣አቋቋም ነበር::

የብፁዕነታቸው ሐሳብና ዕቅድ፣ በመጀመሪያው ዓመት ከየገዳማቱና አድባራቱ እየተመረጡ ወደ ኮሌጅ የሚገቡ ካህናት 200 ኾነው፤ የሚማሩት ትምህርት በክፍለ ትምህርት ተከፋፍሎ (Departmentalized)ነበር:: ይኸውም ኅምሳዎቹ በቤተ ክርስቲያኒቱ መደበኛ ሞያ እየተመረቁ የጉባኤ መምህራን እንዲኾኑ፤ ኅምሳዎቹ በአስተዳደር ትምህርት ተመርቀው፣ገዳማትንና አድባራትን የሚያስተዳድሩ፤ ኅምሳዎቹ ወደ ውጭ አገር እየተላኩ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉባቸውን ጥንታውያን ቋንቋዎችን በብቃት በማጥናት ወደ አገራቸው ተመልሰው መጻሕፍትን የሚተረጉሙና በኮሌጅ የሚያስተምሩ፤ ኅምሳዎቹ ደግሞ በዘመናዊ የስብከት ዘዴ እየተመረቁ ሕዝብን በጥራትና በብቃት እንዲያገለግሉ ለማድረግ እንደ ነበር፤ በወቅቱ የተጻፉ ሰነዶች ያስረዳሉ:: ዛሬ ለተዘረጋው ሥርዓተ ትምህርት መሠረቱ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ አስጠንተው በእንግሊዘኛና በአማርኛ ያቆዩት ጥናት ነው:: ብፁዕነታቸው እንደ መምህሩ አስተያየት÷ እንደ ተማሪው ትጋት የሚወሰነውን የቀድሞውን የጉባኤ ቤት ሁኔታ መልክ ለማስያዝ ያስቡ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የተበላሸ አሠራርን በተመለከቱ ጊዜ ሁሉ የሚናገሩት ነገር ነበር:: «አይ ግድ የላችሁም÷ የጥንቱን ሥርዓተ ትምህርት ከሣቴ ብርሃንን ሳስመርቅ÷ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን ሳስመርቅ አሳያችኋለሁ» ይሉ ነበር:: ቅዱስ ሚካኤልንም ኾነ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ትምህርት ቤትን እንደ ሠርቶ ማሳያ ሊጠቀሙበት ነበር የሚያስቡት፤ ይኸውም ተማሪዎቹ በትምህርት ቤቱ የገበዩትን ዕውቀት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይፈጽሙት ዘንድ ነው::

እንደ ብፁዕነታቸው አሳብ ንጉሠ ነገሥቱ የተጠበቀውን «የሕይወት እስትንፋሳቸውን» በትምህርት ቤቱ ላይ እፍ አለማለታቸው አላስደነገጣቸውም:: ይልቁንም በበለጠ እንዲሠሩ አበረታታቸው እንጂ:: እንደ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ካሣ አገላለጥ:- ብፁዕነታቸው ወደ አሰቡበት ለመድረስ የእንቅስቃሴአቸውን መንገድ ለወጡ:: ይኸውም ለኢትዮጵያ የግብርና ሚኒስቴር ሁኔታውን ለማስረዳት ባደረጉት ጥረት በደቡብ ትግራይ በመኾኒ ወረዳ ለአዳሪ ቤቱ መተዳደሪያ ለም የነበረ አንድ ጋሻ መሬት ተረከቡ:: መሬቱ ለምቶ ሐሳባቸው ተሳክቶ አጥጋቢ ምርት በማፈስ የድካማቸውን ፍሬ ለማየት በቅተው ነበር:: ወደ አዳሪ ትምህርት ቤቱ የሚገቡትን መምህራንና ካህናት መመልመል ተጀምሮ ነበር:: ነገር ግን በዚህ መካከል በ1966 ዓ.ም በሀገራችን ከባድ ድርቅ ተነሥቶ ይህ ነው የማይባል እልቂት በሕዝቡ ላይ አስከተለ:: ድርቁ በፈጠረው የረኀብ መቅሠፍት ብዙ ሕፃናት ያለ ወላጅ÷ ያለ አሳዳጊ ብቻቸውን ቀሩ:: በዚህ ጊዜ ከሁሉ የሚቀድመው የሰውን ሕይወት ማትረፍ እንደ ኾነ ብፁዕ አባታችን ተገነዘቡ::

እንዲህ ላለው በጎ ሥራ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ግንባር ቀደም መኾን አለባት አሉ:: ሐሳባቸው የሕፃናቱን ሕይወት ወደ ማትረፍ አዘነበለና:- «ሕፃናትን እየረዱ ማስተማር፣እያስተማሩ መርዳት» የሚል መሪ ቃል በማንሣት በቅድሚያ ሕፃናትን መርዳት፣ማስተማር እንደ ሚገባ ከውሳኔ ደረሱ::

እነሆ÷በሽራሮ ወረዳ ከሚገኘው ኩናማ ኅብረተሰብ ኀምሳ ሕፃናት፣ ከመኾኒና ከጨርጨር ወረዳዎች ኀምሳ ሕፃናት፣ ከቀሩት የትግራይ ወረዳዎች 100 ሕፃናት በድምሩ ለ200 ሕፃናት ዕድል ለመስጠት በብፁዕነታቸው የታሰበ ነበር:: ስለሆነም መስከረም አንድ ቀን 1967 ዓ.ም. እነዚህ 200 ሕፃናት እንዲሰባሰቡ ተደረገ:: በትምህርት ገበታ በመቀበልም የከሣቴ ብርሃን አዳሪ ትምህርት ተመርቆ ተከፈተ:: ኋላም አመራሩንና አሠራሩን በማሻሻል እስከ 400 ሕፃናት ለመቀበል ችሏል:: እንዲህ ባለ አኳኋን የአዳሪ ትምህርት ቤቱ በሺሕ የሚቆጠሩ ሕፃናትን ተከባክቦ አሳድጓል:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ለተቋቋሙት የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶች በሙሉ መነሻ መሠረት ኾኗል::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ አዳሪ ትምህርት ቤቱን በዚህ መልኩ ካደራጁ በኋላ ስለ ጠቅላላ ትምህርት ቤቱ፣ላይ ታች ሲሉ፣ ከአንዳንድ ርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በመላላክ ላይ ሳሉ ከአራት የመማሪያና ሌሎች የተወሰኑ ክፍሎች በቀር ትምህርት ቤቱ በደርግ መንግሥት ተወረሰ:: አዳሪ ቤቱ ግን አልተወረሰም:: ምክንያቱም ርዳታው የሚመጣው በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ስለነበረ ነው:: ምንም እንኳ ትምህርት ቤቱ ቢወረስም ብፁዕነታቸው እንደ ወትሮአቸው ወደ ትምህርት ቤቱ መመላለስ አላቋረጡም:: እንደ ልማዳቸው ተክል በመትከል፣ የተተከለውን ከማረም፣ ከመኮትኮት አላረፉም:: ከዕለታት አንድ ቀን አትክልቱን በሚኮተኩቱበት ጊዜ አንድ ሰው:- «አባታችን ትምህርት ቤቱ'ኮ ተወርሷል፤ የእኛ አይደለም፤ ለምን ይደክማሉ?» አላቸው:: አባታችን ግን «ቢወርሱት ወዴት ይወስዱታል? አሁንም የሚማሩበት ልጆቻችን ናቸው:: መቼስ የሠራነው ለሕዝብ ጥቅም እንዲኾን ነው:: ለሕዝብ ጥቅም እስከ ዋለ ድረስ ግድ የለም፤ አናዝንም:: ደግሞም መመለሱ አይቀርም:: በጊዜው ጊዜ ይመለሳል:: ዛሬ እነርሱ ቢይዙትም ነገ ተመልሶ የቤተ ክርስቲያን ይዞታ ይሆናል» ብለው ነበር::

ሊቀ ትጉኃን ላእከ ታረቀ:- ይህ የብፁዕነታቸው ቃል «ትንቢታዊ ንግግር» ነበር ይላሉ:: እውነትም ጊዜው ሲደርስ ብፁዕ አባታችን የተናገሩት ቃል ርግጥ ኾኖ በ1987 ዓ.ም ትምህርት ቤቱ ተመልሶ ለባለቤትዋ ቤተ ክርስቲያን ተሰጥቷል:: ንብረቷ ኾኗል:: የአመላለሱን አኳኋንና ከዚያ በኋላ ያሉትን ሁኔታዎች ሊቀ ትጉኃን እንደ ሚከተለው ያብራራሉ::

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት ተቋሙን ሲወርስ የጦር ካምፕ ነበር ያደረገው::

ከጊዜ በኋላ ደግሞ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ሲያስተምርበት ቆይቷል:: የደርግ /ኢ.ሕ.ዴ.ሪ መንግሥት በ1983 ዓ.ም ከወደቀ በኋላ በጊዜው የነበሩት የመማሪያ ክፍሎቹና በውስጣቸው የሚገኙት ንብረ ቶች ተጎሳቁለው ነበር:: እንዲያውም ትዝ የሚለኝ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከስ ደት እንደ ተመለሱ የብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተዝካር ዕለት እዚህ መጥተው ሳለ ተመልክተውት አልቅሰዋል:: «እናንተ ከአሁን በኋላ የብፁዕ አቡነ ዮሐንስን ያህል መሥራት ሳይሆን የሚፈለግባችሁ የብፁዕ አቡነ ዮሐንስን ንብረት መጠበቅ ከቻላችሁ እንደ ሠራችሁ ይቆጠራል» ያሉትን አስታውሳለሁ:: የኾነው ኾኖ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በነበሩት ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አማካይነት ለክልሉ አስተዳደር ጥያቄ ቀረበ:: አስተዳደሩም ትምህርት ቤቱን በአንድ ጊዜ መመለስ እንደ ማይችል፥ ደረጃ በደረጃ ግን ክፍሎቹን መልቀቅ እንደሚቻል ከስምምነት ተደረሰ:: ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ያሉት ክፍሎች በተከታዮቹ ስድስት ዓመታት ውስጥ ተለቀቁ:: እኛም አንዱ ክፍል ሲለቀቅ አንደኛ፥ ሁለተኛው ክፍል ሲለቀቅ ሁለተኛ... እያልን እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ በማስተማር ቆየን::

ከዚህ በኋላ ግን ቀድሞም ብፁዕነታቸው ተቋሙ እንዲከፈት ያሰቡት በኮሌጅ ደረጃ የነገረ መለኮት ትምህርት እንዲሰጥበት ነበር:: ስለሆነም የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ እንዲኾን አልተፈለገም:: ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ኅዳር 12 ቀን 1992 ዓ.ም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር መቐለ በመጡ ጊዜ በቅዱስ ሚካኤል ክብር በዓል ላይ ጥያቄው ተነሣ:: ሕንፃው ለታቀደለት ዓላማ ሳይውል ለ30 ዓመታት ከቆየ በኋላ በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ ይገኝ ነበር:: እድሳት አልተደረገለትም:: ንብረቶችም ጥገና ሳያውቃቸው ወላልቀው ተሰባብረው የተረከብንበት ሁኔታ ነው የነበረው::

ታድያ ቅዱስነታቸው በዚያ ዕለት ቡራኬ ሲሰጡ የብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሐሳብና ዕቅድ በተግባር ለመተርጎም ቅዱስ ሲኖዶስ እንደ ሚያምንበትና እንደ ሚመክርበት ቃል ገቡ:: በቅጥሩ የታነጸው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በካቴድራል ደረጃ እንዲጠራ ሠየሙ ይህ ቤተ ክርስቲያን «ለመንፈሳዊ አገልግሎት፣ ለትምህርት ቤቱም ታላቅ ዋስትና:: ይሆናል» በሚል ዕቅድ ኅዳር 12 ቀን 1968 ዓ.ም መሠረቱ ቀጥሎ ኅዳር 12 ቀን 1970 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ መሪነት ቅዳሴ ቤተ ተከናውኗል:: በውስጡ የቅዱስ ሚካኤልን ጨምሮ የአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ የነገሥታቱ የአብርሃ ወአጽብሐ ታቦታት ይገኛሉ:: በ1975 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኑ «ደብረ ሰላም»፣ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደሪ «መልአከ ሰላም» ተብሎ እንዲሠየም ተደርጓል:: በቅዱስነታቸው አቅራቢነት ጥቅምት 15 ቀን 1993 ዓ.ም ለተሰበሰበው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ አጀንዳው ቀረበ:: የሚከተሉት ውሳኔዎችም ተላለፉ::

1. በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ታስቦ የነበረው መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲቋቋም፤
2. ኮሌጁ «አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ» ተብሎ እንዲጠራ፤
3. በጀቱ ተጠንቶ እስኪቀርብ ድረስ በየዓመቱ ብር 100,000 እየተሰጠ እንዲቆይ የሚሉት ናቸው::

በዚህም መሠረት የቅዱስ ሲኖዶስን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግና ኮሌጁን በተሟላ መልኩ ለማቋቋም ይቻል ዘንድ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር በመነጋገር ጥናቱን የሚያካሂዱ ቡዱኖች ተቋቋሙ:: እነሂም: - 1/ የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ ቡድን 2/ የበጀትና መዋቅር ቡድን 3/ የምሕንድስና ቡድን ናቸው:: የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቦርድ አባላት የሚገኙበት ቡድን ጥናቱን ለመገምገም መቐለ ድረስ መጣ:: ጥናቱ ተገምግሞ ግንቦት ስድስት ቀን 1993 ዓ.ም ለተሰበሰበው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ቀረበ:: ኮሌጁ «ቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን» በሚል ስም እንዲከፈት በተወሰነው መሠረት ለአምስት ዓመት የሚሠለጥኑ ስምንት ደቀ መዛሙርትን ለዲግሪ መርሐ ግብር፣ ለሦስት ዓመት የሚሠለጥኑ 15 ደቀ መዛሙርትን ለዲፕሎማ መርሐ ግብር፣ አምስት ደቀ መዛሙርት የብሉያት መጻሕፍት ትርጓሜ፣36 ካህናትን ለአራት ወራት ሥልጠና በመቀበል ጥቅምት ሦስት ቀን 1994 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ፣ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ተመርቆ የመማር ማስተማሩን ሥራ ጀምሯል:: በ1996 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የዲፕሎማ መርሐ ግብር ደቀ መዛሙርትን አስመርቀናል::

በዲፕሎማና በዲግሪ መርሐ ግብሮች የምናሠለጥናቸው ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ወስደው ለዲፕሎማ ሁለት ነጥብና ከዚያ በላይ፣ ለዲግሪ 2.4 እና ከዚያ በላይ ውጤት ያላቸው፤ ሥልጣነ ክህነት የተቀበሉ መኾን አለባቸው:: በሥርዓተ ትምህርቱ ዓይነት ካልኾነ በቀር በጥንቱና በዘመናዊ መልክ እየተሰጡ ባሉት መርሐ ግብሮች መካከል በምግብና በመኝታ ልዩነት አይደረግበትም:: በሥርዓተ ትምህርቱ መሠረት የብሉያት መጻሕፍት ትርጓሜ ለሰባት ዓመት፣ የሐዲስ ኪዳን ለአምስት ዓመት፣ በሰርተፊኬት ደግሞ የአራት ወራት ሥልጠና ይሰጣል:: በቅርቡ ይህ ጉብኝት መጋቢት 22 ቀን 1997 ዓ.ም ከመድረጉ ሁለት ሳምንት በፊት/ የማታ መርሐ ግብር ተጀምሮ ጥቂት ተማሪዎችን ተቀብለናል:: በየትኛውም መርሐ ግብር ያሉት ሠልጣኝ ደቀ መዛሙርት ከየአህጉረ ስብከቱ የተውጣጡ ናቸው:: ለየአህጉረ ስብከቱ አንድ

/ወደ ገጽ ፳፯ ዞሯል/



የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



*«አቤቱ! እንደ አዘዝክ ዛሬ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፡፡ ዐይኖቼ ትድግናኅን አይተዋልና፡፡»*
/ሉ.ቃ.፪÷25-35/

# ልደተ ስምዖን

ጌታቸው በቀለ

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ከምታከብራቸው የጌታችን ንዑሳን በዓላት አንዱ «ልደተ ስምዖን» ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የካቲት ስምንት ቀን በየዓመቱ የልደተ ስምዖንን በዓል ታከብራለች፡፡ «ልደተ ስምዖን» የተባለበትም ምክንያት ኢየሱስ ክር ስቶስ በአርባ ቀኑ ከእመቤታችንና ከዮሴፍ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ሲሄድ፤ አረጋዊው ስምዖን ሕፃኑን ከእመቤታችን ተቀብሎ በክንዱ በአቀፈ ጊዜ ከአርጅናው ታድሷል፡፡ የበዓሉ የጌታ ሆኖ ሳለ በዓሉ መጠሪያ «ልደተ ስምዖን» ተብሏል፡፡ ይኸውም ካህኑና አረጋዊው ስምዖን ከአርጅናው መታደሱ እንደ ዳግም ልደት ተቆጥሮ መሆኑን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስተምራሉ፡፡

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ልደትን አምልተው አስፍተው ሲተረጉሙትና ሲፈቱት እንዲህ በማለት ያብራሩታል፡፡ ልደት፡-

## ካለመኖር ወደ መኖር መምጣት /መገኘት/ ነው፡፡

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ሰማይና ምድርን በውስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ከእግዚአብሔር መፈጠራቸውን /መገኘታቸውን/ «የሰማይና የምድር ልደት» በማለት ሲያስረዳ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፡፡» በማለት ተናግሯል፡፡ ዘፍ.1÷1፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት ሲልም ኦሪት ዘልደት ብሎ ይገኛል፡፡

## የመንፈስ ልደት

ከተጠቀሱት ልደታት ሁሉ የሚበልጠው ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን ሴቶች በተወለዱ በሰማንያ ቀን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ የሚወለዱት የመንፈስ ልደት ነው፡፡

## ጌታችን በቤተ መቅደስ

በኦሪት ሕግ ማንኛውም አማኝ ልጅ በወለደ በስምንተኛው ቀኑ ሕፃኑን ማስገረዝ የተለመደ ሕግ ነበር፡፡ እንዲሁም ሕፃኑ ወንድ ከሆነ በአርባ ቀን÷ ሴት ከሆነች በሰማንያ ቀንዋ ለመሥዋዕት የሚሆነውን መባዕ በወላጆቹ አማካይነት ይዞ/ይዛ ወደ ቤተ መቅደስ መግባትና በእግዚአብሔር ፊት መታየት ነበረበት/ነበረባት፡፡ ጌታችን ሥርዓተ ኦሪትን፣ ትንቢተ ነቢያትን ሊፈጽም እንጂ ሊያፈርስ ስላልመጣ ሕገ ኦሪትን ፈጽሟል፡፡ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም፡፡» ማቴ.5÷17፡፡ ለሙሴ ሕግን የሰጠ ሲሆን የሙሴን ሕግ ፈጽሟል፡፡ ጌታችን በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ፡- «በስምንተኛው ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ» /ዘሌ.12÷3/ እንዳለ ጌታ በተወለደ በስምንተኛው ቀኑ ወደ ቤተ ግዝረት ገብቷል፡፡ ከዕለተ ዐርብ በፊት ደሙ አይፈስምና በግብረ አምላካዊ ተገዝሮ ተገኝቷል፡፡ ጌታችን ከተወለደበት ታኅሣሥ 29 ቀን ጀምሮ ሲቆጠር ስምንተኛው ቀን /በዓለ ግዝረቱ/ የሚውለው ጥር ስድስት ቀን ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ግዝረት ብላ የምታከብረው ጥር ስድስት ቀን ነው፡፡ /አባ ጎርጎ ርዮስ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ገጽ 117/፡፡ /ስንክሳር÷ ዘወርኀ ጥር/፡፡

ጌታችን በተወለደ በአርባ ቀኑ በዮሴፍና በእናቱ አማካይነት መባውን ይዘው ቤተ መቅደስ በመግባት ሥርዓቱን ፈጽሞ አል፡፡ ሉቃ.2÷22-24፡፡ ወደ ቤተ መቅደስ የገባው የካቲት ስምንት ቀን መሆኑን ስንክሳሩ ይገልጻል፡፡ እንደ ሥርዓተ ኦሪት መሥዋዕት ሊያቀርቡለት ወደ ቤተ መቅደስ አመጡት፡፡ «ወአመ ተፈጸመ ዕድሜ ንጽሖሙ፤ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ» ይላል፡፡ በሌሎች ሴቶች ልማድ መናገር ነው እንጂ በእመቤታችንስ ይህ ሁሉ የለባትም፡፡ «በከመ ሕገ ሙሴ ወሰድዎ ኢየሩሳሌም ያቅምዎ ቅድመ እግዚአብሔር፤ ከእግዚአብሔር ፊት ሊያቆሙት ይኸውም እንደ ኦሪት ሥርዓት እጅ ያስነሡት ዘንድ ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት፡፡» ሕጉም «ወንድ በተወለደ በአርባ ቀን ሴት በተወለደች በሰማንያ ቀንዋ ወደ ቤተ መቅደስ ይወሰዱ» ይላል፡፡ ኩፋሌ 4÷9-13፤ ዘሌ. 12÷8፤ ዘጸ.13÷2፤ ዘኁ.8÷11፡፡

በጌታ ሕግ «የእናቱን ማኅፀን የሚከፍት÷ በኩር ሆኖ የሚወለድ ወንድ ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ የእግዚአብሔር ልዩ አገልጋይ ይባላል፡፡» ተብሎ በኦሪት እንደ ተጻፈ በጌታ ፊት ሊያቆሙት በጌታም ሕግ ሁለት ዋልያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች ስለ እርሱ መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት፡፡ ወላጆች ከዚህ የሚማሩት ልጆችን በተወሰነው ቀን ወደ እግዚአብሔር ቤት መውሰድን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የአዲስ ኪዳን ዘመን ወላጆች ልጆቻቸውን ወንዶችን በአርባኛው ቀን ሴቶችን በሰማንያኛው ቀን ወደ አማናዊቷ ቤተ መቅደስ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ ክርስትና ያሥነሷቸዋል፤ የእግዚአብሔር ልጆች ያደርጓቸዋል፡፡

## ስምዖን አረጋዊ በቤተ መቅደስ

በኢየሩሳሌም ከተማ ስምዖን የሚባል አንድ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር፡፡ ጻድቅና ትጉኅ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ከክፋት ከቂም በቀል የራቀ ደግ ሰው ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበር፡፡ በተዋሕዶ ሰው የሚሆነውን ወልደ እግዚአብሔርን፣ ቃለ እግዚአብሔርን ሳያይ እንደ ማይሞት መንፈስ ቅዱስ ነግሮት ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ራሱን የቻለ ትልቅ ታሪክና ጥልቅ ምሥጢር አለው፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ መሠረት በ284 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ዳግማዊ በጥሊሞስ ፊላዲልፎስ የተባለ፣ በዓለም የታወቀ፣ በጥበብ የተራቀቀ ገናና ንጉሥ ነበር፡፡ ከጥበቡ ብዛት፣ ከመንግሥቱ ስፋትና ከገናንነቱ የተነሣ በግሪክ ኃያል የሥልጣኔ ዘመን /Hellenism/ እንደ ሰም አቅልጦ እንደ ገል ቀጥቅጦ ሰፊ ግዛትን ገዝቷል፡፡ ያገሩን ሁሉ ቋንቋ ያውቅ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ «ምን ቀረኝ?» ብሎ አማካሪዎቹን ነገሥታቱን ጠየቀ፡፡ «እነርሱም የቀረህ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ብዙ ጥበብ፣ ብዙ ምሳሌ




© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያለባቸው አርባ ስድስቱ መጻሕፍተ ብሉያት ቀርተውኻል:: እነዚያን አስመጥተህ ብት መለከት ብዙ ጥበብና ቁም ነገር ታገ ኛለህ::» ብለው ነገሩት::

በጥሊሞስም በእስራኤል ሠልጥኖ ባቸው ስለ ነበር፥ «ጸሐፍቱንም መጻሕፍቱንም ስደዱልኝ» ብሎ መልእክት ላከ:: እነርሱም መጻሕፍቱን ከሰባ ሁለት ጸሐፍት ጋር ሰደዱለት:: ሁለቱ ሊቃውንት ከሀገሩ ርቀት የተነሳ በዋዕየ ፀሐይ ከመንገድ ሙተው ቀርተዋል:: ሰባው ሊቃውንት /ሰብዐ ሊቃናት/ ንጉሡ ዘንድ ደርሰዋል:: ከሰባው ሊቃውንት አንዱ ስምዖን አረጋዊ ነበር:: ንጉሥ በጥሊሞስም የዕብራይስጡን ብሉይ ኪዳን ወደ ጽርዕ ቋንቋ እንዲተረጉሙ አዘዛቸው::

በጥሊሞስ ሊቃውንቱ የሚጽፉበትን አንድ አንድ ድንኳንና የሚያገለግሏቸውን አንዳንድ ብላቴና አድርጎ ሰጣቸው:: መጻሕፍቱን ተከፋፍለው በሚጽፉበት ጊዜ ለስምዖን መጽሐፈ ኢሳይያስ ደረሰው:: ሲጽፍም:- «ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች::» ከሚለው አንቀጽ ደረሰ:: ኢሳ.7፥14:: ስምዖን በሁኔታው ተጠራጠረ:: «ድንግል ትፀንሳለች» ማለት ከዚያ በፊት ተሰምቶም፣ ተደርጎም አይታወቅም ነበርና ስምዖን ተጨነቀ:: ድንግል ትፀንሳለች፥ቢባል ስንኳን የአሕዛብ ንጉሥ ይቅርና የእስራኤል ንጉሥ ቢሆንስ ይቀበለኛል?» ብሎ ተጠራጥሮ «ወለት ትፀንስ፤ ሴት ትፀንሳለች፤ ትወልድማለች» ብሎ ጻፈ:: እንቅልፍ መጥቶበት ተኝቶ ሲነቃ እንደ ገና ቢያይ ያንን ያረመውን «ሴት» የሚለው ቃል ተፍቆ «ድንግል ትፀንስ» የሚል ሆኖ አገኘው:: ሁለተኛም ፍቆ «ወለት ትፀንስ፤ ሴት ትፀንሳለች» ብሎ ጻፈ:: በዚህ ዓይነት ሦስት ጊዜ «ድንግል» የሚለውን እየፋቀ «ሴት» ቢልም እየተለወጠ ድንግል የሚል ንባብ ሆኖበታል:: ለአራተኛ ጊዜ እፍቃለሁ ሲል፤ የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ «የተጠራጠርከውን ከድንግል የሚወለደውን እስከ ምታየውና እስከ ምትታቀፈው ድረስ ሞትን አትቀምስም» አለው:: «ኢትመውት ዘእንበለ ትርአይ መሲሖ ለእግዚአብሔር፤ በጌታም የተቀባውን ሳታይ አትሞትም» ብሎ መንፈስ ቅዱስ ነግሮታል:: ከዚህም በኋላ ጌታችን እስከ ተወለደና ወደ ቤተ መቅደስ እስከ ገባበት /የካቲት 8/ ቀን ድረስ ስምዖን 300 ዓመት ኖረ:: ስምዖን መላው ዘመኑ 500 ዓመት ሲሆን በዚያን ጊዜ ይህን ሲጽፍ ዕድሜው 250 ዓመት ይሆነው እንደ ነበር በታሪክ ተጽፎአል:: /አባ ጎርጎርዮስ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያን ታሪክ፤ ቀሲስ ደጀኔ ሽፈራውና ቀሲስ እሸቱ ታደሰ፥ ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ::

ይህ የሆነበት ምክንያት ጥበበ እግዚአብሔር ነው:: ወደፊት በዕብራይስጥ የተጻፉትን ቅዱሳት መጻሕፍት ዓላውያን ነገሥታት ሲያቃጥሏቸው በጽርዕ የተጻፉት እንዲገኙ ለማድረግ ነው:: ከስምዖን ታሪክ የምንማረው ነገር ቢኖር የእመቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና መፋቅ እንደ ማይቻል ነው:: ቤተ ክርስቲያን ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና የምትመሰክረው የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ፣ ንባቡን በመተርጎም፣ ምሥጢሩን በመግለጥ ነው:: የድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና ፀንሶ መውለድ በሰው ዘንድ ያልተለመደ ከሰው ኅሊና በላይ ነበረ:: መልአኩም:- «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» ብሎ የደመደመው ለዚህ ነው:: ይህ ለማንም ያልተሰጠ፥ የማይሰጥም ልዩ ሀብት ነው:: ስምዖን ጻድቅና ትጉኅ መንፈስ ቅዱስም ያደረበት በመሆኑ እግዚአብሔር አስተማረው:: ሆኖም የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ሳይፈጸም አይቀርምና ከዘመኑ ደርሶ ጌታችን ከድንግል ማርያም ተወለደ:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፣ ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» /ገላ.4፥4/ እንዳለ ጌታችንም ከኃጢአት በቀር የሰውን ሕግና ሥርዓት ፈጽሟል::

አረጋዊው ስምዖን የጌታን መወለድ ሲጠባበቅ እጅግ በጣም ሸምግሎ ነበር:: በሽምግልናው የተነሳ ከመኝታው መነሣት አይችልም ነበር:: የተነገረውን ተስፋ በዐይኑ ሳያይ እንዳይሞት የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ ጻዕሩንና ድካሙን ታግሦ ኖረ:: የተነገረውን የሚያይበት ጊዜ ሲደርስ ክርስቶስ ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት ቀን ስምዖን ወደ ቤተ መቅደስ የመጣው በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ነው:: ከአልጋ ተጣብቆ ሲኖር መንፈስ ቅዱስ አነሣስቶ፣ አጽናንቶ ወደ ምኩራብ ወሰደው:: የእመቤታችን ጠባቂዋ ዮሴፍና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም በኦሪት እንደ ታዘዘ ሕፃኑን ኢየሱስን ወደ ቤተ መቅደስ ባስገቡት ጊዜ እርሱ ደግሞ ተቀብሎ አቀፈው:: በተስፋ ይጠባበቀው የነበረው እርሱ መሆኑን ዐወቀ፤ አዳኝነቱንም አመነ፤ «ወባረኮ ለእግዚአብሔር፤ ከዚሁ ጊዜ ያደረስከኝ፥ ከደዌዬ የፈወስከኝ» ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነ:: ስምዖን ሕፃኑን ጌታችንንም በታቀፈው ጊዜ ከእርጅናው የተነሳ ታውረው የነበሩ ዐይኖቹ ተገለጡ:: ሁለመናውም አዲስ ሆነ፤ መንፈስ ቅዱስም የምትጠብቀው የነበረው ሕፃን ይህ ነው ብሎ ነግሮታልና::

## የስምዖን ጸሎት:-

ካህኑ ስምዖን ጌታችንን በታቀፈው ጊዜ ከእርጅናው ታድሷል፤ ከደዌውም ተፈውሷል:: ከዚህ ያደረሰውን ፈጣሪ አመስግኗል:: ቅዱሳን በዚህ ዓለም በንቃትና በትጋት አገልግለው፤ የአገልግሎት ዘመናቸውን ሲፈጽሙ ወደ ተዘጋጀላቸው የዕረፍት ቦታ ለመግባት የስንብት ጊዜያቸውን ይናፍቃሉ፤ ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ ያምናሉ:: 2ኛጢሞ.4፥7:: »ስምዖንም በዚህ ጊዜ «ባርያህን ዛሬ በሞት ታሰናብተዋለህ [በሰላም አሰናብተው]» በማለት ከዚህ ዓለም የጻዕር ኑሮ ለመገላገል ለመነ:: በዚህ በኃላፊው ዓለም ሕይወት ታስሬ ኑሬአለሁና እነሆ አሁን አየሁህ፤ ወደ ዘላለም ሕይወት እሄድ ዘንድ አሰናብተኝ፤ ዐይኖቼ ትድግናህን አይተዋልና:: ጣር በሽማግሌ ይበዛልና ይህ ሳይጸናብኝ ውሰደኝ::» አለ::

ከዚህ ላይ የምናስተውለው ምስጢር አለ:: ስምዖን ክርስቶስን በክንዱ በአቀፈው ጊዜ ከሽምግልናው ታድሷል:: ከደዌው ተፈውሷል:: ታድያ ከሽምግልና ከታደስኩ፣ ከደዌ ከተፈወስኩ ከድካሜ መጽናናትን ከአገኘሁ በዚህች ምድር ላይ ልቆይ አላለም:: «እስመ ርእያ አዕይንትየ አድኅኖትከ ዘአስተዳሎከ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ፤ አቤቱ ዐይኖቼ ለወገኖችህ ቀድሞ ያዘጋጀኸውን አይተዋል:: እንግዲህ አገልጋይህን በሰላም አሰናብተኝ:: የተናገርከው የተስፋ ቃል ተፈጽሞልኛልና፤ «መሬት አንተ ወትገብዕ ውስተ መሬት፤ መሬት ነህና ወደ መሬትነት ትመለሳለህ::» ብለህ ለአዳም በተናገርከው መሠረት በሰላም አሰናብተኝ» ብሎ ለመነ /ጸለየ/:: ወደፊት ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከሚያዩኝ አስቀድሞ አይቻለሁ:: ይህም ለአሕዛብ ትንቢትን ተስፋን፤ ለእስራኤል ሃይማኖትን ልጅነትን ትገልጽ ዘንድ ነው አለ:: አይሁድ ጌታችንን ገርፈው በመስቀላቸውና በመግደላቸው ትንሣኤውን እያዩ በበደላቸውና በስሕተታቸው ተጸጽተው ንስሐ ባለመግባታቸው በ40 ዘመን በጥጦስ የሚመጣባቸውን መቅሠፍትና ጥፋት አስፋፍቶና አምልቶ ትንቢት ለመናገር በቅቷል:: ሉቃ.2፥23-35:: ትርጓሜ ወንጌል::

## ስምዖን ስለ ድንግል ማርያም የተናገረው:-

«ወባረኮሙ ስምዖን»፥ ስምዖን በኢሳይያስ የትንቢት ቃል መረቃቸው:: ድንግል ማርያምን «የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ:: የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ:: የእግዚአብሔርም ከተማ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል::» አላት:: ኢሳ.60፥14:: ስለ ሕፃኑ ደግሞ «እነሆ በጽዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ አለት አኖራለሁ:: በእርሱም የሚያምን አያፍርም::» ሲል ተናገረ:: ኢሳ.28፥16:: ጽዮን የተባለች ድንግል ማርያም ስትሆን ድንጋይ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ «ያም አለት ክርስቶስ ነበረ::» ብሏል:: /1ቆሮ.10፥4/:: ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱን ግንበኞች የናቁት ድንጋይ» ካለ በኋላ «በዚህ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል:: ድንጋዩ ግን የሚወድቅበትን ሁሉ ይፈጨዋል::» ብሏል::


አረጋዊው ስምዖን ከምርቃቱ በኋላ:- «ይህ ሕፃን ከእስራኤል ወገን ለብዙ ሰዎች ለልማታቸው፣ ለጥፋታቸውም በሚፈረድባቸው ገንዘብ ይፈረድባቸው ዘንድ የተዘጋጀ ምልክት ነው» አለ:: እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በተመለከተ በዕለተ ዓርብ ክርስቶስን አይሁድ በመልዕልተ መስቀል ቸንክረው ሲሰቅሉት በእመቤታችን ምን ያህል የመረረ ሐዘንና ልቅሶ እንደ ሚደርስባት ደግሞ «ወለኪሰ ይበውእ ውስተ ነፍስኪ ኲናተ፤ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» አላት:: እንደ ሰይፍ የሚከፍል ሐዘን በልቧ እንደ ሚያድር መናገሩ ነው:: የጌታ ሞት /መከራ መስቀሉ/ እንደ ጦር የምትሰማ ሐዘን ናትና እንዲህ አለ:: በነፍስሽ ያለው በልብሽ ማለቱ ነው:: ስምዖንም ስለ ጌታ እና ስለ እመቤታችን የተናገረው በመንፈስ ቅዱስ ነው:: ዛሬም ቢሆን በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በስተቀር ስለ ጌታም ስለ እመቤታችን ሁለቱም መናገር አይቻልም:: /ሉቃ.2፥33-35፤ የሉቃስ ወንጌል ትርጓሜ/::





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org



*ሐዲስ ሐዋርያ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይ ማኖት /1197-1299 ዓ.ም/*

# ሐዋርያዊነት በኢትዮጵያ እንዴት?

/ዲ.ን ዳንኤል ክብረት /

ክርስትና በዓለም ላይ የተስፋፋው በአራት መንገዶች ነው። እነ ሆም፦ በሐዋርያዊ አገልግሎት፣ በሕዝቦች እንቅስቃሴ፣ በጦርነት እና በተጠቃሚነት ምክንያት ናቸው። *በሐዋርያዊ አገልግሎት*፦ ሲባል ክርስትናን ለመስበክና ሕዝቡን ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ለመመለስ በተ ሠማሩ መስተጋድላን መነኮሳት፣ ካህናተ እግዚአብሔርና ሰባክያነ ወንጌል አማካይነት ማለት ነው። ከዐሥራ ሁለቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ በየዘመኑ የተነሡ የወንጌል ገበሬዎች መከራውን ሳይሰቀቁ፣ በባዕድነት ሳይጨነቁ ከሀገር ወደ ሀገር ተዘዋውረው የወንጌልን ዘር ዘርተው የቅድስናን ፍሬ አፍርተዋል።

*የሕዝቦች እንቅስቃሴ ሲባል*፦ በንግድ፣ በአዳዲስ ቦታዎች በመሥፈር፣ ችግሮችን ለመሸሽ ሲባል በሚከሠት ስደት፣ በቅጣት ወይም በግዞት ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ በመላክ፣ ሀገር በማሰስ፣ ወዘተ አማካይነት እግረ መንገድ /አጋጣሚው በፈጠረው ምቹ ሁኔታ/ የሚሠራ ሐዋርያዊ አገልግሎት ነው። በቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ሞት ምክንያት በኢየሩሳሌም ከተማ ተመሥርታ የነበረችው 8000 ማኅበር ስትበተን፦ «የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።» ይላል። /የሐዋ.8÷4/። ከዚህም በተጨማሪ በዘመነ ሰማዕታት ዲዮቅልጥያኖስን የመሳሰሉ ጨካኝ ነገሥታተ ሮም ያደርሱት ከነበረው መከራ የሸሹ ክርስቲያኖች በየሀገሩ ክርስትናን አስፋፍተዋል። ተስዐቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በዚህ ምክንያት ነበር። ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ የተባለው ወንድሙ ከዘመዳቸው ሜሮጵዮስ ጋር ከጢሮስ ተነሥተው በቀይ ባሕር በኩል ወደ ሕንድ አቅጣጫ በጀልባ የሚጓዙት ለንግድ ተግባር ነበር። ነገር ግን በአዱሊስ ወደብ ወንበዴዎች ዘመዳቸውን ሜሮጵዮስንና የጀልባዉቱን ቀዛፊዎች ገድለው ንብረታቸውን ዘርፈው ከጉዞ አሰናከሏቸው። ሁለቱን ወጣቶችም የሀገሬው ሰዎች ለንጉሡ አስረከቧቸው። ሁለቱ ወጣቶች እየዋሉ እያደሩ በአኩስም ቤተ መንግሥት መሠረቱ ተጥሎ ያገኙትን ክርስትና በአክሱም ቤተ መንግሥት አጠናክረው ሰበኩ÷አስፋፉ ሁኔታ ተሰበከ።

ክርስትና በታላላቅ ሀገሮች ብሔራዊ ሃይማኖት ከሆነ በኋላ ነገሥታቱና መኳንንቱ ግዛታቸውን ለማስፋፋትና ሥልጣናቸውን ለማጠናከር ሲሉ ስብከተ ወንጌልን ያበረታቱ፣ ሕዝቦችን ወደ ክርስትና ለመመለስም መንግሥታዊ ኃይላቸውን ይጠቀሙ ነበር። ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች «ክርስትናን» የተቀበሉት በቅኝ ግዛት መስፋፋት ምክንያት ነው። ይህም ከአንዳንድ ሚስዮናውያን ቀና ተግባር በቀር ዋና ዓላማው ክርስትናን የቅኝ ግዛት መሣሪያ ማድረግ ነበር።

*ተጠቃሚነት*፦ ሲባል ክርስትናን መቀበል የሚያስገኘውን ጥቅም በመመልከት ወደ ክርስትና መቀየር ማለት ነው። ከነገሥታቱ ጋር መስማማት፣ የሥልጣኔ ተሳታፊ መሆን፣ የትምህርት ዕድል ማግኘት፣ ውትድርናና የመንግሥት ሥራን የመሰሉ የሥራ ዕድሎች ማግኘት፣ ወዘተ ግለሰቦችና ሕዝቦች ወደ ክርስትና እንዲገቡ ያደረጉበት አጋጣሚ አለ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት በአራት ዘመናት ከፋፍለን መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

1. *ዘመነ አክሱም*፦ ከአንደኛው መ/ክ/ዘ እስከ ዘጠነኛው መ/ክ/ዘ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስናጤን በኢትዮጵያ ግዛትም ይሁን ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ ክርስትና የተሰበከው በሕዝቦች ንቅናቄና በሐዋርያዊ አገልግሎት አማካይነት መሆኑን እንረዳለን። ቀደም ብለን እንደ ጠቀስነው ፍሬምናጦስ በንግድ፣ ተስዐቱ ቅዱሳን በስደት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተተከለውን ዐጸደ ወንጌል÷ ፍሬ እንዲያፈራ አድርጎታል። ከእነርሱም በተጨማሪ ማኅበረ ጻድቃን የተባሉትና ቁጥራቸው ከ7000 በላይ የሆኑት የወንጌል መልእክተኞችም ወደ ኢትዮጵያ ሊገቡ የቻሉት የኬልቄዶንን ጉባኤ ተከትሎ የተስፋፋውን የክልኤ ባሕርይ ኑፋቄ ባለመቀበላቸው በገጠማቸው ስደት ምክንያት ነበር።

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ተጠምቆ ወደ አክሱም ከመጣና ክርስትናን ካስተማረ በኋላ በየመን፣ በፋርስ፣ በሕንድና በመጨረሻም በሰማዕትነት ባረፈባት በሲሎን ያከናወነው የወንጌል ስብከት ደግሞ ሐዋርያዊ አገልግሎትን ያሳየናል። ከእርሱም በተጨማሪ በሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ አንበሮ እድ ተሾሞ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ ሆኖ የመጣው ቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በትግራይ፣ በጎንደር፣ በወሎ፣ በጎጃምና በሸዋ ከነገሥታቱ ከአብርሃና አጽብሐ ጋር በመሆን ሐዋርያዊ አገልግሎት ሰጥቷል። በቅድምና ሕገ ኦሪትን ተቀብለው የኖሩትን አካባቢዎችም ወደ ሕገ ወንጌል መልሷቸዋል። ከእርሱ በተጨማሪም በጥንቱ የአክሱም የአሪት ት/ቤት የነበሩ ሊቃውንትን አስተምሮ በማጥመቅ በቁምስና መዓርግ ሾሞ በኑቢያና በየመን ለሐዋርያዊ አገልግሎት አሠማርቷቸዋል።

በስደት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ተስዐቱ ቅዱሳን፣ ማኅበረ ጻድቃን፣ አባ ሊባኖስ፣ ወዘተ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በኤርትራ፣ በወሎ፣ በሸዋና በመሳሰሉት አካባቢዎች ሐዋርያዊ አገልግሎት ሰጥተዋል::

ከዚህም በተጨማሪ በሀገረ ናግራን /የመን/ ከኢትዮጵያ በሚላኩ ሐዋርያውያን አበው አማካይነት ክርስትና ተስፋፍቶና ጸንቶ ነበር:: በርግጥ በአካባቢው የነበረውን የንግድ መስመር ለመቆጣጠርና የናግራን ክርስቲያኖች ከአካባቢው አይሁድ ይደርስባቸው የነበረውን ወታደራዊ ተጽዕኖ ለመግታት የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሠፈር /military colonies/ በአካባቢው መኖሩ ለክርስቲያኖቹ የእፎይታ ዘመን ለግሏቸው ነበር:: ይሁን እንጂ በ524 ዓ.ም የአይሁድ ኃይል እየገፋ መጥቶ ድሁኖባስ /ፊንሐስ/ የተባለው የሃምርያት ንጉሥ ናግራንን ከብቦ ክርስቲያኖችን በፈጀቸው ጊዜ በቁስጥንጥንያው ንጉሥ በዩልያኖስ ጥያቄ÷ በግብጹ ፓትርያርክ በአቡነ ጢሞቴዎስ ተማኅፅኖ እንዲሁም በናግራን ክርስቲያኖች ልመና የዐፄ ካሌብ ጦር ወደ ሥፍራው ተጉዞ ክርስቲያኖችን ከመከራው ታድጓቸዋል::

2. *የመካከለኛው ዘመን*:- ከ10ኛው - 15ኛው መ/ክ/ዘ ያለውን ጊዜ በዚህ ክፍለ ዘመን ውስጥ አካትተን እንመለከተዋለን:: በዚህ ጊዜ የነበረው የወንጌል መስፋፋት በሁለት መንገዶች የተፈጸመ ነበር::

2.1.*በሐዋርያዊ አገልግሎት*፡- በዐርባ ሐራ /ዐርባዎቹ ቅዱሳን በሰሜን ሸዋ በ10ኛው መ/ክ/ዘ ያስተማሩ/ እና በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት እስከ 13ኛው መ/ክ/ዘ የተሠሩት ሐዋርያዊ ተግባራት ለኋለኞቹ ሐዋርያውያን አበው መሠረት ጥለዋል:: አባታችን ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአቡነ አረጋዊና ከዐፄ ገብረ መስቀል በኋላ ከክርስቲያኑ ሕዝብ ተቆራርጦ የነበረውን የደቡብ ኢትዮጵያ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌል እንደ ገና ፈልገው አግኝተውታል:: በስብከትና በተአምራት ሕዝቡን በማሳመን ወደ ጥንት ክርስትናው መልሰውታል::

ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመቀጠል በመላ ሀገሪቱ የስብከተ ወንጌል ሥምሪቶች ተደርገዋል:: ከእነዚህም መካከል ሦስት ሥምሪቶችን ለአብነት እናነሣለን::

ሀ. *የብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ሥምሪት*፡- በዐፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ካረፉ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተጠናከረውን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት የበለጠ ለማጽናት ዐሥራ



*አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ*

ሁለቱን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት ሀገረ ስብከት ከፋፍሎ በመስጠት አሠማርቷቸው ነበር:: በዚህም መሠረት:-

ምሥራቅ:- -

አባ ቀውስጦስ እና አባ ዮሐንስ -በይፋትና ጥሙጋ፣ በመተሐራ

- አባ ታዴዎስ በጽላልሽ-

አባ ማትያስ በምንጃርና ሸንኮራ

ምዕራብ-

አባ አኖሬዎስ /ታናሹ/ በሞረትና ወግዳ፣

- አባ መርቆሬዎስ በመርሐ ቤቴ

ደቡብና ደቡብ ምዕራብ:-

አባ አኖሬዎስ /ታላቁ/ በወረብ፣ጺጋጅ፣ ግንደ በረት፣ ጉደር፣ ባሌ

- አባ ኪዳኔ - በዳሞት

-አባ ኢዮስያስ- በአዋሽ፣በጉራጌ

- አባ ዮሴፍ - እናርያ /ከፋ/ በመሳሰሉት አካባቢዎች ተሠማርተው ስብከተ ወንጌልን አስፋፍተዋል::

ለ. *የአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ሥምሪት*፡- የደብረ በንኰል ገዳም መሥራች የሆኑት አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በጣና ሐይቅ ዙርያ ወንጌልን ያስተማሩና ገዳማትን የመሠረቱ አበውን አሠማርተው ነበር:: እነዚህም *«ሰባቱ ከዋክብት»* በመባል ይታወቃሉ:: አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አቡነ ሳሙኤል ዘቆየጻ፣ አቡነ ሳሙኤል ዘጣሬጣ፣ አቡነ ዮሐንስ ዘጉራንቋ /ክብራን /ጣና/፣ አቡነ ታዴዎስ ዘባልተዋር /ደብረ ማርያም /ጣና/፣ አቡነ ያሳይ ዘማንዳባ፣ አቡነ ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤን ናቸው::

ሐ. *የዕጨጌ ሕዝቅያስ ሥምሪት*፡- አምስተኛው የደብረ ሊባኖስ አበምኔት የሆኑት ዕጨጌ ሕዝቅያስ በወሎ፣ በትግራይና በኤርትራ *«አምስቱ ከዋክብት»* በመባል የሚታወቁትን አባቶች አሠማርተው ነበር:: አቡነ አሮን ዘከቱር፣ አቡነ መርቆሬዎስ ዘዴባ፣ አቡነ ዘካርያስ ዘከፋ፣ አቡነ ገብረ ክርስቶስ እና አቡነ ዳንኤል ዘጸዐዳን ናቸው::

እነዚህ በኢትዮጵያውያን ሐዋርያውያን አበው በኅብረት የተደረጉ ሥምሪቶች ናቸው:: በተናጠል ከየገዳማቱ ተነሥተው ወደ ልዩ ልዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመጓዝ በመላዋ ኢትዮጵያ የወንጌል አገልግሎት ያበረከቱ አበው ግን ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ ያህል:-

- አባ አንበስ በአፋር /ደብረ ሐዘሎ ገዳምን የመሠረቱት

- አቡነ ዜና ማርቆስ - በጉራጌ

አባ ያፍቅረነ እግዚእ - በአገው

-አባ ገብረ ኢየሱስ - በፈላሻ

-አባ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግ በአሰቦት፣በአሩሲ፣ በእንዳግብጦን፣ በውጋዴን ይገኙበታል::

2. *በስደት ምክንያት:*

- ከ13ኛው እስከ 15ኛው መ/ክ/ዘ የነበሩ ነገሥታት ምንም እንኳን ለሀገራቸው ቀናዕያን÷ በራሳቸውም ክርስቲያኖች ቢሆኑም ቅሉ ከተስፋፋው ግዛታቸው የሚወርሱት ልዩ ልዩ ዓይነት የባዕድ አምልኰ ጠባይ ያስቸግራቸው ነበር:: በዚህም የተነሣ አልፎ አልፎ ለክርስትና በማያመች መንገድ ሲጓዙና ሕዝቡንም በመጥፎ ምሳሌ ሲያሰናክሉት ገጸ ሰብእ አይተው የማይፈሩትና የነገሥታቱን ኃይል ከሃይማኖት ኃይል በታች የሚመለከቱት አበው ስሕተቱን ሊያርሙ በደሉን ሊያስቆሙ ይነሣሉ:: በዚህ ጊዜ በቤተ መንግሥትና በቤተ ክህነቱ መካከል ቅራኔ ይፈጠራል:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን በዐፄ ዓምደ ጽዮንና በዐፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመናተ መንግሥታት የተፈጠሩት ቅራኔዎች ናቸው::

በዐፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ንጉሡ የአባቱን ዕቁባት በማግባቱ የተነሣ በዚያ ዘመን የነበሩ ዐሥራ ሁለቱ አበው /አቡነ በጸሎተ ሚካኤል፣ አቡነ አሮን፣ አቡነ ናትናኤል፣ አቡነ ፊልጶስ፣ አቡነ ድምያኖስ፣ አቡነ ዮሐንስ፣ አቡነ እንድርያስ፣ አቡነ ገብረ ናዝራዊ፣ አቡነ ዘርዐ ክርስቶስ፣ አቡነ ገብረ አምላክ፣ አቡነ ብንያም/ ከየቦታቸው ተሰብስበው ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብተው ፊት ለፊት ተቃወሙት:: በዚህም የተነሣ የመጀመሪያው ስደት ተነሣ:: ብዙ አበውም ወደ ትግራይ፣ ወሎ፣ ዝዋይ፣ ሲዳማ እና ባሌ ተሰደዱ፤ በዚያም የስብከተ ወንጌል ሥራ ሊስፋፋ ቻለ::

በዐፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመንም በተመሳሳይ ንጉሡ የአባቱን ሚስት በማግባቱ የተቃወሙትን አበው ወደ ዝዋይ፣ ደቡብና ሰሜን ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ አድርጎ ነበር::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በአጠቃላይ በዘመኑ በዚያ ጊዜ የሀገሪቱ ግዛት በነበሩት ቦታዎች ሁሉ የክርስትናው ደወል ተሰምቶ ነበር። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ተተክለው ነበር። ለዚህ አንዱ ምስክር የግራኝ ታሪክ ጸሐፊ የግራኝን የወረራና የጥፋት ግሥጋሴ ሲዘግብ ከደቡብ የኢትዮጵያ ጀምሮ ግራኝ ያቃጠላቸ ውን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ መዝግቧል። እነ ብርብር ማርያም በደቡብ ኢትዮጵያ፣ እነ አሰቦት ደብረ ወገግ አባ ሳሙኤል ገዳም በምሥራቅ ኢትዮጵያ፣ እነ ሊሙ እናርያ በምዕራብ ኢትዮጵያ የታሪክ ምስክርነታ ቸውን ይዘው የጥንቱን የክርስትና ዱካ ዛሬም ያሳያሉ። እንዲያውም የሐመር ሕዝቦች እንደ ሚተርኩት በቡስካ ተራራ ላይ ጥንት ቤተ ክርስቲያን ነበር። ዛሬም ድረስ ከተራራው የቅዳሴና የዝማሬ ድምፅ እንደ ሚሰሙ ይናገራሉ፤ በዱራሜ /ከምባታ፣ አላባና ጠንባሮ ዞን/ በማገኘው የአንበርቾ ተራራም እንዲሁ።

በዚህ በመካከለኛው ዘመን በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ ታላቅ የስብከተ ወንጌል ሥምሪት በመደረጉ የሰሜኑና የደቡቡ ሕዝብ በትውፊት እስከ መወራረስና የታሪክ መስተጋብርም እስከ መፍጠር ዘልቋል። በዚህ የተነሣ በሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘንድ የምናያቸውን ታሪካውያን ቅርሶችን በደቡብም የምናገኝበት ጊዜ አለ።

ለምሳሌ፡- የከፋ ነገሥታት /ታቶ/÷ ራሳቸውን ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥት ሳባ የተወለዱ አድርገው ይቆጥሩ ነበር። «ክርስትናን በዐፄ ሠርጸ ድንግል ዘመነ መንግሥት እንደ ተቀበሉ ተደርጎ የሚነገረውን የከፋ ሕዝቦች አያምኑበትም። ከዚያ ዘመን በፊት «ሺፔናዎ» በተባለው የእናርያ ንጉሥ አማካይነት በከፋ ክርስትና የተሰበከ መሆኑን ይተርካሉ። ይህ ሰው በትምህርትና በተአምራት የታወቀ ነበር። ዋና ከተማውም ጨሬቆ ላይ ነው። በእናርያ አብያተ ክርስቲያናትን የገነባው÷ በዚያ ዘመን ሲዳማ በሚባለው ግዛት የመጀመሪያውን ምሥዋዕ የሠራው እርሱ ነው። ዛሬ በአንድራቻ አጠገብ የሚገኘውን የጉርጉቶ ድልድይ በአንድ ቀን በተአምራት የሠራው እርሱ መሆኑ ይነገርለታል። በዚህ ድልድይ በኩል ተሻግሮ ጫራ የሚገኘውን ቋጥኝ ለሁለት በመሰንጠቅ አለፈ። ከዚያም ወደ ምዕራብ ተሻግሮ በበሃ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን ተከለ። በዚያ ቤተ ክርስቲያን ከኢየሩሳሌም ካመጣ ቸው የድንጋይ ጽላት አንዱን አኖረ። በመጨረሻ ወደ ምዕራብ ጠረፍ በመጓዝ በዚያው ተሰወረ።» /Ethnology and History of South - West Ethiopia, Hunting Ford: P.10-11/

ይህ ታሪክ በእናርያ /ከፋ/ በአቡነ ዮሴፍ የተፈጸመው የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ከተሠራበት ዘመን ጋር ተቀራራቢ ነው። ቢሆንም ግን የበለጠ ጥናት የሚፈልጉ ጉዳዮች ከፋ ውስጥ ዛሬም አሉ፤ በግራኝ ወረራ ጊዜ የተሰወሩ፣ ከልዩ ልዩ ቦታዎች ተሰባስበው የተቀመጡ ቅርሶች መኖራቸውን የሀገር ሽማግሌዎች ይተርካሉና።

የወላይታ ሕዝብን ብንወስድ ከ13ኛው መ/ክ/ዘ ጀምሮ በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተሰበከ ነው። ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን የተቀናቀነው ንጉሥ ሞቲ ለሚ /በተለምዶ መተለሚ የሚባለው/ ካመነበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ገዳማት ተተክለው ነበር። በኋላ ዘመን በዐፄ ሠርጸ ድንግል ጊዜ የጎንደርን አብያተ ክርስቲያናት ለመሥራት የጥንት ታቦታት ከተገኙባቸው ቦታዎች አንዱ ወላይታ ነው። ለምሳሌ፡- የጎንደሩ አደባባይ ኢየሱስ ታቦት የሄደው ከወላይታ መሆኑን በዐፄ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕልና በታቦቱ ላይ በተጻፈው ጽሑፍ መረዳት ይቻላል።

የጉራጌን ሕዝብ ብንመለከት ከአቡነ ዜና ማርቆስ የ13ኛው መ/ክ/ዘ ሐዋርያዊ ተልእኮ ጀምሮ የጸና የክርስትና ሕይወት የነበረው ነው። እንዲያውም በግራኝ አሕመድ ወረራ ምክንያት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ሊቃውንቱ ሲጓደሉ በሕይወት የተረፉት ሊቃውንት የተገኙት ከጉራጌ ምሑር ኢየሱስ መሆኑን የጎንደር ደብረ ማርያም ገዳም ታሪክ ይገልጣል። ዐፄ ሠርጸ ድንግል አባ መሰንቆ ድንግልን ለቤተ ልሔም፣ አባ ለባዌ ክርስቶስን ለዙር አባ፣ አባ ብእሴ እግዚአብሔርን ለገደባ ማርያም ከመምህር ተክለ ወልድ ጋር መድቦ ነበር።

ከግራኝ በኋላ የጉራጌ ሕዝብ በሐዋርያ እጥረት ክርስትናው እየተዳከመ አምልኮ ባዕድ ሊወርሰው ሲል በዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመን በትግራይ ይኖሩ የነበሩና «አባ ጉራጌ» እየተባሉ የሚጠሩ አባት ለዐፄ ዮሐንስ ዘወትር ማሳሰቢያ ያቀርቡ ነበር። በኋላም በዐፄ ዮሐንስ ትእዛዝ በዐፄ ምኒልክ አማካይነት ክርስቲያኑን የጉራጌ ሕዝብ ከሌላው ክርስቲያን ጋር አገናኝ ተውታል።

3. *በቅርቡ ዘመን፡-* የቅርቡ ዘመን የምንለው ከግራኝ አሕመድ የወረራና የጥፋት ዘመን በኋላ ያለውን ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ የተደረጉትን የስብከተ ወንጌል ተግባራት በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

3.1. በባሕታውያን

3.2. በካህናት

3.3. በመኳንንት

3.1. *በባሕታውያን፡-* ከልዩ ልዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚነሡ መናንያን ክርስትናን የበለጠ ለማጽናት በየቦታው እየተጓዙ አስተምረዋል። ለምሳሌ፡ - በወለጋ በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እየተዘዋወሩ ያስተምሩ የነበሩትን አባ ሐናን መጥቀስ ይቻላል። አባ ሐና መናኝና የኰምቱ ሥላሴ እንዲተከል ያደረጉ አባት ናቸው። የመጡት ከጎጃም አካባቢ ሲሆን በወለጋ ተዘዋውረው በማስተማር በዚያው እንደ ተሰወሩ ይነገራል።

3.2. *በካህናት፡-* ከግራኝ ዘመን በኋላ ተመልሳ አንድ የኾነችው ኢትዮጵያ በአንድ መንግሥት ሥር መተዳደር ስትጀምር በየቦታው ለሚዘዋወሩ ካህናት ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ። ይህም ዓለም በሮም መንግሥት ሥር አንድ በመሆንዋ ለክርስትና መስፋፋት

/ወደ ገጽ ፴፰ ዞሯል/

የሐመር ሕዝቦች እንደ ሚተርኩት በቡስካ ተራራ ላይ ጥንት ቤተ ክርስቲያን ነበር። ዛሬም ድረስ ከተራራው የቅዳሴና የዝማሬ ድምፅ የሚሰሙ መኖራቸውን ይናገራሉ፤ በዱራሜ /ከምባታ፣ አላባና ጠንባሮ ዞን/ በሚገኘው የአንበርቾ ተራራም እንዲሁ።



የምዕራብ ኢትዮጵያው ሐዋርያ - መልአከ ኃይል አባ እንየው ውቤ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ሆኖ ከዚህ እትም ጀምሮ የተከፈተ ነው:: ማኅበራችን ይህንን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ሲሆን፤ አጠቃላይ የሥራ ሂደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል እንዲደረግበት ሆኖ ነው::

# መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ለጠባይ ለውጥ

*ጸጋዬ ጥላሁን*
*/አ.አ.ዩ/*

ባለፉት ሦስት ተከታታይ እትሞች ስለ አጠቃላይ የምክክር አገልግሎትና ለአዎንታዊ የጠባይ ለውጥ ያለውን ጠቀሜታ በአጭሩም ቢሆን ለማየት ሞክረናል:: በዚህ እትማችን ደግሞ ስለ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት /Pastoral counseling/ በተለይም ሰዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና ከቫይረሱ ጋር አብሮ በመኖር ዙሪያ የጠባይ ለውጥ እንዲያመጡ የሚኖረውን አስተዋፅዖ ለማየት እንሞክራለን::



የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በጉባኤ ምክክር ላይ

## መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት /Pastoral counseling/

እናት ቤተ ክርስቲያናችን ልጆቿ የተለያዩ ማኅበራዊ፣ሥነ ልቡናዊ እና መንፈሳዊ ችግሮች ሲገጥማቸው ችግራቸውን ለመቅረፍ ብሎም ለመከላከል ከምትጠቀምባቸው የተለያዩ መንፈሳዊ የአገልግሎት ዘዴዎች አንዱ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ነው:: ይህ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች የሚሰጠው÷ ቃለ እግዚአብሔርንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መሠረት በማድረግ በቤተ ክርስቲያን አባቶች /በካህናት/ ነው::

ሰዎች በጥሩ ሥነ ምግባር የታነጹ፣ ለሀገርና ለወገን የሚበጁ፣ዓላማና ራእይ ያላቸው፣በራሳቸው የሚተማመኑ፣ራሳቸውን የሚሆኑ፣ማንነታቸውን የሚያውቁ፣ለሥራ ተነሣሽነት ያላቸው፣ከማንኛውም ሱስ የጸዱ፣በአገልግሎት የሚተጉ፣ ሓላፊነት የሚሰማቸው፣ የተሰጣቸውን ጸጋ /ነጻ ስጦታ/ በአግባቡ የሚጠቀሙ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚበጁ ምርምሮችን የሚያደርጉ፣በትዳራቸው በኑሯቸው የሚረኩና ደስተኛ የሆኑ ዜጎችን ለማፍራት የምክክር አገልግሎት በእጅጉ አስፈላጊ ነው:: በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን ለሰው ልጆች ሁሉ ከምትሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች በተጨማሪ በመንፈሳዊ የምክክር አገልግሎትዋ የምታበረክተው አስተዋፅዖ የጎላ ነው::

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ምን ይላል?

ምክክር /counseling/÷ የሚለው ጥሬ ቃል በቀጥታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይገኝም «ምክር» የሚለው ቃል ግን በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በብዙ ቦታ ላይ ተጽፎ ይገኛል:: ለአብነት ያህልም መልካም ምክር ከእግዚአብሔር እንደ ሆነና ምክር በሌለበት ቦታ ሁሉ ዕቅድ እንደ ማይሳካ ተጠቅሷል:: ምሳሌ.8÷1:- «... ምክርና መልካም ጥበብ የእኔ ነው፤ ማስተዋልም እኔ ነኝ÷ ብርታትም አለኝ::» ይላል:: እንደዚሁም በምሳሌ 15÷22 ላይ:- «ምክር ከሌለች ዘንድ የታሰበው ሳይሳካ ይቀራል፤ መካሮች በበዙበት ዘንድ ግን ይጸናል::» ይላል::

ቅዱስ መጽሐፋችን አስቀድሞ ሰዎች መዳን ስለ ሚችሉበት መንገድ ይናገራል:: ከዚህም ባሻገር ሰዎች እርስ በእርሳቸውም ስለ ሚኖራቸው ግንኙነትና የእርስ በእርስ ምክክርን ጠቃሚነትም በአጽንዖት ይናገራል:: ስለሆነም በዘፍ.5÷2–18 ላይ:- «እግዚአብሔር አምላክም አለ÷ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም:: የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት::» ይላል:: ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በምዕራፍ 6÷1 ላይ:- «ወንድሞች ሆይ÷ በማንኛውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደ ዚህ ያለውን ሰው በየዋህነት መንፈስ አቅኑት:: አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ:: ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ::» በማለት አንድን የተቸገረን ሰው እንዴት መርዳትና መከባከብ እንዳለብን በግልጽ አስቀምጧል::

እነዚህንና ሌሎችን ጥቅሶች ስናይ÷ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ከጥንት ጀምሮ ሰዎች፣ራሱ ጌታችን፣ሐዋርያት እንዲሁም ሊቃውንት በስፋት ይጠቀሙበት እንደ ነበር ያመለክታል:: ይህን አገልግሎት በአንድም ይሁን በሌላ አባቶቻችን ካህናት መደበኛ ባልሆነ መልኩም እንኳ ቢሆን ለመንፈሳዊ ልጆቻቸው አገልግሎቱን በስፋት እየሰጡ ይገኛሉ::

## መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ምን ማለት ነው?

መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት /Pastoral counseling/ በአጭሩ ሲተረጎም:- በአመካካሪው /በካህኑ/ እና በተመካካሪው /counselee/ መካከል የሚደረግ ምስጢራዊ ውይይት ነው:: በዚህ ውስጥ ምክክር የሚለው ቃል ቀጥታ ምክር በመስጠት ላይ የተመሠረተውን አገልግሎት የሚያመለክት አይደለም::

መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት አመካካሪው /ካህኑ/ ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ የተመካካሪውን የችግር ምንነት፣ስፋት፣ መንሥኤና ውጤት በሚገባ ተገንዝቦና ዐውቆ በራሱ ፈቃድና ጥረት ለችግሩ መፍትሔ የሚሆነውን ነገር እንዲፈልግና ከችግሩ እንዲላቀቅ ወይም ያጋጠመውን ችግር ተጋፍጦ /ተቀብሎ/ የወደፊት ሕይወቱን በሰላም፣ በደስታና በጥንካሬ እንዲኖር ማስቻል ነው:: እዚህ ላይ ካህኑ /አመካካሪው/ የተመካካሪውን ችሎታ፣አቅም፣ልምድ፣ መንፈሳዊ ጥንካሬና ብስለት በማገናዘብ



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ለችግሩ መፍትሔ የሚሆኑትን አማራጮች /የመፍትሔ ሐሳቦች/ ማቅረብ ይጠበቅበታል:: ያንን አማራጭ /የመፍትሔ ሐሳብ/ መቀበል ወይም አለመቀበል ግን የተመካካሪው መብት ነው:: ለምሳሌ:- ከፍተኛ የሆነ ጭንቀት (የስሜት መረበሽ) ያለበት ሰው ከመንፈሳዊ አመካካሪው ዘንድ አገልግሎት ለማግኘት ይመጣል:: አመካካሪው በመጀመሪያ ጥሩ አቀባበል ከአደረገለት በኋላ ስለ ችግሩ ምንነት÷ መንሥኤ÷ እያስከተለበት ስላለው መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ችግር በጥልቀት ከተመካካሪው ጋር ይወያያሉ:: አመካካሪው ከተመካካሪው ጋር ለችግሩ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን /የመፍትሔ ሐሳቦችን/ ለማመንጨት ጥረት ያደርጋሉ:: በመጨረሻም ተመካካሪው የቀረቡትን የመፍትሔ ሐሳቦች በመመርመርና በመመዘን በራሱ እንዲወስን ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት የአመካካሪው ድርሻ ነው:: የመፍትሔ ሐሳቦች ግን የተመካካሪውን አቅም፣ዕድሜ፣ችሎታ መንፈሳዊ ብስለት ያገናዘቡ መሆን አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ተመካካሪው የመፍትሔ ሐሳቦችን ላይተገብራቸውና ከችግሩ ላይላቀቅ ይችላል:: በውይይታችን ወቅት የሰዎችን /የተመካካሪዎችን/ ችግር ስንረዳና የመፍትሔ ሐሳብ ስናቀርብ ሁልጊዜ የተመካካሪውን ሁለንተናዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን:: በምክክር አገልግሎት **/counseling/** ውስጥ ወሳኙ ተመካካሪው (counselee) ነው:: ሰዎች እንዲወስኑ ማበረታታት /ሁኔታዎችን ማመቻቸት/ እና ስለ ሰዎች ተገብቶ መወሰን የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: እኛ ለሰዎች /ለተመካካሪዎች/ ከወሰንላቸው ለጊዜው ይቀበሉና ተግባራዊ ለማድረግ ግን ሲቸገሩ እናያቸዋለን:: ስለ ራሳቸው አቅም፣ ችግርን የመቋቋም ችሎታ፣ ልምድና ፍላጎት፣መንፈሳዊ ጥንካሬ .... ወዘተ ከራሳቸው በላይ ማንም ሊያውቅ አይችልም:: ምክንያቱም ሁሉም ሰው እነዚህን ነገሮች በተወሰነ መልኩም ቢሆን የማወቅ አቅም አለውና:: ለዚህ ነው በምክክር አገልግሎት ውስጥ ስለ ራሱ መወሰን ያለበት ተመካካሪው **/counselee/** ነው የሚባለው::

በመንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ውስጥ ተመካካሪው ነጻ በሆነ ስሜት የሚያስጨንቀውን፣የሚሰማውን ነገር፣ የውስጥ ችግሩንና ሐሳቡን ወይም ደግሞ መሆን የሚፈልገውን÷ እንዳይሆን ያደረጉትን ነገሮች ያለ ምንም ችግር ለአመካካሪው መግለጽ እንዲችል አመካካሪው /ካህኑ/ ከሰላምታ /አቀባበል/ ጀምሮ ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን /ግንኙነቶችን/ መፍጠር አለበት:: ይህም ማለት ተመካካሪውን ለመርዳት ዝግጁ መሆኑን በተግባር ማሳየት መቻል አለበት:: ይህ ካልሆነ ግን ለችግራቸው መፍትሔ ሊያገኙ መጥተው ችግራቸውን ሳይናገሩ አምቀው ይዘውት ሌላ ተጨማሪ ችግር ይዘው ይመለሳሉ::

በዚህ ዙሪያ ለተመካካሪዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ለመርዳት ዝግጁ መሆናቸውንና ውሳኔን ለተመካካሪዎች በመተው ውጤታማ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት የሰጡ ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ:: ለምሳሌ:- ዮቶር የተባለው የሙሴ አማት ለሙሴ ምክር ከመስጠቱ በፊት የሙሴን ድርጊት በትክክል ለማወቅ ስለ ፈለገ ጥያቄ በመጠየቅ ነበር የጀመረው:: ዘጸ.18÷14–27:- «... የሙሴም አማት በሕዝቡ ያደረገውን ባየ ጊዜ ይህ በሕዝቡ የምታደርገው ምንድን ነው? ሕዝቡ ሁሉ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ በዙሪያህ ቆመው ሳሉ አንተ ብቻህን ስለ ምን ተቀምጠሃል?» አለው::

ዮቶር የሰጠውን ምክር ሙሴ የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት ነበረው:: ይህ ደግሞ አንዱ የምክክር አገልግሎት ባሕርይ መገለጫ ነው:: ለተመካካሪው በራሱ ሕይወት ምርጫ ላይ የመወሰን ሙሉ ሥልጣን መስጠት ማለት ነው:: ተመካካሪዎች በሚሰጡን መረጃና በተመካካሪዎች ላይ በምናስተውለው /observation/ ድርጊት መሠረት ለተመካካሪው ችግር የመፍትሔ ሐሳቦችን /አማራጮችን/ ከሕገ እግዚአብሔር አንጻር በማቅረብ እነርሱ እንዲ መርጡና እንዲወስኑ ማገዝ ነው:: ዮቶርም ያደረገው ይህን ነበር:: ሙሴም በመጨረሻ አማቱ የመከረውን ምክር መልካም መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ ተቀበለውና በተግባር ላይ አዋለው:: ተመካካሪዎች አቅማቸውን ያገናዘቡና ለችግራቸው መፍ ትሔ የሚሆኑ አማራጮች ካቀረብን ላቸው ከአገልግሎቱ ተፈላጊውን ውጤ ት የማያገኙበት ምንም ምክንያት የለም::

«በመንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ውስጥ ተመካካሪው ነጻ በሆነ ስሜት የሚያስጨንቀውን፣የሚሰማውን ነገር፣ የውስጥ ችግሩንና ሐሳቡን ወይም ደግሞ መሆን የሚፈልገውን÷ እንዳይሆን ያደረጉትን ነገሮች ያለ ምንም ችግር ለአመካካሪው መግለጽ እንዲችል አመካካሪው /ካህኑ/ ከሰላምታ /አቀባበል/ ጀምሮ ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን /ግንኙነቶችን/ መፍጠር አለበት::»

እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስ በሥቃይና በመከራ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለመርዳት አመካካሪዎች እንደ ነበሩ ይናገራል:: ጻድቁ ኢዮብ በመከራና በሥቃይ ውስጥ የነበረ÷ ቅንና እግዚአብሔርን የሚፈራ ታላቅ ሰው ነበር:: ጻድቁ ኢዮብን ከመከራው ወይም ከደረሰበት ከባድ ፈተናና ጭንቀት ለማጽናናት የቀረቡትን ሦስቱን ወዳጆቹን እናስተውላለን:: እነዚህ አመካካሪዎች ወደ እርሱ በሄዱ ጊዜ የኢዮብ ሥቃይ እጅግ ከብዶ ነበር:: «...ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊትም ከእርሱ ጋር በምድር ላይ ተቀመጡ፤ ሕመሙም እጅግ እንደ በዛ አይተዋልና አንድ ቃል የሚናገርም አልነበረም::» (ኢዮ.2÷13):: በመጀመሪያ ሁሉም በዝምታ ተውጠው ነበር:: እነዚህ አመካካሪዎች በኢዮብ ቤት ውስጥ በመግባት ከእርሱ ጋር በምድር ላይ ተቀመጡ:: እነርሱ ኢዮብን ለመርዳት ዝግጁነታቸውን ከእርሱ ዘንድ በመገኘት አረጋገጡ:: በዚህም ኢዮብ መናገር የሚፈልገው ነገር ካለ ለማዳመጥ የተዘጋጁ መሆናቸውን ገለጹለት:: ጻድቁ ኢዮብ ይህን ስለ ተረዳ ነበር መናገር የጀመረው:: ይህ አንድ መንፈሳዊ አመካካሪ /Pastoral counselor/ ተመካካሪውን የምክክር አገልግሎት ፈላጊውን /counsolleer/ ለመርዳት ማለትም ለችግሩ በጋራ መፍትሔ ለማፈላለግ ዝግጁ መሆኑን መግለጽ እንዳለበትና ጥሩ አድማጭ መሆን እንደ ሚገባው ያመለክተናል::

ሰዎች በውስጣቸው ያለባቸውን ችግር አውጥተው የሚነግሩን ችግሮቻቸውን ለማዳመጥና እነርሱን ለመርዳት ዝግጁነታችንን በተግባር ስናሳያቸው ብቻ ነው:: እኛ ያለብንን ችግር ለሰዎች ለማካፈል የምንፈልገው ሰዎች እኛን ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባር ሲያሳዩን ነው::

የጻድቁ ኢዮብ አመካካሪዎች የእርሱን መከራና ሥቃይ የተረዱበት መንገድ መንፈሳዊ ማስተዋል የጎደለው ነው:: ቢሆንም የእነርሱ በሥቃዩ ጊዜ ከእርሱ ጋር መገኘት ግን ጻድቁ ኢዮብ በውስጡ የተሰማውን ስሜት በተገቢ ሁኔታ እንዲገልጽ ረድቶታል::

ሰው ምንም እንኳ ለችግሩ መፍትሔ ባያገኝም ችግሩን ለሰዎች ሲናገር በተወሰነ መልኩም ቢሆን ውስጡ ዕረፍት ያገኛል::

ሌላው ከዚህ ጋር ሊያያዝ የሚችለው የንጉሥ ሳዖልና የቅዱስ ዳዊት ሁኔታ ነው:: ንጉሥ ሳዖል ችግር የመጣበት የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ተለየው ነበር:: በዚህ ጊዜ ይረዳው የነበረው ቅዱስ ዳዊት ነበር:: የቅዱስ ዳዊት የማማከር ዘዴም ለንጉሥ ሳዖል በሚገባ ጠቅሞት ነበር:: ሆኖም ግን ንጉሥ ሳዖል ከአመካካሪው ጋር የነበረው ግንኙነት መልካም አልነ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

> «ሁልጊዜ ከተመካካሪዎች ጋር ስንወያይ መነሣት ያለብን ከአላቸው ጠንካራ ጎን መሆን አለበት። እንደዚሁም የእኛን ሐሳብ ብቻ በተመካካሪው ላይ መጫን የለብንም።»



የምክክር ጉባኤ

በረም። ሳዖል የራሱን ችግር አመካካሪው ያመጣበት እንደ ሆነ በማሰብ ቅዱስ ዳዊትን ለመግደል አሰበ። ከማሰብም አልፎ ሙከራዎችን አደረገ። ቅዱስ ዳዊት ግን እንደ መልካም አመካካሪ ተመካካሪውን /ንጉሥ ሳዖልን/ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ /uncondtional acceptance/ እስከ መጨረሻው ድረስ ተቀበለው። የተመካካሪውን ችግር በሚገባ ስለ ተረዳ ተመካካሪውን በምንም መልኩ ለመጉዳት /ለመበቀል/ አላሰበም። 1ኛ ሳሙ.16÷23። «እንዲህም ሆነ÷ ከእግዚአብሔር ዘንድ መንፈስ በሳዖል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር። ሳዖልንም ደስ ያሰኘው÷ ያሳርፈውም ነበር። ርኩስ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር።» ይላል። የተጨነቀን ሰው ከጭንቀቱ ለትንሽ ደቂቃም ቢሆን ማሳረፍ ምንኛ ደስ ይላል!! እስኪ ራሳችንን በዚያ ጭንቀት ውስጥ እናድርገውና ጭንቀታችንን ሊያቃልልን፣ የጨለመ ተስፋችንን የሚያለመልምልንን ሰው ስናገኝ ምን ያህል እንደ ምንደሰት እና ስብ።

ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ የሚገኝን ሰው÷ ተስፋ የቆረጠንና ሞት ብቻ የሚታየውን ሰው ወይም ደግሞ ምክን ያታዊ ባልሆነ ፍርሃት የሚጨነቅን ሰው በቃለ እግዚአብሔር አጽናንተነው ተስፋውን ስናለመልምለት ተመካካሪው ምን ያህል ደስ ይለው ይሆን? ለዚህም ነበር ቅዱስ ዳዊት በመዝ.22÷1–4:- «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው። የሚያሳጣኝ የለም፤ በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት÷ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ፤ በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።» በማለት የተናገረው።

ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ታዝዘው የማሰርና የመፍታት ሥልጣን የተሰጣቸው የነፍስም የሥጋም ጠባቂዎች ካህናት ናቸው። እነዚህ የሰው መንፈሳዊና የሥጋዊ ሕይወት መሪዎችና ጠባቂዎች የሆኑ ካህናት ትጉሆች ናቸው፤ ሊሆኑም ይገባል። በመሆኑም የእነዚህ ሰዎች ሓላፊነት እጅግ ከባድ በመሆኑ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን እረኞችን /ጠባቂዎችን/ ሲወቅስ እናያለን። «እረኞችንም እንዲህ በላቸው:- እረኞችም ወዮላቸው÷ እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ፣ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ፣ የወፈሩትን ታርዳላችሁ፤ በጎቹን ግን አታሰማሩም፣ የደከመውን አላዳናችሁትም፣ የታመመውንም አላከማችሁትም፣ የተሰበረውን አልጠገናችሁትም፣ የባዘነውንም አልመለሳችሁትም። የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም።» /ሕዝ.34÷1–5/።

በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱን መንጋ ለሚጠብቁት ለቅዱሳን ለሐዋርያት:- በጎቹን በመጠበቅ ወደ መልካሙ ሁሉ እንዲመሯቸው፣ በለመለመ መስክ እንዲያሰማሯቸው፣ በሥጋቸውም በነፍሳቸውም እንዲከባከቧቸው፣ሲደክሙ እንዲያበረቷቸው ተስፋ ሲቆርጡ እንዲያጽናኗቸው ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። ጌታችን ሐዋርያው ጴጥሮስን:- «በጎቼን አሰማራ» /ዮሐ. 21÷17/ ብሎታል። በእኛ ዘመን የሐዋርያትን ሥልጣን በአንብሮተ እድ የወረሱት ካህናትም ከእግዚአብሔር የታዘዙ ጠባቂዎ ቻችን ናቸው።

ጌታችን ይህን ሁሉ ሓላፊነት የሰጣቸው ራሱ በተግባር አሳይቶ ነው።

ጌታችን በዚህ ምድር ላይ እየ ተዘዋወረ ሕዝቡን በአንድ ላይ በመሰብሰብ ያስተምር ነበር። እንዲሁም ሰዎች ያለባቸውን ችግር ይዘው ወደ እርሱ ይሄዱ ነበር። እርሱም ወደ እነርሱ በመሄድ በግልም ብቻቸውን ሲያገኛቸው ያስተምራቸው÷ አቅጣጫ ያሳያቸው÷ ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስ ይሰጣቸው እንደ ነበር በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተጽፏል። ለምሳሌ: - በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3÷1–21 ላይ: «ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበር። እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ መምህር ሆይ÷ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን አለው።» ይላል። በተለይም በዮሐንስ 4÷7 –2 ላይ የሰማርያይቱን ሴት እንዲሁም በሉቃስ 19÷1–9 ላይ የዘኬዎስን ሁኔታ እንመልከት። ዘኬዎስ የቀራጮች አለቃ ስለ ነበር ከሰዎች ከሚገባው በላይ ቀረጥ ይሰበስብ ነበር። በሰዎች ዘንድ የተጠላ፣እንደ ኃጢአተኛም ሰዎች የሚቆጠሩት ነበር። ለዚህም ነበር ጌታችን በዘኬዎስ ቤት ስለ ገባ አይሁዳውያን ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ ብለው ያንጎራጎሩት።

ከላይ የተጠቀሱትን ሰዎች ስናይ ሁሉም ደካማ ጎኖች አሏቸው። ግን ደግሞ ለመዳን ጥረት አድርገዋል። ያላቸውን ደካማ ጎናቸውን ለማጥፋት /ለመቀነስ/ ፍላጎት ስላላቸው ያንን ሊያጠፋላቸው÷ ጥረታቸው ውጤታማ እንዲሆን ሊያግዛቸው የሚችል ወገን ፈለጉ። ፈልገውም አልቀሩም÷ አገኙ። ፍላጎታቸው ጽኑ በመሆኑና ጥረታቸውን ዳር በማድረሳቸው÷ ችግራቸው በፈጣሪያቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተወገደላቸው። ጌታችን ለእነዚህ ሰዎች ድኅነተ ሥጋ ደኅነተ ነፍስ የሰጣቸው ለመዳን ያደረጉትን ብርቱ ጥረትና ጠንካራ /ከውስጥ የመነጨ/ ፍላጎታቸውን ተመልክቶ ነው። የሥነ ልቡና ባለሞያዎች የስኬት ምስጢሩ ፍላጎትና ጥረት ነው ይላሉ። ለመለወጥ ፍላጎት ከአለን÷ ጥረት ካደረግንና የፈለግነው ነገር ፈቃደ እግዚአብሔርን መሠረት ያደረገ ከሆነ በማንኛውም መስክ ያለ ጥርጥር ስኬታማ እንሆናለን። የብዙ ዎቻችን ችግር ግን ፍላጎት እናሳያለን እንጅ ጥረት አናደርግም። በመሆኑም ስኬታማ አንሆንም። ሳይሠሩ በመመኘት ብቻ ምንም አይገኝም። ሁሉም ሰው መጽደቅ+ርስት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ይፈልጋል። ግን ብዙዎቹ ያንን ለማግኘት ሲሠሩ /ጥረት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሲያደርጉ/ አይታዩም:: አይ ደለም ዘላለማዊ ነገር ጊዜያዊ የሆነ ነገር እንኳ ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድ ይጠይቃል::

እዚህ ላይ ሰዎች ለመለወጥ ፍላጎት በሚያሳዩበት ጊዜ አመካካሪው ያንን ጠንካራ ጎናቸውን ተጠቅሞ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ማገዝ ይኖርበታል:: ጌታችን ብዙ ሰዎችን በዚህ ምድር ላይ ሲያስተምራቸው ወይም ሲመክራቸው መነሻው የአለባቸው ደካማ ጎን አልነበረም፤ ከጠንካራ ጎናቸው እንጅ:: ያም ለመዳን /ለመለወጥ/ ያላቸው ፍላጎት ነበር:: የዘኬዎስን ጉጉት አይቶ በቤቱ ገባ:: አንድ መንፈሳዊ አመካካሪም ለሁሉም ነገር አብነት የሆነውን የጌታችንን መንገድ መከተል አለበት:: ጌታችን ሁሉንም ሰዎች ለመዳን ያላቸውን ፍላጎትና ሊደረግላቸው የሚፈልጉትን ነገር ይጠይቃቸው ነበር:: «ልትድን ትወዳለህ/ትወጃለሽ?» እያለ ያላቸውን ፈቃደኝነት ይጠይቃቸው ነበር:: «በግድ ላድናችሁ» ብሎ ያስገደደበት ጊዜ አልነበረም:: ከዚህም የምንረዳው አንድ መንፈሳዊ አመካካሪ ተመካካሪውን በግድ መክሬ ልቀይርህ ብሎ መቀየር ውጤታማ እንደ ማይሆን ነው:: ሁልጊዜ የሰዎችን ፈቃደኝነትና ፍላጎት መጠየቅና ማስቀደም አለብን::

በምክክር አገልግሎትም መከተል ያለብን ይህንኑ ነው:: ሁልጊዜ ከተመካካሪዎች ጋር ስንወያይ መነሣት ያለብን ከአላቸው ጠንካራ ጎን መሆን አለበት:: እንደዚሁም የእኛን ሐሳብ ብቻ በተመካካሪው ላይ መጫን የለብንም:: ይህ ሲባል ግን ተመካካሪው በሚፈልገው መንገድ ብቻ እንዲቀጥል መፍቀድ /ተባባሪ/ መሆን አለብን ማለት አይደለም:: ተመካካሪውን የማይጠቅመው ከሆነና ከእግዚአብሔር የሚያርቀው፣ ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውጪ የሚሆን ከሆነ አካሄዱን እንዲያስተካክል በግልጽ ልንነግረው ይገባል:: በዮሐንስ 10÷10–11 ላይ፡ - «መልካም እረኛ እኔ ነኝ:: መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል::» ይላል:: ከዚህ ላይ አንድ መንፈሳዊ አመካካሪ ስለ ተመካካሪው መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ሕይወት ምን ያህል ማሰብ እንደ ሚጠበቅበት በሚገባ ያሳያል::

የጌታችን ይከተል የነበረው የማማከር ስልት /technique / ተመካካሪውን ማዕከል ያደረገ /client centered/ ነው:: ጌታችን ተመካካሪዎችን በጥንቃቄ ያደምጣቸውና ለችግራቸውም መፍትሔ ይሰጣቸው ነበር:: ይረዳቸውና ይከባከባቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ወደ አልሆነ መንገድ ሲያመሩና ከሃይማኖት ውጪ ሲሆኑ ይገሥጻቸው ነበር:: ሰዎች ሥጋዊና መንፈሳዊ ኑሯቸውን እንዴት አጣጥመው መኖር እንደ ሚችሉ ያስተምራቸው ነበር:: ችግር ያለባቸው በሰላምና በተስፋ እንዲሁም በተረጋጋ ሁኔታ እንዲኖሩ መንገዱን ያሳያቸው ነበር:: የአንድ መንፈሳዊ አመካካሪም መንገድ እንደዚሁ መሆን አለበት::

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

***ይቀጥላል::***

## ሐዋርያዊነት በኢትዮጵያ... /ከገጽ ፴፬ የዞረ/

ከተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው::

በዚህም መሠረት አያሌ ካህናት የግራኝ ወረራ ሳይደርስበት ወይም ንዋያተ ቅድሳታውን መጻሕፍታቸውን ይዘው በጥፋቱ ሳይጎዳ ከተረፈው አካባቢ እየወጡ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን ማደስ፣ የጠፋውን ሕዝብ መፈለግ፣ የተረሳውን ክርስቲያናዊ ባህል ማስታወስ ጀመሩ:: ይህ የካህናት ሥምሪት እስከ ሀገሪቱ ጠረፍ የደረሰ ነው:: ዛሬ የምናያቸው ከ100 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው የጠረፍ አብያተ ክርስቲያናት የተሠሩት ያን ጊዜ ነበር::

3.3 *በመኳንንት፡-* ክርስትናን ተቀብለው የተሾሙ ወይም ከተሾሙ በኋላ የተቀበሉ መኳንንት በአካባቢያቸው አብያተ ክርስቲያናትን በመትከልና ሰባክያንንም በማበረታታት ለወንጌል መስፋፋት አስተዋፅዖ አድርገዋል:: የወለጋው ገዢ የነበሩት ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ሞሮዳ ለዚህ ምሳሌ ናቸው:: ግእዙን ጠንቅቀው የሚያውቁት፤ በሰላሌ ሜዳ ላይ ዳዊቱን በቃላቸው በመዝለቅ ዐፄ ምኒልክን ያስደነቁት ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ሞሮዳ የነቀምቴ ኢየሱስን በ1906 ዓ.ም ካስተከሉ በኋላ ከዴዴሳ በረሓ በታች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል::

በርግጥ ከመኳንንቱ መካከል አንዳ ንዶቹ ክርስትና ከሚፈቅደው ውጭ ሕዝቡን ያስገደዱበትና የጅምላ ጥምቀት ለማካኼድ የሞከሩበት ሁኔታ ቢኖርም በግለሰቦች እንደ ተፈጸመ ስሕተት ይቆጠራል እንጂ ጠቅላላውን የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮና ሂደት አይለውጠውም::

በጠቅላላው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከላይ የገለጥነውን መልክ የተከተለ እንጂ ከነፍጠኛነትና ከግዛት መስፋፋት ብሎም ሕዝቦች በማንነታቸው ከሚጨቆኑበት ሁኔታ ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም:: እነ ሂትለርና ሞሶሎኒ «እኩልነትና ፍትሕ» የሚሉትን ነገሮች ለጥሩ ዓላማቸው ስለ ተጠቀሙ ብቻ «እኩልነትና ፍትሕ» በራሳቸው እኩይ ናቸው አይባሉም:: ግለሰቦችም ክርስትናን ለክፉ ዓላማቸው ማካኼጃ እዚህም እዚያም ቢያውሉት ኦርቶዶክሳዊ ክርስትናን /የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን/ ሊወክሉ አይችሉም:: የቅዱሳን አበው አምላክ የተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ያጽናልን፤ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን ያስፋልን:: አሜን::

## ነገረ ድኅነት ... /ከገጽ ፳፬ የዞረ/

ተስፋ በመስጠትህ፣ ወንጌልን በመሥራትህ ቅዱስ ሥጋህን ክቡር ደምህን በመስጠትህ በሥራህ ሁሉ እናመሰግንሀለን::» ይላል::

የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ፍቅር አንድነት የሚለከው ወደፊት ሊደረግለት ስለሚገባው ነገር በመጸለይ ብቻ አይደለም:: እስከ አሁን በአባቶቹም ሕይወትም ሆነ በእርሱ ሕይወት የተፈጸሙትን አምላካዊ ቸርነቶች እያዘከረ /እያሳሰበም/ መሆን አለበት እንጂ:: የወላዲተ አምላክን የጸሎት መደምደሚያ ብንመለከት በቂ ምስክር ነው:: «ለአባቶቻችን እንደ ተናገረው ለአብርሃምና ለዘሩ የዘለዓለም ምሕረቱን አስቦ እስራኤል ባሪያውን ረድቶአል::» በማለት የውዳሴ፣ የጸሎትና የምስክርነት ፍጻሜ እግዚአብሔር ለአበው ያደረገውን በማስታወስ መጠናቀቁን እናያለን:: በጸሎተ ቅዳሴ ወቅት ካህኑ በማን ፊት እንደ ቆመ ለማስታወስ «ሥነ ፍጥረትን የፈጠርህ እናመሰግንሀለን» እያለ እንዲያመሰግን አባቶች የወሰኑት እግዚአብሔርን በሦስት ምሥጢራት ከፍሎ ማመስገን እንዲገባ ሲያጠይቁ ነው:: /ቅዱስ ባስልዮስ/:: ይህም ላለፈው ዘመን፣ ለአሁኑ ላለበት ዘመንና ከምድራዊ ሕይወት ፍጻሜ በኋላ ላለው ዘመን ማመስገን እንደ ሚገባ ለማመልከት ነው::

ስሙን ለመቀደስ÷ ክብሩን ለመውረስ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን:: አሜን::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የሁሉም ናት!!

«ቤተ ክርስቲያን የምታገናኝ ናት፣ ሕዝብንና ሕዝብን የምታዋሕድ አንድ የምታደርግ ናት።»

/ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ባወጣው የ1997 ዓ.ም የአብያተ ክርስቲያናት፣ የካህናትና የምእመናን ብዛት መረጃ መሠረት 77.4 ሚልዮን ከኾነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከ45 ሚልዮን በላይ የሚኾነው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ ነው። ይህም ከአጠቃላዩ ሕዝብ 60 በመቶ ያህል ነው። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ቢሮ የ1994 ዓ.ም መረጃ መሠረት ደግሞ ከአጠቃላዩ 53,130,783 የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል 50.6% የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ ነው። ከዚህም ውስጥ በክልል ደረጃ ከፍተኛው 95.4 በመቶ በትግራይ ክልል የሚኖር ሲሆን 0.9 በመቶው ደግሞ በሶማሌ ክልል የሚኖር ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምእመናን በሁሉም ብሔርና ክልል ውስጥ መገኘታቸው በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን ይህም የሃይማኖታችንን ሁሉን ዓቀፋዊነትና ኅብረ ብሔራዊነት ያንጸባርቃል። ታድያ አንዳንድ ወገኖች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት «የእገሌና የእገሌ ሃይማኖት ብቻ ናት» የሚሉት በምን ላይ ተመሥርተው ይሆን?

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ የ1997 ዓ.ም. የአብያተ ክርስቲያናት፣ የካህናትና የምእመናን ብዛት

| ተ.ቁ | የሀገረ ስብከት ስም | የአብያተ ክርስቲያናት ብዛት | የምእመናን ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | አክሱም | 1035 | 1597193 |
| 2 | መቐሌ | 30 | 177894 |
| 3 | አዲግራት | 733 | 790422 |
| 4 | ሽሬ | 580 | 611241 |
| 5 | ሑመራ | 192 | 529812 |
| 6 | ማይጨው | 773 | 878951 |
| 7 | አፋር | 22 | 42345 |
| 8 | ዋግ ሕምራ | 429 | 438621 |
| 9 | ሰሜን ወሎ | 1259 | 1328125 |
| 10 | ደቡብ ወሎ | 724 | 57513 |
| 11 | ሰሜን ጎንደር | 1912 | 2697208 |
| 12 | ደቡብ ጎንደር | 1471 | 242042 |
| 13 | ምዕራብ ጎጃም | 1350 | 2168737 |
| 14 | መተከል | 94 | 179122 |
| 15 | አዊ ዞን | 629 | 800008 |
| 16 | ምሥራቅ ጎጃም | 1443 | 2230415 |
| 17 | ሰሜን ሸዋ | 1763 | 1816220 |
| 18 | ሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ | 449 | 1033371 |
| 19 | ምዕራብ ሸዋ | 393 | 945240 |
| 20 | ምሥራቅ ሸዋ | 319 | 10557198 |
| 21 | አርሲ | 435 | 1078314 |
| 22 | ምሥራቅ ሐረርጌ | 44 | 101676 |
| 23 | ምዕራብ ሐረርጌ | 72 | 201543 |
| 24 | ባሌ | 151 | 411699 |
| 25 | ምሥራቅ ወለጋ | 345 | 516322 |
| 26 | ምዕራብ ወለጋ | 322 | 228039 |
| 27 | ኢሉባቦር | 214 | 547874 |
| 28 | ጅማ ዞን | 250 | 399990 |
| 29 | ኦጋዴን | 9 | 51821 |
| 30 | ድሬደዋ | 13 | 77251 |
| 31 | አሶሳ | 86 | 68275 |
| 32 | ጉራጌ | 311 | 395846 |
| 33 | ሲዳሞ | 103 | 552974 |
| *34 | ቦረና | | |
| 35 | ሰሜን ኦሞ | 206 | 429997 |
| 36 | ደቡብ ኦሞ | 24 | 31091 |
| 37 | ከፋ ሸካ | 98 | 131402 |
| 38 | ጋምቤላ | 24 | 29991 |
| 39 | ወላይታ ዳውሮ | 206 | 365979 |
| 40 | አዲስ አበባ | 114 | 4561535 |
| 41 | ሐድያና ስልጤ | 94 | 76374 |
| 42 | ከምባታ አላባ ጠምባሮ | 67 | 120850 |
| 43 | ወሊሶ | 256 | 645380 |
| 44 | ከፋ | 177 | 314405 |
| | ጠቅላላ ድምር | 19,221 | 45,392,106 |

* የቦረና ሀገረ ስብከት መረጃ ለዚህ እትም አልደረሰልንም።

ምንጭ፦ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ የ1997 ዓ.ም መረጃ



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምእመናን የመቶኛ ሥርጭት በብሔር
/1994 ዓ.ም/

| | ብሔር | ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት | የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምእመናን ብዛት | የምእመናኑ ብዛት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አፋር | 972,766 | 2,148 | 0.2 |
| 2 | አገው አዊ | 397,494 | 395,946 | 99.6 |
| 3 | አገው /ካሚር/ | 158,225 | 157,313 | 99.4 |
| 4 | አማራ | 16,010,892 | 13,420,756 | 83.8 |
| 5 | አኙዋክ | 45,656 | 8,764 | 19.2 |
| 6 | አርቦሬ | 6,622 | 1,306 | 19.7 |
| 7 | አርጎባ | 62,913 | 1,664 | 2.6 |
| 8 | አሪ | 155,065 | 36,207 | 23.3 |
| 9 | ባስኬቶ | 51,089 | 24,335 | 47.6 |
| 10 | ቤንች | 173,149 | 9,884 | 5.7 |
| 11 | ሺ | 13,164 | 213 | 1.6 |
| 12 | መር | 1,195 | 190 | 15.9 |
| 13 | ቡርጂ | 46,552 | 18,393 | 39.5 |
| 14 | ጫራ | 6,976 | 96 | 1.4 |
| 15 | ዳሰነች | 32,094 | 310 | 1.0 |
| 16 | ዲሚ | 6,189 | 724 | 11.7 |
| 17 | ደዚ | 21,888 | 12,269 | 56.1 |
| 18 | ፈላሻ | 2,306 | 128 | 5.6 |
| 19 | ጋንጁሌ | 1,142 | 126 | 11.0 |
| 20 | ጌድኦ | 639,879 | 86,734 | 13.6 |
| 21 | ገዋዳ | 33,945 | 3,575 | 10.5 |
| 22 | ጊዶሌ | 54,339 | 11,558 | 21.3 |
| 23 | ጓጉ | 165 | 82 | 49.7 |
| 24 | ጉሙዝ | 121,481 | 17,957 | 14.8 |
| 25 | ጉራጌ | 2,290,334 | 818,450 | 35.7 |
| 26 | ሐዲያ | 927,747 | 208,040 | 22.4 |
| 27 | ማረቆ | 38,093 | 8,436 | 22.1 |
| 28 | ሐመር | 42,448 | 356 | 0.8 |
| 29 | ሐራሪ | 22,884 | 375 | 1.6 |
| 30 | ጀበላዊ | 118,670 | 2,306 | 1.9 |
| 31 | ፌዳሺ | 7,323 | 17 | 0.2 |
| 32 | ጋሚሊ | 184 | 120 | 65.2 |
| 33 | ጌባቶ | 67 | 34 | 50.7 |
| 34 | ቀጨማ | 2,735 | 513 | 18.8 |
| 35 | ከፋ | 599,146 | 444,187 | 74.1 |
| 36 | ሞቻ | 53,846 | 27,110 | 50.3 |
| 37 | ቅማንት | 172,324 | 171,877 | 99.7 |
| 38 | ከምባታ | 499,632 | 70,466 | 14.1 |
| 39 | አላባ | 125,894 | 2,103 | 1.7 |
| 40 | ቀቤና | 35,065 | 522 | 1.5 |
| 41 | ጠምባሮ | 86,499 | 24,652 | 28.5 |
| 42 | ቀዋማ | 140 | 69 | 49.3 |
| 43 | ኮማ | 1,522 | 77 | 5.1 |
| 44 | ኮንሶ | 153,407 | 7,692 | 5.0 |
| 45 | ኮይሬ | 107,586 | 12,595 | 11.7 |
| 46 | ኩናማ | 2,003 | 1,584 | 79.1 |
| 47 | ማባን | 21 | 11 | 52.4 |
| 48 | ማኦ | 16,226 | 2,717 | 16.7 |
| 49 | ሜኤን | 52,808 | 1,200 | 2.3 |
| 50 | ቦዲ | 4,685 | 26 | 0.6 |
| 51 | ማሊዮ | 46,458 | 479 | 1.0 |
| 52 | መሰንጎ | 15,329 | 542 | 3.5 |
| 53 | ሞሲያ | 9,205 | 4,595 | 49.9 |
| 54 | ሙርሲ | 3,254 | 78 | 2.4 |



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 55 | ናኦ | 4.004 | 981 | 24.5 |
| 56 | ኑዌር | 64,527 | 2,632 | 4.1 |
| 57 | ኛንጋቶም | 14,201 | 24 | 0.2 |
| 58 | ኦሮሞ | 17,088,136 | 6,330,237 | 37.0 |
| 59 | ወርጂ | 20,480 | 685 | 3.3 |
| 60 | አይዳ | 14,059 | 1,755 | 12.5 |
| 61 | ሳሆ | 23,258 | 9,539 | 41.0 |
| 62 | ሸኮ | 23,772 | 2,269 | 9.5 |
| 63 | ሺናሻ | 32,660 | 31,668 | 97.0 |
| 64 | ሺታ | 290 | 65 | 22.4 |
| 65 | ሲዳማ | 1,842,444 | 47,328 | 2.6 |
| 66 | ሶማሌ | 3,139,422 | 2,142 | 0.1 |
| 67 | ሱሪ | 19,616 | 276 | 1.4 |
| 68 | ትግራዋይ | 3,284,443 | 3,148,658 | 95.9 |
| 69 | ፀማይ | 9,699 | 455 | 4.7 |
| 70 | ወላይታ | 1,268,443 | 506,360 | 39.9 |
| 71 | ዶርዜ | 28,969 | 24,716 | 85.3 |
| 72 | ጋሞ | 719,862 | 305,372 | 42.4 |
| 73 | ጎፋ | 241,818 | 85,895 | 35.5 |
| 74 | ኮንታ | 49,625 | 21,480 | 43.3 |
| 75 | ኮሎ | 331,477 | 136,371 | 41.1 |
| 76 | ሜሎ | 20,181 | 5,911 | 29.3 |
| 77 | ወይጦ | 1,631 | 51 | 3.1 |
| 78 | ዬምሳ | 165,771 | 71,985 | 43.4 |
| 79 | ዘይሲ | 10,842 | 1,601 | 14.8 |
| 80 | ዘርጉላ | 390 | 138 | 35.4 |
| 81 | ኤርትራውያን | 62,120 | 55,080 | 88.7 |
| 82 | ጅቡቲያውያን | 806 | 47 | 5.8 |
| 83 | ሶማልያውያን | 34,480 | 68 | 0.2 |
| 84 | ሱዳናውያን | 1959 | 462 | 23.6 |
| 85 | ሌሎች የውጭ ዜጎች | 17,731 | 2199 | 12.4 |
| 86 | ያልተገለጹ | 5698 | 1934 | 33.9 |
| | ጠቅላላ ድምር ............... | 53,130,783 | 26,877,658 | 50.6 |

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ክልላዊ ሥርጭት በመቶኛ /1994 ዓ.ም/

| ተ.ቁ | ክልል | የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን /በመቶኛ/ |
|---|---|---|
| 1 | ትግራይ | 95.4 |
| 2 | አፋር | 3.8 |
| 3 | አማራ | 81.4 |
| 4 | ኦሮሚያ | 41.3 |
| 5 | ሶማሌ | 0.9 |
| | ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 34.8 |
| 7 | ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች | 27.6 |
| 8 | ጋምቤላ | 24.1 |
| 9 | ሐረሪ | 38.1 |
| 10 | አዲስ አበባ | 82.0 |
| 11 | ድሬዳዋ | 34.5 |
| | ጠቅላላ ድምር ................................<br>በመቶኛ ........................................ | 26.877,657<br>50.6 |

ምንጭ:- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ቢሮ የ1994 ዓ.ም ኢሐዛዊ መረጃ

© ማኅበረ ቅዱሳን 

# ለማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ግንባታ የበኩልዎን አስተዋፅኦ ያበርክቱ!!!







በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት መስጠት የጀመረው በተደራጀ ቢሮ እና በተሟላ የሰው ኃይል አልነበረም:: ይልቁንም ጥቂት የቤተ ክርስቲያን ልጆች በዛፍ ጥላ ሥር በመሰባሰብ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት በጀመሩት አገልግሎት ነው:: በማኅበሩ የአገልግሎት ታሪክ ከዛሬ 14 ዓመት በፊት በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሕንፃ ላይ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በነበረች ሁለት ሜትር በሁለት ሜትር ስፋት ያላት የመታጠቢያ ክፍል ገንዳውን ደፍኖ እንደ ቢሮ በመጠቀም ሐመር መጽሔትንና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን ማዘጋጀት እንደ ጀመረ ይታወቃል::

ከጊዜ ወደ ጊዜ አገልግሎቱ እየሰፋና አባላቱ እየበዙ ሲመጡ ተጨማሪ ቢሮ መከራየት አስፈላጊ ነበር:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማኅበሩ ዛሬ እስከ ሚገኝበት ጽ/ቤት ድረስ በተበታተኑና በተለያዩ ቦታዎች ላይ ቤት በመከራየት መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: ይሁን እንጂ አከራዮቹ «ዋጋ ጨምሩ፣ ያለዚያም ልቀቁ» እያሉ እንዳሻቸው የሚናገሩትን የማስፈራሪያ ቃል ሁል ጊዜ ማኅበሩ እየሰማ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ለመስጠት ፈተና ስለ ሆነበት የራሱን ጽ/ቤት መገንባት እንዳለበት በ1994 ዓ.ም ወሰነ:: እግዚአብሔር ፈቅዶ በውሳኔው መሠረት ከመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ፊት ለፊት ለቤተ ክርስቲያን ቅን አሳቢ ከሆኑ ምእመናን ቤት ሰዎች ቦታውን ለመግዛት ቻለ::

ማኅበሩ ጽ/ቤት ለመገንባት ሲወስን በወቅቱ አስተማማኝ የገንዘብ አቅም ኖሮት አልነበረም:: የቦታውን ግዥ ለመፈጸም ለጊዜው በቂ ገንዘብ ስለሌለው አባላቱ ተበድረውና የወር ደመወዛቸውን አዋጥተው ግዢው ተፈጽሟል::

ማኅበሩ በቀጣይ የሕንፃ ግንባታውን ለማከናወን በቋሚነት የሚያገኘው ገንዘብ የለም:: ወደ ግንባታው ሥራ ሲገባ እግዚአብሔርን አጋዥ፣ አባላትንና በጎ አድራጊ ምእመናንን ተስፋ በማድረግ ነው:: ስለዚህ *«ጋን በጠጠር ይደገፋል»* እንዲሉ ማኅበረ ቅዱሳን ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን መንፈሳዊ አገልግሎት በላቀና በተቃና መልኩ ለመፈጸም እንዲያስችለው ለሚያሠራው ሕንፃ አባላትና በጎ አድራጊ ምእመናን በሙሉ በጸሎት፣ በሐሳብ፣ በገንዘብና በጉልበት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ጥሪውን ያስተላልፋል::

አድራሻ:-
ለማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ግንባታ
አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የሒሳብ ቁጥር 062
TEL. 011-1- 57 56 08 P.O.Box 80078
E-mail: Seramerar see@eotc-mkidusan.org
Http://www-geocities.Com/genbta

ረድኤት እግዚአብሔር አይለየን
የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ግንባታ ዐቢይ ኮሚቴ

ሜጋ ማተሚያ ድርጅት

ዋጋ ብር 3.50

© ማኅበረ ቅዱሳን
ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣ እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው።